# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ

በ


ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ


ለኢትዮጵያ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


አዲስ አበባ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም

# አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ


## የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

## የአማርኛ ቋንቋ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል


## የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ


በ

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ


ለኢትዮጵያ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት


አማካሪ

ቴዎድሮስ ገብሬ (ተባባሪ ፕሮፌሰር)



አዲስ አበባ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

የሂዩማኒቲስ፣ የቋንቋዎች ጥናት፣ የጆርናሊዝም እና የኮሚዩኒኬሽን ኮሌጅ

የአማርኛ ቋንቋ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

የድኅረ ምረቃ መርሃ ግብር

# የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ

በ

ወንድወሰን ሽመልስ ታደሰ

ለኢትዮጵያ ሥነ- ጽሑፍና ፎክሎር የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ የቀረበ ጥናት

*ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም*

<u>የፈተና ቦርድ አባላት</u>

የአማካሪ ስም፡ ______________________________ ፊርማ ______________

የውስጥ ፈታኝ ስም፡ ________________________ ፊርማ ______________

የውጭ ፈታኝ ስም፡ ________________________ ፊርማ ______________

## ማረጋገጫ

ይህ ጥናት (ቴሲስ) የእኔ መሆኑንና የተገለገልኳቸውን ምንጮችም በአግባቡ መጥቀሴን በፊርማዬ አረጋግጣለሁ፡፡

ስም፡-

ፊርማ፡-

የኢትዮጵያ ሥነ-ጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል

አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ

ሰኔ፣ 2010 ዓ.ም

# ምስጋና

ከሁሉም በፊት፣ ሁሉን ነገር በጊዜው ውብ አድርጎ ለሚሰራ፣ የልጆቼን ብርታት እንጂ ተፈትኖ መውደቅ ለማይሻው የድንግል ማርያም ልጅ ልዑል እግዚአብሔር ክብርና ምስጋና ይግባው!!!

በመቀጠል ውድ ጊዜህን ሰውተህ፣ የእኔን የተጣመሙ ሀሳቦች አቃንተህ፤ የጎደሉትንም እንዳሟላ የሚነበቡ ጽሑፎችን በመስጠት ጭምር አግዘህ፤ ስዘናጋና ፈር ስለቅቅ ተቆጥተህ፣ ጥናቴ ለዚህ ደረጃ እንዲደርስ ሳትሰለቸኝ በፍጹም ቅንነት ላገዝከኝ መምህሬና አማካሪዬ ተባባሪ ፕሮፌሰር ቴዎድሮስ ገብሬ፣ ምስጋናዬ የላቀ ነው፡፡ በቀጣይም ቅንነት ከተመላውና ከማትሰስተው እውቀትህ እያካፈልክ የምትዘልቅበትን እድሜና ጤና ፈጣሪ ይስጥህ፡፡

ምንም እንኳን የምርምር በጀት ባይመድብልኝም፣ የመማር እድሉን ስላገኘሁበት አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲን ላመሰግን እወዳለሁ፡፡ ጥናቴን ሳከናውን የምፈልገውን መረጃ ስጠይቅ ፊታቸውን ሳይቀይሩብኝ ላገለገሉኝ የዩኒቨሲቲው የቤተ መጻሕፍት ሰራተኞችም ምስጋናዬ ይድረሳቸው፡፡

በችግሬ ተቸግረው፣ በጥድፊያዬ ተጣድፈው፣ በሃሳብና በቁሳቁስ ድጋፋቸው ላልተለየኝ የስራ ባልደረቦቼና ጓደኞቼም ምስጋናዬ ከልብ ነው፡፡

በመጨረሻም፣ ለትምህርቴ ከዳር መድረስ ሲደግፉኝና ሲያበረታቱኝ ለነበሩ ቤተሰቦቼ፤ በተለይም ከእኔ ብዙ ስትፈልግ፣ በአንድ በኩል ለስራዬ በሌላ በኩል ለትምህርቴ ስባዝን ጥቂት ጊዜ እንኳን ልሰጣት ባልቻልኩበት ወቅት ከማኩረፍ ይልቅ አበረታተሽ፣ ከመከፋት ይልቅ ነገን ተስፋ አድርገሽ እውነተኛ አጋርነትሽን ላሳየሽኝ ካሳዬ ተጎድ፣ ከልብ የመነጨ ምስጋናዬ ይድረስሽ፡፡

# አጠቃሎ

ይህ ጥናት "የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በየሕሊና ባርነት ልቦለድ ውስጥ" በሚል ርዕስ የተከናወነ ሲሆን፣ በልቦለዱ ውስጥ የሰብዓዊነት መንጠፍ እንዴት ቀረበ የሚለውን የማሳየት ዓላማን ይዟል፡፡ ንድፈ ሀሳባዊ ዳራውም የሞራል ፍልስፍና (የግብረ ገብ እሴቶች አንጻር) ሲሆን፣ በአውዱ (ቴክስቱ) መሰረትነት የሰብዓዊነት መንጠፍ ተተንትኖ ቀርቧል፡፡ በዚህም መሰረት ጥናቱ በልቦለዱ የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ኪናዊ ፈርጆች ምን እንደሆኑ በመለየት ኪኖቹ የሚኖራቸውን ረብ ለመመርመር ሞክሯል፡፡

ጥናቱ በትንታኔው ለሰብዓዊነት መንጠፍ ምክንያት ከሆኑ እስቦችና ክዋኔዎች (ከሃሳብ እስከ ተግባር የሚገለጹትን ለማለት ነው) በልቦለዱ ውስጥ ለሰብዓዊነት መንጠፍ መሂሻነት እንዴት እንደተከሰቱ እና የቀረቡበት አግባብ የደራሲውን ርዕይ ከማሳየት አኳያ ያላቸው ረብ በጽንሰ ሃሳብ መተንተኛነት ከየታሪኮቹ በሚወሰዱ አስረጂዎች አማካኝነት አቅርቧል፡፡ በዚህም የልቦለዱ ታሪክ ፊት ለፊት ይዞ ከቀረበውና እንደ ሰም ማልበሻ ሆነው ከሚያገለግሉት ውቅሮች ባሻገር፣ ልቦለዱ ሲመረመር ሰው እንደ ሰው አካል ገዝፎ እየታየ ነገር ግን የሰውነት ባህሪን ሲያጣ፣ ግብረገባዊ እሴቱ ሲከስም፣ በአጠቃላይ የሰውነት መገለጫዎቹ ሲነጥፉበት ይታያል፡፡

በልቦለዱ የሰብዓዊነት መንጠፍ በዋናነት በሁለት መልኩ የተከሰተ ሲሆን፣ አንዱ የሰው ልጅ ሰዋዊ ባህርይና ምግባሩን ትቶ ከእንስሳት ጎራ ተቀላቅሎና በዚሁ ተገልጾ የታየበት የ"አኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዛሽን" ፈርጅ ነው፡፡ ሁለተኛውም ደግሞ የሰው ልጅ ከሰውነት ሚዛን ወርዶ በቁስ ሚዛን የተለካበትና እንደ እቃ የተቆጠረበት የ"ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽ" ፈርጅ ነው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ፣ በልቦለዱ ውስጥ የሰው ልጆች የግብረ ገብ (ሞራል) እሴቶቻቸውን ቸል ብለው፣ ስብዕናቸውን ረስተው፣ ራስ ወዳድነትን አንግሰውና አብሮነትን ዘንግተው ራሳቸውን ከእንስሳት ጎራ አስመድበው፣ ከቁስ ተርታም ተሰልፈው በዛው መጠን አንዱ ሌላኛውን የገለጸበትን ሂደት ለመመርመር ጥረት አድርጓል፡፡

# ማውጫ

ምስጋና ---------------------------------------------------------------------------------- i

አጠቃሎ ---------------------------------------------------------------------------------- ii

1. መግቢያ ---------------------------------------------------------------------------- 1

1.1. የጥናቱ ዳራ ------------------------------------------------------------------ 1

1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት --------------------------------------------------- 3

1.3. የምርምር ጥያቄዎች ------------------------------------------------------- 3

1.3.1. ዓብይ ጥያቄ ------------------------------------------------------------- 3

1.3.2. ንዑሳን ጥያቄዎች ------------------------------------------------------- 3

1.4. የጥናቱ ዓላማ ------------------------------------------------------------------ 4

1.4.1. ዋና ዓላማ ------------------------------------------------------------------ 4

1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች ------------------------------------------------------- 4

1.5. የጥናቱ ፋይዳ ------------------------------------------------------------------ 4

1.6. የጥናቱ ወሰን ------------------------------------------------------------------ 5

1.7. የጥናቱ አደረጃጀት ------------------------------------------------------------ 5

1.8. የጥናቱ ዘዴ ------------------------------------------------------------------- 6

1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች ------------------ 6

2. ክለሳ ድርሳን -------------------------------------------------------------------------- 8

2.1. የሞራል (ግብረ ገብ) ፍልስፍና ---------------------------------------------- 8

2.2. የሰብዓዊነት መንጠፍ ------------------------------------------------------ 14

2.2.1. "አኒማልስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" እና "ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" ----- 18

2.3. የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ ---------------------------------------------------------- 22

3. ትንተና ---------------------------------------------------------------------------------- 29

3.1. የሰብዓዊነት መንጠፍ በየሕሊና ባርነት፡ ከሞራል ፍልስፍና አንጻር -- 29

3.1.1. የሰብዓዊነት መንጠፍ ከ“አኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን” አንጻር--- 30

3.1.2. የሰብዓዊነት መንጠፍ ከ“ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን” አንጻር ----- 40

4. ማጠቃለያ ------------------------------------------------------------------------------ 51

ማጣቀሻ ጽሑፎች ------------------------------------------------------------------------------ 54

# 1. መግቢያ

የሰው ልጆችን ማህበራዊ ጉዳዮች፣ የስነ ልቡናና የፍልስፍና እስቦች፣ ተግባራት ከሚንጸባርቁባቸው አውዶች አንዱ ሥነ ጽሑፍ ነው፡፡ በእነዚህ የፍልስፍና እስቦች መስመር ተጉዞ የሥነ ጽሑፍን ጉዳይ ለመረመረ ደግሞ፤ ሥነ ጽሑፍ የሰው ልጆችን ሰዋዊ ባህርይ እና ማህበራዊ ግንኙነት የሚመለከት ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ አንድ ደራሲ ደግሞ የማህበረሰብ አባል እንደመሆኑና ከዚሁ ማህበር እንደመገኘቱ በተረዳውና ባወቀው ልክ የማህበረሰቡን እውነት ያቀርባል፡፡ ደራሲ ነቢዩ ኢያሱም በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ ይሄንኑ የማህበራዊ ተግባርና ግንኙነት አውጥቶ ያሳየበትና የሄሰበት ነው፡፡ እኔም ይሄን ጥናት "የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ውስጥ" በሚል ርዕስ ለማከናወን ስነሳ፤ ይህ ድርሰት ለጥናቴ ለመረጥኩት የሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ በብዙ መልኩ መከሰቻ ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የሰብዓዊነት መንጠት ፈርጆች ተለይተው ከሞራን ፍልስፍና አንጻር ተመርምረዋል፤ ኪናዊ ፋይዳቸውም ተለይቶ ከቴክስቱ በተወሰዱ ማስረጃዎች ተደግፎ በትንተና ቀርቧል፡፡

ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋሉ የንድፈ ሀሳብም ሆኑ የጽንሰ ሀሳብ ማጣቀሻዎች በአመዛኙ በኢንግሊዘኛ ቋንቋ ተጽፈው የተገኙ እንደመሆናቸው፤ ከምንጮቹ የተወሰዱ ጥቅሶች ተተርጉመው ቀርበዋል፡፡ ሆኖም አልፎ አልፎ በአማርኛ የቀረበው ትርጉም የኢንግሊዘኛውን ሙሉ ሀሳብ መግለጽ የማይችል ሊሆን ስለሚችል የኢንግሊዘኛው ጽሑፍ በአማራጭነት አብሮ ቀርቧል፡፡ ከዚህ ባለፈም የተወሰደው ጥቅስ ከሚተረጎም ይልቅ እንዳለ መቀመጡ የተሻለ ሆኖ ሲገኝም በየማብራሪያዎች መሃል የእንግሊዘኛው ሀሳብ ሳይተረጎም እንዳለ ቀርቧል፡፡

## 1.1. የጥናቱ ዳራ

የሰብዓዊነት መንጠፍ የሚለው ጽንሰ ሀሳብ የሰው ልጆች ከሰብዓዊ ባህሪያቸው ውጪ የሆነ ወይም ያፈነገጠ ተግባርን ማከናወንን የሚመለከት ሲሆን፤ ይህ ተግባር ግን እንደ ሙያ መስኩና እንደየማህበረሰቡ ባህል፣ ወግና ግብረገባዊ እሴት የሚለያይ ነው፡፡ ከሰብዓዊነት እሳቤና ተግባር በከፊል ወይም በሙሉ ባፈነገጠና በወጣ መልኩ

የሚገለጽም ነው፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍ ሰዎች የሰብዓዊ እሴቶችን ማፍረሳቸውን፤ እንደ ሰው የሚያስቆጥራቸውን ተግባር ተቃርነው መገኘትን፤ የሰዎችን የሃሳብና ተግባር መዝቀጥ፤ በሕሊና መጠቀም አለመቻልን፤ የግል ነጻ ፈቃድን አለመጠቀምንና የሰዎች ከሰው በታች ተደርጎ መታየትን፤ በጥቅሉ ሀሳብና ስሜትን በመተግበር ረገድ የሚገለጽ ሰፊ ጽንሰ ሀሳብ ነው፤ [ዮናስ (1992)፣ Smith (2014)፣ Luna (2015)፣ Haslam (2006)፣ Oliver, (2011)]፡፡

ይህ የሰብዓዊነትና የሰብዓዊነት መንጠፍ ትይዩነት ወይም ተቃርኖና መዛነቅ ደግሞ ከሰዎች ግብረገባዊ እሴት አንጻር ይለካል፤ ይመዘናል፡፡ ምክንያቱም፣ የሰብዓዊነት መንጠፍ ሲነሳ የግብረ ገብነት እሴት (የሞራል ፍልስፍና) ቸል ሳይባል ግለሰቦች ወይም ቡድኖች በምን መልኩ የግብረ ገብ እሴቶችን ጥሰውና ሰብዓዊነታቸውን ዘንግተው ሰብዓዊነታቸው ነጠፈ የሚለውን ለመመዘን የሚያግዝ ነው፤

> *Dehumanization undermines ways of viewing that have moral implications (e.g. Haslam, 2006; Hinton, 1996; Leyens, 2009; Scheck, 2006; Uvin, 1997). These moral implications determine what is good and bad, acceptable and non-acceptable towards an in-group versus an out-group. By framing others as something other than human, the dehumanizer challenges their sense of individuality, identity and community (Kelman, 1973), enables their moral exclusion and group discrimination (Opotow, Gerson, & Woodside, 2005); [በLuna 2015, ገጽ፣ 19 የተጠቀሰ].*

እንደ McKay and Whitehouse, (2014)፣ ደግሞ፣ ግብረ ገብነት አንድም በባህል፣ አንድም በሃይማኖታዊ እሴቶች ተጽዕኖ ስር ይወድቃል፡፡ Henry, (2005)፣ በበኩሉ የሰው ግብረ ገብነት የሰው ልጅ በፈጣሪ ፍላጎት ላይ ተመስርቶ የሚገነባው እሴት መሆኑን ያስረዳል፡፡ የአማርኛ ልቦለዶችን በማጥናት ሂደት ውስጥ ደግሞ በበርካታ ጽንሰ ሀሳቦች የተከናወኑ ስራዎች ቢኖሩም፤ በአማርኛ ልቦለዶች የሚስተዋሉ የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችም ሆነ ረቦቻቸውን ለማመላከት የተደረጉ ጥናቶችን ማግኘት አልቻልኩም፡፡ እኔም በጥናቱ በልቦለዱ ውስጥ የተከሰቱ የሰብዓዊነት መንጠፍ ፈርጆችን ስፈትሽ ከግብረ ገብ እሴቶች አንጻር በመተንተን ኪናዊ ፋይዳቸውን ለማቅረብ ጥረት አድርጌያለሁ፡፡

## 1.2. የጥናቱ አነሳሽ ምክንያት

*የሕሊና ባርነት* በሚል ርዕስ በነቢዩ ኢያሱ የተደረሰው ይህ ልቦለድ ምንም እንኳን የሂስ መድረክ ያላገኘ ቢሆንም፤ ልቦለዱን በትኩረት ለተመለከተው የሰው ልጆችን የስብዕና ደረጃ ፍንትው አድርገው ለማሳየት በኪን ተቀምረው በቀረቡ ፈርጆች የተመላ፤ የማህበራዊ ሂስን በውስጣቸው አቅፈው ፊት ለፊት ቀርቦ እኔን ብቻ ተከተሉ በሚል ታሪክ የተሸፈኑ አያሌ ቁምነገሮችን የያዘ ነው፡፡

አንድ ደራሲ የአንድ ማህበረሰብ አባል እንደመሆኑ፣ ባወቀውና በተረዳው ልክ ከሰፊው ማህበራዊ አውድ ወስዶ የሚያቀርበው ልቦለድ ቢጠና የማህበራዊ አስተሳሰቦችና ምግባራትን የሚነቅስበት አንዳች ጉዳይ አያጣም የሚል እምነት አለኝ፡፡ እኔም "የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ" በሚል ርዕስ ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቴን በዚህ ልቦለድ ላይ ለማከናወን ስነሳ ልቦለዱን ከሰብዓዊነት መንጠፍ አኳያ የሚያነሳቸው ማህበራዊ ሂሶች ስለመኖራቸው ለመፈተሽ ባደረብኝ ፍላጎት ነው፡፡

ከዚህ ባለፈ ግን ልቦለዱ አንደኛ የጋዜጠኝነት ሙያን መሰረት አድርጎ መቅረቡ፤ ሁለተኛም ጥናቱን በማከናውንበት ወቅት የምሰራበት ድርጅት በተለይም የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ጋዜጠኞችና ዋና አዘጋጅ ሙያዊና የግብረ ገባዊ ኃላፊነታቸውን የሚመለከቱ ጉዳዮችንም የሚመለከት መሆኑ፣ ልቦለዱን ለጥናቴ እንድመርጠው ተጨማሪ ምክንያት ሆኖኛል፡፡

## 1.3. የምርምር ጥያቄዎች

### 1.3.1. የምርምሩ ዓብይ ጥያቄ

በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ የሚስተዋሉ የሰብዓዊነት መንጠፍ ውቅሮች እንዴት ተከስተዋል? የሚል ነው፡፡

### 1.3.2. ንዑሳን የምርምር ጥያቄዎች

በጥናቱ ከሚነሱ ንዑሳን ጥያቄዎች መካከል፦

- በልቦለዱ ውስጥ የሰብዓዊነት መንጠፍ መንስኤዎች ምንድን ናቸው?

- በልቦለዱ ውስጥ የሰብዓዊነት መንጠፍ ያለው ግለሰባዊና ማህበራዊ ገጽታ እንዴት ይገለጻል?
- በልቦለዱ ውስጥ ያሉ ገጸ ባህሪያት በሰብዓዊነት መንጠፍ ውስጥ መግባታቸውን ያውቁታልን?
- ከገቡበት የማህበራዊ እሴት ቀውስ ለመውጣትስ ምን ጥረት ያደርጋሉ? የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 1.4. የጥናቱ ዓላማ

### 1.4.1. ዋና ዓላማ

የዚህ ጥናት ዋና ዓላማ በ*የሕሊና ባርነት* ውስጥ የሰብዓዊነት መንጠፍ እንዴት እንደቀረበ መመርመር ነው፡፡

### 1.4.2. ዝርዝር ዓላማዎች

ጥናቱ በዝርዝር ዓላማነት ከያዛቸው ጉዳዮች መካከል፡-

- ለሰብዓዊነት መንጠፍ የሚያጋልጡ ሁነቶችንና ሁኔታዎችን መለየት፤
- የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰት በገጸ ባህሪያቱ ላይ የሚያሳድረውን/ያሳደረውን ተጽዕኖ መግለጽ፤
- ከልቦለዱ በሚወሰዱ ታሪኮች ማሳያነት የሰብዓዊነት መንጠፍን ከሞራል ፍልስፍና አንጻር መመርመር፤ የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፡፡

## 1.5. የጥናቱ ፋይዳ

አንድ ጥናት ሲከናወን ይብዛም ይነስ የራሱ የሆኑ ፋይዳዎች አሉት፡፡ የዚህ ጥናት መከናወንም የሚያበረክታቸው ፋይዳዎች ይኖሩታል፡፡ ከእነዚህ መካከልም፤ አጥኚው ይሄን ጥናት ለማከናወን የተለያዩ ጽሑፎችን ማንበቡ ጥናቱ ትኩረት ባደረገበት የሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብና የሞራል ፍልስፍና ንድፈ ሀሳብ ዙሪያ የተሻለ ግንዛቤ እንዲጨብጥ አድርጎታል፡፡ ጥናቱን የሚያነብ ሰውም ቢሆን ተጨማሪ እውቀት የሚያገኝበት ነው፡፡ ከዚህ ባለፈም ቀደም ሲል ትኩረት ያላገኙ እንደ *የሕሊና ባርነት*

አይነት ልቦለዶች በተለያዩ ንድፈ ሀሳቦችና ጽንሰ ሀሳቦች ሊታዩና ሊፈተሹ እንደሚችሉ ጠቋሚ ይሆናል፡፡ ለሌሎች አጥኚዎችም እንደ ግብዓት ያገለግላል፣ አዲስ የጥናት ሀሳብ እንዲያፈልቁም አቅጣጫን ያመላክታል፡፡

## 1.6. የጥናቱ ወሰን

"የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆችና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ" በሚል ርዕስ የሚከናወነው ይህ ጥናት ለሰብዓዊነት መንጠፍ ምቹ ሆኖ ባገኘሁት በነቢዩ ኢያሱ *የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ላይ ብቻ ተወስኖ የሚከናወን ሲሆን፣ ጥናቱ በልቦለዱ ውስጥ ገጸ ባሕሪያቱ በሚኖራቸው የእርስ በእርስ መስተጋብር (በሚፈጠርላቸው አውድ)[1] ላይ በማተኮር የሚመረመር ይሆናል፡፡

## 1.7. የጥናቱ አደረጃጀት

በልቦለዱ ውስጥ የሚታይን የሰብዓዊነት መንጠፍ ለመመልከት ይረዳኝ ዘንድ ጥናቱን በአራት ክፍል አደራጅቼ አቅርቤዋለሁ፡፡

የመጀመሪያው ክፍል የጥናቱን ዳራ፣ ጥያቄ፣ ዓላማ፣ አነሳሽ ምክንያት፣ ወሰን፣ ፋይዳና ዘዴን ይዟል፡፡ ሁለተኛው ክፍል ደግሞ ጥናቱ የተመሰረተበትን ጽንሰ ሃሳብ፣ ንድፈ ሃሳባዊ ዳራ እንዲሁም ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው የጥናት ስራዎች (የተዛማጅ ጽሑፍ) ቅኝት ተደርጎበታል፡፡

በሦስተኛው ክፍልም በሁለተኛው ክፍል የቀረቡትን ጽንሰ ሀሳብና ንድፈ ሃሳብ መሰረት በማድረግ ገጸ ባህሪያቱ እንደምን የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ሆኑ የሚለውን ለማሳየት ይቻል ዘንድ ልቦለዱ (ቴክስቱ) የተተነተነበት ነው፡፡

አራተኛውና የመጨረሻው ክፍል ደግሞ በቴክስቱ የታዩ የሰብዓዊነት መንጠፍ ሁነቶችን መሰረት በማድረግ የጥናቱ ግኝት በተጠቃለለ መልኩ ቀርቦበታል፡፡

---

[1] በገጸ ባህሪያቱ የእርስ በርስ መስተጋብር (በሚፈጠርላቸው አውድ) ላይ ብቻ በመመስረት መከናወኑ፣ በቴክስቱ ገጸ ባህሪያቱ በአካል ተገናኝተውም ሆነ በምንናብ በሚፈጥሯቸው አውዶች እንዲሁም በሦስተኛ አንጻር የሚተረከው፣ የገጸ ባህሪያቱ የታሪክ አካል ነው ብዬ ስለማምን ነው፡፡ በመሆኑም የገጸ ባህሪቱ የእርስ በእርስ መስተጋብር ተብሎ የተገለጸው በዚህ መልኩ የሚታይ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

## 1.8. የጥናቱ ዘዴ

አጥኚው በቅድሚያ በሰብዓዊነት መንጠፍ ዙሪያ አጋዥ የሆኑ የተለያዩ ጽሑፎችን አንብቧል፤ ለሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ናቸው ያላቸውን ልቦለዶችም በመለየት በብዛት ካልተሰራባቸውና ትኩረት ካላገኙት መካከል *የሕሊና ባርነትን* መርጧል፡፡ በልቦለዱ የሰብዓዊነት መንጠፍ እንዴት እንደተከሰተ ለመመርመር ይችል ዘንድም ደጋግሞ በማንበብ ፊርጆቹን በመለየት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራውን መርጧል፡፡

ለጥናቱ ጥቅም ላይ የዋለው ንድፈ ሀሳብ የሞራል ፍልስፍና በተለይም የዲኦንቶሎጂያዊ ንድፈ ሀሳብ ነው፡፡ ምክንያቱም አንድ ድርጊት ወይም ጠባይ ግብረ ገብነትን የሚመዝነው የማህበራዊ የሞራል እሴቶቹ የሚጥሉበትን የራስ ተግባር ወይም ግዴታ በሚገባ ከመፈጸም አንጻር የሚለካ ከመሆኑ ጋር ስለሚያያዝ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሰዎችን የስብዕና ደረጃ ለመመልከት የሚያግዝ ነው፡፡ በመሆኑም በዚህ ጥናት የሰብዓዊነት መንጠፍን ከማህበረሰቡ ግብረ ገባዊ እሴቶች አንጻር ለመመርመር ተሞክሯል፡፡ John Yolkowski (2011), "Literary works often take as their starting point human situations or, more generally, can reflect the moral thoughts of their author(s)" (ገጽ፣ 1)፤ እንዳለውም በአንድ ልቦለድ ውስጥ የሰብዓዊነት መንጠፍን ለመመርመር ከሞራል ፍልስፍና (የግብረ ገብ እሴቶች) አንጻር መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ለዚህም በጥናቱ ሁለተኛ ክፍል ንድፈ ሀሳባዊና ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራዎች የቀረቡ ሲሆን፤ በሶስተኛው ክፍል እነዚህ ንድፈ ሃሳባዊና ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራዎች ከልቦለዱ በሚወሰዱ ታሪኮች አማካኝነት ደራሲው በድርሰቱ ያቀረበውን የሰብዓዊነት መንጠፍ ማህበራዊ ሂስ ፊርጆች ለማሳየት ጥረት የተደረገበት ነው፡፡

## 1.9. ያጋጠሙ ችግሮችና የተወሰዱ የመፍትሄ እርምጃዎች

ይህን ጥናት ሥራ ብቻ ሳሆን ትምህርቴንም ስማር መደበኛ ሥራዬን እያከናወንኩ ነው፡፡ የጥናት ስራ ደግሞ ጥልቅ ንባብና ዕይታን የሚጠይቅ፤ ጊዜ ወስዶና ቁጭ ብሎ ማሰላሰልና አዳዲስ ጉዳዮችን መፈተሸ የግድ የሚል ነው፡፡ በተለይ ከስራዬ ጠባይ እንዲሁም በተቋማት ባለ የበዛና የተንዛዛ የስብሰባ ሂደት ጋር በተያያዘና ለዚህ የሚሆን በተለይም በቤተ መጻሕፍት የሚገኙ ማጣቀሻዎችን ለመመልከት የሚያስችል ጊዜ ለማግኘት እጅጉን ተፈትኜ ነበር፡፡ ይሁን እንጂ በራሴ ከማደርገው ጥረት በተጓዳኝ

አማካሪዬ የተለያዩ ማጣቀሻዎችን በሐርድ ኮፒና ሶፍት ኮፒ በማዋስና በኢሜል በመላክ ከፍተኛ ድጋፍ አድርጎልኝ፤ እኔም ያለኝን ጊዜ አጣብቤና እረፍትና መዝናናት ሳያምረኝ ጊዜዬን ለመጠቀም ባደረግሁት ጥረት በተወሰነ ደረጃም ቢሆን ልቋቋመው ችያለሁ፡፡

ከዚህ ባለፈም ትምህርቱን በግል ወጪ የምማር እንደመሆኑ ዩኒቨርሲቲው ለጥናት የሚሆን በጀት አልመደበልኝም፡፡ ይህም ጥላቱን ለማከናወን የሚያስችሉ ቁሳቁሶችን ለማሟላት በማደርገው ጥረት ላይ የጎላ ችግር ፈጥሮብኛል፡፡ ጥናቱን ከዳር ለማድረስ በማደርገው ጥረትም ለራሴ መሰረታዊ ፍላጎቶች ማሟያ የሚተርፍ ገንዘብ ለማግኘት ስል ማህበራዊ ግንኙነቴ እንዲቀዛቀዝ እስከማድረስ ጫና ፈጥሮብጫል፡፡ ሆኖም ነገን ተስፋ በማድረግ ዛሬዬን አጉድዬ የጀመርኩትን ጥናት ከዳር ለማድረስ ችያለሁ፡፡

# 2. ክለሳ ድርሳን

በዚህ ክፍል ከጥናቱ ጋር ተዛማጅነት ያላቸው ድርሳናት የተዳሰሱበት ሲሆን፣ በሶስት ክፍል ተደራጅተው ቀርበዋል፡፡ በመጀመሪያው ክፍል ጥናቱ የተመሰረተበት ንድፈ ሀሳባዊ ዳራ የሞራል ፍልስፍና (ግብረገብ)[2] የቀረበበት ሲሆን፣ ሁለተኛው ክፍል የሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳባዊ ዳራ የተብራራበት ነው፡፡ በሶስተኛው ክፍል ደግሞ ከጥናቱ ጋር ተያያዥነት ያላቸው ቀደምት የጥናት ስራዎች ተዳስሰው ቀርበዋል፡፡

## 2.1. የሞራል (ግብረ ገብ) ፍልስፍና

የሰው ልጅ ለራሱ ብቻ ሳይሆን ለነገሮች የሚሰጠው ጥልቅ ስሜትና ትርጉም አለው፡፡ ይሄን ሰዋዊ ነገሮችን የመረዳትና የማስረዳት ስሜቱን ደግሞ በተለያዩ የፍልስፍና መንገዶች እየመዘነ ይገልጻቸዋል፡፡ የሰው ልጅ ስሜት፣ አስተሳሰብና ምግባር ከሚገለጽባቸውና ከሚመዘንባቸው መንገዶች አንዱ ደግሞ የሞራል ፍልስፍና (የግብረ ገብ እሴት) ሲሆን፣ ይህ ፍልስፍና እንደየማህበረሰቡ ባህልና የኃይማኖት አስተሳሰብ የሚመዘን፣ የሰው ልጆችን ሰናይ ወይም እኩይ ባህሪን ለመፈተሽ የሚያስችል አይነተኛ መሳሪያ ነው፡፡ ጠና (2008)፣ የGrayling, (2002)ን ሀሳብ መነሻ አድርገው እንዳሰፈሩት፣ በግብረ ገብ ውስጥ ቁልፍ ከሆኑ የሰው ልጅ ጥያቄዎች መካከል፣ አንዱ፣ "ለሰው ልጆች እጅግ መልካም የሆነው ሕይወት የቱ ነው?" የሚል ሲሆን፣ ሁለተኛው፣ "መልካም የሆነውን ህይወት ለመገንባት የሚያስችሉ ማህበራዊ ተቋማት ምን አይነት መሆን አለባቸው?" የሚለው ነው (ገጽ፣ 21)፡፡ ይህ የሰው ልጆች በሰውነታቸው ካላቸው የግል መገለጫዎች መካከል አንዱ የሆነው ግብረገባዊ እሴታቸው ደግሞ፣ በግልም ይሁን በጋራ ያላቸውን እምነትና ፍላጎት ለማራመድ በሚያደርጉት እንቅስቃሴ ሁሉ የህሊናን ዳኝነት ያጎናጽፋቸዋል፡፡ ለግጭት እንዳይዳረጉና እርስ በእርስ እንዳይጎዳዱ መሳሪያ ይሆናቸዋል፡፡

[2] ለዚህ ጥናት በንድፈ ሃሳብነት የተገለገልኩበትን የሞራል ፍልስፍና ንድፈ ሀሳብ ሲሆን፣ የተለያዩ መዝገበ ቃላትና የጥናት ስራዎችን መነሻ በማድረግ በዚህ ጥናት ውስጥ የግብረ ገብ እሴት በሚለው አቻ የአማርኛ ትርጉም ተክቼ ተገልግዬበታለው፡፡ በመሆኑም በጥናቱ ውስጥ የሚያጋጥሙ የሞራል ፍልስፍና ወይም የግብረ ገብ እሴት የሚሉ ቃላት፣ አቻ ትርጉም የያዙ መሆኑን ለመግለጽ እወዳለሁ፡፡

ጠና፣ Raphael, (1981)ን ዋቢ አድርገው እንደሚሉት፣ ግብረ ገብ ለድርጊቶች ዋጋ ወይም እሴት ይሰጣል፤ ይወስናል፡፡ ግብረ ገብ እሴት የሚሰጠው ግን ለማንኛውም አይነት ድርጊትና ክስተት አይደለም፡፡ ምክንያቱም ማንኛውም ዓይነት ድርጊት ግብረ ገባዊ ይዘት የለውም፡፡ በመሆኑም ተጠያቂነት የሚያስከትል አይደለም፡፡ የግብረ ገብ ፍልስፍና እሴት ወይም ፋይዳ ትክክል ወይም ስህተት፣ በጎ ወይም መጥፎ፣ መደረግ ስላለበት ወይም መደረግ ስለሌለበት ድርጊት ማጥናት ላይ የሚያተኩር ነው፡፡ በዚህም ሰዎች ቀደም ብለው ትክክል ወይም ስህተት፣ ሰናይ ወይም እኩይ ብለው የፈረጇቸውን ወይም ያመኑባቸውን ነገሮች ሂሳዊና አመክንዮያዊ በሆነ መንገድ ይፈትሻል፡፡

በመሆኑም ግብረ ገብነት ለራሳቸው እንዲሆን የማይፈልጓቸውን በሰዎች እንዳያደርሱ፤ የመልካም እንጂ የእኩይ ተግባራትና ባህሪያት ተገዢ እንዳይሆኑ ይመራቸዋል፡፡ እንዲሁም ማህበራዊ ህጋቸውን የሚቀርጹበትና ትውልድን የሚያንጹበት በጥቅሉ ሰው መሆናቸው የሚጠይቃቸውን ስብዕና አሟልተው ማህበራዊ ጉድኝታቸውን እንዲያከናውኑ የሚያስችላቸው እሴታቸው ነው፡፡ ይህ ማህበራዊ ጉድኝትን የሚያጠናክረው የሰው ልጅ መልካምነት ሲነሳ ደግሞ ሁለት ነገሮች አብረው ይታሰባሉ፡፡ ይሄም አንዱ የመልካምነቱ መገለጫ አስተሳሰብና ምግባሩ ሲሆን፤ ሁለተኛው ከመልካምነት ተቃርኖ የሚቆመው የሰው ልጅ አስተሳሰብ ባህሪና ምግባር ናቸው፡፡ በመሆኑም የሞራል ፍልስፍና የሰው ልጆችን አስተሳሰብና ምግባር ለመመርመር የሚያግዝ ነው፡፡

የሞራል ፍልስፍና የሰው ልጆች አብይ ጉዳይ እንደመሆኑም የሰው ልጆችን የአስተሳሰብና ምግባር ትክክለኛ አቅጣጫ ማስተማሪያና የመልካምነት መገንቢያም ነው፡፡ የእለት ተዕለት እንቅስቃሴን የመምራት አቅም ስላለው የሰው ልጆችን ባህሪ በመቅረጽ፣ ፍትህና ህጋዊነትን በማስፈን የሰው ልጆችን የጋራ ህይወት ይገነባል፡፡ ይህ ግብረ ገባዊ እሴት የሰው ልጆች በዘመናቸው የሚያጎለብቱት፤ የሚያሳድጉትና የሚገለገሉበትም ነው፡፡ ወልደ ጊዮርጊስ (1943)፣ "ሰው በሕጻንነቱ ተክል ማለት ነው፡፡ ተክል የሚሆነውን ሁሉ ሊሆን ይችላል፡፡ ይለመልምና በልምላሜው ደስ ያሰኛል፡፡ ያብብና በአበባው የዓይን ደስታ ይሆናል፡፡ ያፈራና በፍሬው የልብ ተስፋ ይሰጣል፡፡ እንዲህ ለመሆን የሚችል ወጣት ሰውነቱን በቆሻሻ ምግባር ያቆራመደው እንደሆነ

ተስፋ ያስቆርጣል፤" (ገጽ፣ 33)፤ ሲሉ እንደገለጹትም፤ የሞራል ፍልስፍና የሰው ልጆችን ባህሪ በማጎልበት ከራስ አልፎ ለሌሎች የሚተርፍ ተጽዕኖ ያለው እሴት ነው፡፡

የRossano, (2008)ን፣ "Morality is the cultivation and application of virtue" (ገጽ፣ 170), ሚለውን ጥቅስ ቀደም ብዬ ካሰፈርኩት ከወልደ ጊዮርጊስ ተምሳሌታዊ ገለጻ ጋር ደምረን ለመረዳት ብንሞክር ደግሞ፤ ግብረ ገብነት የበጎ ምግባራት መከሰቻና ማጎልበቻ ማህበራዊ እሴት መሆኑን መገንዘብ ይቻላል፡፡ ይህ እሴት የበጎ ምግባራት ልምምድ የሚደረግበትና የሚገበይበት መድረክ እንዲሁም የሚተገበርበት አውድ አለው፡፡ Henry (2005) እንደሚያመለክተው፣ የሰው ልጆች ግብረገባዊ ሰብዕና አንድም በተፈጥሮ፣ አንድም በስምምነት የሚገኝ ነው፡፡ ሰዎች በሚኖራቸው ማህበራዊ መስተጋብርና ትስስር ተፈጥሯዊ የሆነውን ግንኙነታቸውንና እሴታቸውን መሰረት የሚያደርግ የራሳቸውን ምድራዊ ሕግ ይሰራሉ፡፡ ይህ ደግሞ የሞራል ፍልስፍና መነሻ ምን እንደሆነ እንድንፈትሽ ወይም እንድንመረምር ያስገድደናል፡፡

በዚህ ረገድ የሞራል ፍልስፍና መገኛ ተብለው በቀዳሚነት የሚታወቁት ለዘመናትም ስራውን ሲያከናውኑ የኖሩት የኃይማኖት ተቋማት ነበሩ፡፡ ይሄም የሞራል ፍልስፍና የሰው ልጆች ከሞት በኋላ ያለውን ሕይወት በማሰብ በፈጣሪ ፍላጎትና ፈቃድ ላይ ተመስርተው መልካም ነገሮችን በመፈጸም የሚያጎለብቱት በመሆኑ ነው፡፡ የሞራል ፍልስፍና ህልውና ከኃይማኖታዊ እሴት ጋር በማስተሳሰር ከሚገልጹ በርካታ ምሑራን መካከል፤ Henry (2005), "morality depends entirely on the will of God, and that his will creates the only obligation we lie under to be virtuous, is the opinion of several writers." (ገጽ፣ 66); ሲል አብራርቷል፡፡

ይሁን እንጂ የሞራል ፍልስፍናን የሃሳብና ምግባር ሂደት ከፈጣሪ ፈቃድ ባፈነገጠ መልኩ በራስ (ግለሰባዊ) ፍላጎት ላይ የሚመሰረትበት አጋጣሚ መኖሩን መዘንጋት አይገባም፡፡ Oliver, (2011)፣ ከDeutsch (2000) ወስዶ ባሰፈረው ጥቅስ፤ "At various periods in history and in different societies, groups and individuals have been treated inhumanly by other humans"; ካለ በኋላ፤ "Who is and who is not entitled to fair outcomes and fair treatment by inclusion or lack of inclusion in one's moral community?"(ገጽ፣ 86) ሲል ይጠይቃል፡፡ በመሆኑም የሰዎችን ከሞራል ፍልስፍና አስተሳሰብና ምግባር

አፈንጋጭነት ለመፈተሽ ከማህበራዊ እሴቶች ተጠግቶና ከሥነ ምግባር መመሪያዎች ጠቅሶ ለማመሳከሪያነት መጠቀሙ ተገቢ ይሆናል፡፡

ከዚህ በዘለለም የሞራል ፍልስፍና ሰፋ ያለ እሳቤን ነገር ግን የበርካቶችን የጋራ ስምምነት የያዘ እሴት ነው፡፡ ይህ ምግባር ደግሞ ከግብረ ገብነት የሚቀዱ የራሱ የሆኑ ሥነ ምግባራዊ መለኪያዎች ያሉትም ነው፡፡ Nel (2008), Morality is the sense and view of what is right and wrong …an absolute reference for character and behavior… an authoritative code of conduct in matters of right and wrong… usually seen in a broader sense than "ethics" (ገጽ፣ 35)፤ ሲል የገለጸውም ይሄንኑ ነው፡፡ ግብረገባዊ እሴቶች ምንም እንኳና እንደየ አከባቢው ባህልና ማህበራዊ ሁነቶች ሊለያዩ ቢችሉም፤ የአንድ ማህበረሰብ ወይም ቡድን አባላት በአመዛኙ የሚስማሙባቸውና ተቀብለውም የሚገዙባቸው ባህበራዊ ሀብት መሆናቸውንም የዘርፉ ባለሙያዎች ይገልጻሉ፡፡ ጠና (2008)፣ pojman, (2005)ን ዋቢ አድርገው እንዳሰፈሩት፤ "ግብረ ገብ በባህሪው ሁለንተናዊ ይዘት አለው፤ በመሆኑም ሁለንተናዊ ህግ ነው፤"[3] (ገጽ፣ 45)፤ በማለት የሚከተሉትን የግብረገብ የጋራ ባህሪያት ዘርዝረዋል፡፡ እነዚህም፡ አትዋሽ፣ ቃል ኪዳንን ጠብቅ፣ አትግደል፣ የሌሎችን ነጻነት አክብር፣ አትስረቅ ወይም አታጭበርብር፣ ሌሎች ሰዎችን እርዳ፣ ሰዎችን በዘር፣ በቆዳ ልዩነት፣ በብሔር ወይም በሃይማኖት ላይ የተመሰረተ ልዩነት አታድርግ፣ ሥቃይ የሚያስከትል ነገር በማንም ላይ አትፈጽም፣ መልካም ነገርን በመልካም እንጂ በእኩይ አትመልስ፣ ፍትሃዊና ምክንያታዊ የሆኑ ሕግጋትን አክብር የሚሉት ተጠቃሽ ናቸው፤ (ገጽ፣ 45-46)፡፡

Ronald M. Green (2014)[4] በበኩሉ ከBaier (1958) ወስዶ እንዳሰፈረው፤ የሞራል ፍልስፍና በአንድ ማህበረሰብ አባላት ዘንድ ተቀባይነት ያላቸው የምግባር ህግጋት ወይም ስርዓት እሴት ሲሆን፤ እነዚህም የአንዳችን ፍላጎት በሌላኛችን ውስጥ እንዲጠበቁ የሚያግዙ

[3] በዚህ ጥናት ውስጥ የግብረ ገብ እሴት ሁለንተናዊ ሕግ ነው ተብሎ የተገለጸው አንድ ማህበረሰብ ለማህበራዊ መስተጋብርና ጉድኝቱ የሰራቸው ማህበራዊ ህጎች የዛ ማህበረሰብ የጋራ ሕግ ሆነው ማገልገላቸውን ለመግለጽ የቀረበ ነው፡፡ ይህ ማለት ደግሞ የዛ ማህበረሰብ ማህበራዊ ህግ፣ ለዛ ማህበረሰብ እንጂ ከማህበረሰቡ ውጪ ላለ ሌላ ማህበረሰብ የሚሰራ ላይሆን ይችላል፡፡ ይህ ብቻም ሳይሆን የማህበራዊ ቡድኑ አባለት በአመዛኙ የሚቀበሉት ቢሆንም፤ ያንን እሴት የማይቀበሉ፣ የማይገዙና የማይፈጽሙ የሉም ፍጹም ሁሉንም የሚያስማማ ነው ማለት ግን አይደለም፡፡

[4] ይህ ጥናት እአአ በ2015 ኢራን ላይ በተካሄደ በሶስተኛው "contemporary philosophy of religion with focus on religion, ethics and culture," በተሰኘ ዓለም አቀፍ ኮንፍረንስ ላይ የቀረበ መሆኑን ልብ ይሏል፡፡

እና ግለሰቦችም ሆኑ ቡድኖች ይሄንኑ ለማግኘት የሚጠብቋቸውና የሚፈጽሟቸው ናቸው፡፡

> *Moralities are systems of principles whose acceptance by everyone as overruling the dictates of self-interest is in the interest of everyone alike . . . . The answer to our question "Why should I be moral?" is therefore as follows. We should be moral because being moral is following rules designed to overrule self-interest whenever it is in the interest of everyone alike that everyone should set aside his interest. (P. 24).*

McKay እና Whitehouse, (2014), እንዳመለከቱት፤ የሞራል ፍልስፍናን መሰረት ብቻ ሳይሆን ጠቅለል ያሉ መመሪያዎች ለመረዳት የሞራል ፋውንዴሽንስ ቲዎሪን (moral foundations theory) ይዞ መፈተሽ እንደሚገባ አብራርተዋል፡፡

> *Moral foundations theorists have highlighted five core foundations, giving rise to the following pan-human principles: (a) care–harm: harming others is wrong, whereas treating others with kindness and compassion is right; (b) fairness–cheating: people should reap what they sow and not take more than they deserve; (c) in group loyalty– betrayal: what is good for the community comes above selfish interests; (d) respect for authority–subversion: we should defer to our elders and betters and respect tradition; and (e) purity– degradation: the body is a temple and can be desecrated by immoral actions and contaminants; (p. 7).*

ቀደም ብዬ እንደጠቀስኩት ከጥንት ጀምሮ ግብረ ገብነት የኃይማኖት ፍሬ ተደርጎ ይቆጠር ነበር፡፡ ይሁን እንጂ የግብረ ገብነት ጉዳይ ለሃይማኖት ብቻ የሚተው ሳይሆን፤ ከቤተሰብ ጀምሮ የተለያዩ የግብረገብነት መገንቢያ ተቋማት መኖራቸውን የተለያዩ ባለሙያዎች ያስረዳሉ፡፡ ጠና (2008)፣ ምንም እንኳን ግብረገባዊ ተግባሮችን ከማከናወን አኳያ የተወሰነ ድርሻ የሌላቸው ማህበራዊ ተቋማት ባይኖሩም፤ "የግብረ ገባዊ እሴቶችንና ሕግጋትን በመፍጠር ወይም በመቅረጽ፣ በማክበርና በማስከበር፣ በማወቅና በማሳወቅ፣… ከፍተኛ ሚና ወይም ድርሻ ያላቸው ማህበራዊ ተቋማት አሉ፤" (ገጽ፣ 203)፡፡ እነዚህም የእምነት ተቋማት፣ ቤተሰብ፣ የትምህርት ተቋማትና የመንግስት ተቋማት መሆናቸውን (ገጽ፣ 203-211) ያብራራሉ፡፡

ይህ ደግሞ የሞራል ፍልስፍናን የማስረጽ ስራው ለረዥም ጊዜ በቤተ እምነቶች የተወሰነ በሚመስል መልኩ ዛሬም ድረስ ያለ ቢሆንም፤ ስራው የቤተ እምነት ብቻ እንዳልሆነ ያስረዳል፡፡ Brock Bastian እና ሌሎችም (2010)፣ "Being human implies a particular moral status: having moral value, agency, and responsibility." (ገጽ፣ 469)፣ እንዳሉት፤ የሞራል ፍልስፍና ሰፊ ገጽታ ያለው፤ ይልቁንም ከሰው ልጆች የእለት ተእለት ተግባርና እንቅስቃሴ ጋር እጅጉን የሚጣመር፤ በሰዎች የእርስ በእርስ

ግንኙነት የህሊና ዳኝነት የሚያስቀምጥ እሴት ነው፡፡ ይህም እንደየአከባቢው ኃይማኖታዊና ባህላዊ ሁኔታ በመተርጎም ሂደት የሚገለጽ ነው፡፡ በዚህም የሞራል ፍልስፍና በጎለበተ ቁጥር የሰው ልጆችን የሚያስደስቱ አስተሳሰቦች የሚጎለብቱበት ብቻ ሳይሆን እነዚሁ በተግባር የሚገለጹበት እድል ሰፊ ነው፡፡ በአንጻሩ የሞራል ፍልስፍና እየከሰመ ሲሄድ ሰዎች ለሰዎች አለኝታነታቸው ቀርቶ ስጋትና ጥፋት መሆን ይጀምራሉ፡፡

Karim እና ሌሎችም (2012)፣ "Literature and Morality" በተሰኘ ስራቸው Hyman (1971) እና Kaufman (1983)ን ጠቅሰው እንዳብራሩት፤ በኪነጥበብ በተለይም በሥነጽሑፍ ዘርፍ ያሉ ባለሙያዎች ሥራዎቻቸውን በሰዎች የሞራላዊ ፍልስፍና ላይ በማተኮር እያቀረቡ ነው፡፡ በተለይ ከ20ኛው ምዕተ ዓመት ወዲህ የሥነጽሑፍ ባለሙያዎች በድርሰቶቻቸው የሞራል ፍልስፍናን እንደ አንድ ጉዳይ ይዘው በመጻፍ ላይ ይገኛሉ፡፡ በተመሳሳይ West and Fox, (1960)ን ጠቅሰው እንደሚያስረዱት፤ ዘመናዊ ሕይወት ሁልጊዜም ለውጥ ፈላጊና በለውጥም የታጀበ በመሆኑ 20ኛው ምዕተ ዓመት የሞራል እሴቶች ገጽታዎች እየወረዱ እና እየቀሩ፣ ሰብዓዊ ኃላፊነት እየተዘነጋና የግለሰቦች መተሳሰብም እያሽቆለቆለ የመጣበት ነው፡፡ ሥነጽሁፍም የሞራል ፍልስፍናን ጉዳይ እንደ አንድ የትኩረት መስክ አድርጓል፡፡ በሥነጽሑፍ የምናገኛቸው ገጸ ባሕሪያትም የገሃዱን ዓለም ወካዮች፤ የድርሰቱ አንባቢያንም የህብረተሰቡ አካል እንደመሆናቸው በተለያየ መልኩ የሞራል ፍልስፍና አስተሳሰብ ጉዳይ የሚመለከታቸው ናቸው፡፡

በሞራል ፍልስፍና ያልተገራና በምግባር ያልታነጸ ሰው፣ ምግባሩ ከሰብዓዊነት ጎራ ያፈነግጣል፤ ሰብዓዊ ማንነቱ ይነጥፋል፡፡ ለራሱም ለሌሎችም በማይመች መልኩ ሰብዓዊ ክብርን ያዋርዳል፤ ለሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ይሆናል፡፡ ከዚህ አኳያ ነቢዩ ኢያሱም ይሄን ልቦለድ የሰብዓዊነት መንጠፍን ከተለያዩ ፈርጆችና ሁነቶች አኳያ ያቀረበበት ሲሆን፤ የማህበራዊና የግብረ ገብ እሴቶችን ዋቢ በማድረግ የሞራል ፍልስፍና ባህሪን ማሳየት አንዱ ትኩረቱ ነው፡፡

## 2.2. የሰብዓዊነት መንጠፍ

የሰው ልጅ ምንም እንኳ ማህበራዊ እንስሳነቱ የሚታመን ቢሆንም፤ አንደኛ በአካላዊ ቁመናው፤ ሁለተኛ በማሰብና ማገናዘብ ልዩ ተሰጦየው ከእንስሳት ይለያል፡፡ በዚህም ከሌሎች እንስሳት በተለየ መልኩ እርስ በእርሱ እንዲተሳሰብ፣ እንዲረዳዳና አንዱ ለአንዱ አለኝታ እንዲሆን አድርጎታል፡፡ በትናንት መነሻነት ዛሬውን የተሻለ ለማድረግ ይጥራል፤ ስለነገው የሚጨነቅና የተሻለች ዓለምን ለመፍጠር ልዩ የሆነውን የማስብና የማሰላሰል ተሰጦዖ ተጠቅሞ አዳዲስ ፈጠራዎችን ያወጣል፡፡ የማህበራዊነት ማጠንከሪያና መግሪያ የግብረ ገባብ እሴቶችን በመገንባትም ይመራባቸዋል፤ የሰብዓዊነት ኃላፊነቱን ለመወጣትም ይጠቀምባቸዋል፡፡

በአንጻሩ ግን ሰው ሆኖ እንደ ሰው ከማሰብና ከመመራት ይልቅ ሰብዕናውን ዘንግቶ ይታያል፡፡ የሰው ልጆች ታሪክም የሰው ልጆች መልካም ገጽታን ብቻ ሳይሆን ይሄንኑ ሰው ሆኖ ሰው ያለመሆን ውጤትን "ሰው መኮኑ ለምን ነው" እስኪያስብል ሰውነትን ጥያቄ ውስጥ አስገብተዋል፡፡ በዚህም ሰው ሰውን ጠልቶ፤ ሰው ሰውን ገፍቶ፤ ሰው ሰውን ረግሞና፤ ሰው ለሰው የሰውነት ክብር ነፍጎ አያሌ ዓመታትን አሳልፏል፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጆች ሰብዕና መውረድን፣ ሰብዓዊ ማንነቱም መንጠፉን ማሳያ ነው፡፡ Adrienne F. McFaul (2010), "Any behavior intended to deny full human status to another individual falls under the definition of dehumanization**."** (ገጽ፣.2)፣ሲል እንደበየነውም፤ ሰዎች በከፊልም ሆነ በሙሉ የሰውነት ክብራቸው መውረድን የሚገልጽ ነው፡፡ በመሆኑም የሰብዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ ግለሰቦችን ወይም የተወሰኑ ቡድኖችን ሙሉ ሰው እንዳልሆኑ/ከሰው በታች እንደሆኑ አድርጎ ማሰብንና በዚሁ ልክ መግለጽን ይመለከታል፡፡ "*Dehumanization beliefs* are the tendency to think of all or most other people as less than fully human." (ገጽ፣.2)፡፡

የአማርኛ ስነጽሑፍ ትኩረቱ ከሚያደርጋቸው ማህበራዊ ጉዳዮች መካከል ደግሞ ይህ የሰብዓዊነት መንጠፍ አንዱ ነው፡፡ የሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ ከተዋወቀ ከ19ኛው ክፍለ ዘመን አንስቶም የተለያዩ ባለሙያዎች ሥራዎች ላይ ጎልቶ እንደሚስተዋል Smith (2014) ይናገራል፡፡ ለሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ እንደየ ሙያ መስኩ የተለያየ ትርጉም እንደሚሰጠውም አመልክቷል፡፡ በዚህም የሰብዓዊነት

መንጠፍ ሌሎችን ዝቅ አድርጎ ማሰብ፣ ሰው ካልሆኑ እንስሳት ወይም ግዑዝ ነገሮች ጋር ማነጻጸርና በዚሁ ልክ መግለጽ፣ እነዚህንም በድርጊት ጭምር በማስደገፍ ሰብዕናን ከሰው በታች አድርጎ ማቅረብን የመሳሰሉ እሳቤና ምግባራትን የሚመለከት ነው፤ (ገጽ፣ 1-2)፡፡

በተመሳሳይ ሌሎችን ከሰው እኩል አድርጎ ያለማሰብ የሰብዓዊነት መንጠፍ በሶስት መሰረታዊ መመዘኛዎች ከፍሎ ያብራራዋል፡፡ አንደኛው፣ ለሰብዓዊነት መንጠፍ ተግባር ተጋላጭ የህብረተሰብ ክፍሎች አፈጣጠር (ከሰዋዊ አካላቸው) ጋር ያለውን ቁርኝት ወይም (the relation between the appearance of members of the dehumanized population and their real nature) ሲሆን፤ ሁለተኛው፣ የሰው ልጆችን ሰብዓዊ ባልሆኑ ቁሶች ወክሎ መግለጽ ወይም (a purported metaphysical fact that accounts for their non-human status) ነው፡፡ ሶስተኛው፣ ትኩረት የሰብዓዊነት መንጠፍ ተጠቂዎች የሚደርስባቸው የስነልቡናና ሞራል ስብራት ወይም (the demotion of the dehumanized population on the moral hierarchy)ን የሚመለከት ነው፡፡ እነዚህም በተለይ በባህልና ታሪክ ማዕቀፍ ውስጥ በስፋት የሚስተዋሉ መሆናቸውን ከአፍሪካውያን ቅኝ ግዛትና የባርነት ዘመን ጋር አያይዞ የነበረውን ገጽታ በማውሳት ያስረዳል፡፡

ዮናስ አድማሱ (1992)፣ "‹አስረኛንኩዋ?›፤ ሀዲስ ዓለማዬሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው" በሚል ርዕስ በ*ፍቅር እስከመቃብር* ላይ ባቀረቡት ሐቲት፣ የሰብዓዊነት መንጠፍን ከሰው ልጅ ሰብዓዊ ተግባር ያፈነገጠ መሆኑን ከመግለጽ ባለፈ፤ የዚህ ተጠቂዎች ችግሩን በራሳቸው ማስወገድ የማይችሉት ይልቁንም ከፈጣሪ የተሰጣቸው እድል ፈንታ አድርገው እንደሚያስቡት ነው የሚያብራሩት፡፡

> *…የሰብዓዊነት መንጠፍ በህሊና መጠቀም አለመቻልን፣ የግል ነጻ ፈቃድን አሳልፎ መስጠትን ያመለክታል፡፡ በሌላ በኩል፣ ሰዎች ሰውነታቸው ተረግጦ፣ ሰብዓዊ ማዕረጋቸው ተዋርዶና ተንቆ፣ ከእንስሳ፣ ከዕቃ ተራ ተመድበው የሚታዩበትን፣ እነሱም ይህን የማይገነዘቡበትን ሁኔታ ያመለክታል፡፡ ከሁሉ በላይ ግን የሰብዓዊነት መንጠፍ፣ ሰዎች ከሰዎች በታች ተደርገው የሚታዩበት ሁኔታ ከተፈጥሮ የተሰጠ አድርገው መቀበላቸውን ያመለክታል፤ (ገጽ፣ 108)፡፡*

Oliver (2011)፣ በበኩሉ የሰብዓዊነት መንጠፍ ከሰዎች አዎንታዊ አስተሳሰብና ሰብዕና በተቃራኒው ተጉዞ የሚከወን ተግባር መሆኑን የገለጸበት፤ "dehumanization defines, the concept in terms of a negation of such positive 'human' qualities as individuality, autonomy,

personality, civility, and dignity" (ገጽ፣ 85)፤ የሚለው ብያኔ ደግሞ የሰብዓዊነት መንጠፍን ምንነት ለማወቅ የተለያዩ አቅጣጫዎችን እንድናይ የሚያደርገን ነው፡፡ ምክንያቱም አንደኛ፣ ሰብዓዊነት ማለት ምንድን ነው? የሚለውን እንድንገነዘብ ሲያደርግ፤ ሁለተኛ ይሄን መነሻ በማድረግ ከሰብዓዊነት ያፈነገጡ ተግባራት ምንድን ናቸው? የሚለውን እንድንመረምር ያግዘናል፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍ ተከስቷል ስንል የተጣሰው ሰብዓዊነት ተግባር ወይም እሳቤ ምንድን ነው? ብለን በተጨባጭ እንድንፈትሽ እድል የሚሰጥ አገናዛቢ ብያኔ ነው፡፡

Oliver (2011)፣ Kelman (1973)ን ጠቅሶ እንዳብራራው፣ ሰብዓዊነት ማለት የአንድ ማህበረሰብ አባላት የእርስ በእርስ መተሳሰብንና መረዳዳትን በጥቅሉ የእርስ በእርስ መደጋገፍና መከባበርን የሚያመለክት በጎነት ነው፡፡ ከዚህ በተቃራኒ መልኩ የሚስተዋል እሳቤና ምግባር ግን ከሰብዓዊነት ያፈነገጠ የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ነው፡፡ ይህ አሉታዊ የሰብዓዊነት ተግባር ደግሞ ከማህበረሰብ አባልነት ማዕቀፍ እስከ መገለል የሚያደርስ አሉታዊ ተጽዕኖን ያስከትላል፡፡ "community imagines humanity as 'an interconnected network of individuals who care for each other, who recognize each other's individuality and who respect each other's rights'. To be dehumanized is to be excluded from this community; (ገጽ፣ 87)፡፡

ይሁን እንጂ፣ በዚህ መልኩ በማህበረሰቡ የሚገለለው ግለሰብ ወይም ቡድን ተመልሶ በአግላዩ ማህበረሰብ ላይ ኢ-ሰብዓዊ[5] የሆነ ተግባርን እንዲፈጽም ይገደዳል፤ ወይም ያላንዳች ግብረገባዊ ስሜት ሌሎች በእነርሱ ላይ የከፋ ጉዳት እንዲያደርሱባቸው ይፈቅዳል፡፡ ሰዎችን በከፊልም ሆነ በሙሉ ከሰብዓዊ ክብራቸው ዝቅ ማድረግ መገለልን ወይም ከማህበራዊ ማዕቀፍ ውጭ መሆንን እንደሚያስከትልም የስነ ልቡና አጥኚዎች ይናገራሉ፡፡

Deutsch (2000)፣ በበኩሉ እንደሚገልጸው፤ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ የሚከሰቱ በርካታ ማህበራዊና ስነልቡናዊ ሁነቶች የተለያዩ አመለካከቶችን ባገናዘበ መልኩ አካተው ላይገኙ ይችላሉ፡፡ ይህ ደግሞ ለተወሰኑ ግለሰቦች ወይም ቡድኖች እንዲገለሉ፣

[5] ይህ ሰዎች ሰብዓዊ ተፈጥሯቸው እንዲያደርጉ የሚያስገድዳቸውን ሳይሆን በተቃራኒው በሰዎች ላይ ጭካኔ የተመላበት አካላዊም ሆነ ስለ ልቡናዊ ጉዳት የሚያደርስ ተግባር የመፈጸም ሂደትን የሚመለከት ነው፡፡

የማህበራዊና ስነልቡናዊ ጫና እንዲፈጠርባቸው ያደርጋል፡፡ የኢኮኖሚ ችግር እና የፖለቲካ አለመግባባትንም ያስከትላል፡፡ Luna (2015)፣ በሰጠችው ማብራሪያም፣ የሰብዓዊነት መንጠፍ በሃሳብ፣ በስሜትና እነዚህን በመተግበር ረገድ የሚገለጽ ነው፡፡ ይሄንንም፣ “Dehumanization is thus presented in ways of thinking, feeling, and acting” (ገጽ፣ 18)፣ ስትል ገልጻዋለች፡፡

የሰብዓዊነት መንጠፍ ሂደትና ተግባር በተለያየ መልኩ የሚፈጥራቸው ስሜቶች አሉ፡፡ እነዚህ የፍርሃት፣ የበቀል፣ የበላይነትና የበታችነትን የመሳሰሉት በሰው ልጆች የባህልና የሞራል ፍልስፍና ሚዛን ሲታዩ ሰዎችን ከሰውነት በታች ለማድረግ ወይም ራስን ከሰውነት በላይ የመግለጽ አዝማሚያም ነው፡፡ Haslam (2006)፣ ስለ ሰብዓዊነት መንጠፍ በሚመለከት Bar-Tal (2000)ን ጠቅሶ እንደገለጸው፤ “…involving “labeling a group as inhuman, either by reference to subhuman categories … or by referring to negatively valued superhuman creatures such as demons, monsters, and satans”; (Haslam, 2006, ገጽ፣ 254) ፡፡

በዚህ መልኩ የሚገለጽ ራስን ዝቅ አድርጎ ወይም በአሉታዊ መንገድ ከፍ አድርጎ የመመልከት የሰብዓዊነት መንጠፍን በተለያየ መልኩ መረዳት ይቻላል፡፡ እንደ Haslam (2006)፣ የሰብዓዊነት መንጠፍን ለመረዳት የሰብዓዊነት መገለጫዎችን መገንዘብ ይገባል፡፡ ሰብዓዊነትም የሚገለጽባቸው ሁለት መሰረታዊ የሰብዕና ስሜቶች (Senses of Humanness) አሉ፡፡ እነርሱም የሰው ልጅ ከእንስሳት ራሱን የሚለይበት ሰዋዊ ባህሪው (Human Uniqueness)፤ እንዲሁም ከዚህ ሰዋዊ ባህሪው የመነጨ ልዩ የሚያደርጉት አስተሳሰብና ምግባሩ (Human Nature) ናቸው፡፡ “ዩኒክሊ ሂዩማን” የሚባለው የሰው ልጅ ባህሪ የሰው ልጅን ከሌሎች እንስሳት ልዩ የሚያደርገው ተፈጥሯዊ ድንበር፣ ወይም (Uniquely human characteristics define the boundary that separates humans from the related category of animals) መሆኑን ያስረዳል፡፡ በአንጻሩ “ሂዩማን ኔቸር” የሰው ልጅ መሰረታዊ የሰውነት መገለጫዎች መሆናቸውን፣ (humanness may also be understood noncomparatively as the features that are typical of or central to humans. These normative or fundamental characteristics might be referred to as human nature) (ገጽ፣ 256) ሲል ይገልጸዋል፡፡ የእነዚህ ሁለት ሰዋዊ መገለጫዎች መሸርሸር ደግሞ “UH and HN are distinct senses of humanness, and that different forms of

dehumanization occur when the characteristics that constitute each sense are denied to people." (Halsam 2006፣ ገጽ፣. 256)፣ ሲል እንደገለጸው፤ ለሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰት ምክንያት እንደመሆኑ፤ የሰብዓዊነት መንጠፍን ለመመልከትም የእነዚህን መጣስ ወይም የእነዚህ ሰዋዊ መገለጫዎች ከሰው ልጆች ስሜትና ምግባር መራቅን በትኩረት መመርመር ተገቢ ይሆናል፡፡

Haslam ከዚህ ጋር አያይዞ እንዳብራራው፣ ሁለት የሰብዓዊነት መገለጫዎች እንደመኖራቸው እነዚህኑ መሰረት ያደረጉ ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻዎች አሉ፡፡ "If there are two distinct senses of humanness, then two distinct forms of dehumanization should occur when the respective properties are denied to others." (ገጽ፣ 257)፡፡ እነዚህም አንደኛው የሰው ልጅ ሰብዓዊነትን ወደ እንስሳዊ ጎራ የመቀላቀል ገጽታው (Animalistic dehumanization) ነው፡፡ ሁለተኛ ደግሞ የሰው ልጅ ሰዋዊ ተግባር ከሰው እጅ ወጥቶ ለሰው ልጅ ውጤት ለሆነው ቁሳዊ ነገር የመገዛትና በዚሁ ልክ መመልከትን፣ እንዲሁም የሰው ልጅን በዚሁ ተክቶ የመግለጽ አዝማሚያ (Mechanistic dehumanization) ነው፡፡ እነዚህን ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻውችም የየራሳቸው ባህሪ ያላቸው ሲሆን፤ የዘርፉ ባለሙያዎችም በሚከተለው መልኩ አስፍረዋቸዋል፡፡

## 2.2.1."አኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" እና "ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዝሽን"

ለበርካታ የዘርፉ ምሁራን መሰረት ሆነው እያገለገሉ ያሉ እነዚህን ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻዎች የHalsam ሲሆኑ፤ በ2006 ስራው ላይ በሰጠው ብያኔ መሰረትም፤

> *Animalistic dehumanization involves the denial of UH attributes, typically to essentialized outgroups in the context of a communal representation of the ingroup. …Mechanistic dehumanization, in contrast, involves the objectifying denial of essentially human attributes to people toward whom the person feels psychologically distant and socially unrelated. (p.262).*

ከዚህ መረዳት እንደሚቻለውም፣ የሰብዓዊነት መንጠፍ የሚከሰትባቸው "የአኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" እና "ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" ፈርጆች ሲሆኑ፤ ሁለቱም በየፊናቸው ይሄንኑ የሰውነት ዝቅጠት ደረጃ ለማሳየት የሚውሉ ናቸው፡፡ በዚህ

መሰረት "አኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" ሰዎች ሰውነታቸውን ትተው እንስሳዊ ባህሪን መላበስን እንዲሁም በዚሁ ልክ መወከልን የሚገልጽ ነው፡፡ የሰውን ልጅ የሀሳብና ምግባር ውጤቶች ስብዕናውን የሚገልጹና የሚወክሉ ሳይሆኑ ሲቀሩ የሚከሰት እንደመሆኑ፤ ሰዎችን፣ በባህሪያቸው በማስተዋል ሳይሆን በደመነፍስ በሚንቀሳቀሱ እንስሳት እንዲወከሉ ያደርጋቸዋል፡፡ በሌላ በኩል የ"ሜካኒስቲክስ ዲሂዩማናይዜሽን" ፈርጅ፣ የሰው ልጅን ሰውነት ከቁስ ተራ ማስገባት፣ በዚሁ ልክ መግለጽና ማየትን የሚጨምር ነው፡፡ በዚህ ፈርጅ የሚገለጸው የሰብዓዊነት መንጠፍ፣ ሰው ሰውነቱ ተዋርዶ ለራሱ የስራ ውጤት ለሆነው ቁስ ሲገዛ፤ በዚሁ ልክ ሲመዘንና ራሱንም በዚሁ መንገድ የሚያቀርብበት ነው፡፡

Martínez እና ሌሎችም (2012)፣ Haslam (2006)ን ጠቅሶ እንዳሰፈረው፤ የሰብአዊነት መንጠፍ በእነዚህ ሁለት መንገዶች የሚገለጽ ቢሆንም ከሚያሳድረው ተጽዕኖ አኳያ እንደየ አከባቢውና ግለሰቡ ወይም ቡድኑ ነባራዊ ሁኔታ ሊለያይ ይችላል፡፡ ሆኖም በእነዚህ ሁለት መንገዶችም ሰዎች በሰዎች ላይ ኢ-ሞራላዊ የሆነ ጥቃታቸውን ሲያደርሱ ይስተዋላል፡፡ "Some groups are subjected to animalistic dehumanization while others are subjected to mechanistic dehumanization. According to Haslam, animalistic and mechanistic dehumanization are the two ways in which people dehumanize members of groups they do not belong to" (ገጽ. 1119) ፡፡

እነዚህ ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ፈርጆች በግለሰቦች ወይም የማህበረሰብ ቡድኖች መካከል የሚስተዋሉ ናቸው፡፡ እነዚህም በአንድ በኩል ሰዎች ሰዎችን ልክ እንደ እንስሳ የሚገልጹበት የአኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዝሽን ፈርጅ አስተሳሰብና ምግባርን መሰረት አድርጎ የሰውነትን ማዕረግ ከእንስሳዊ ባህሪይ ጋር የማኖር ነው፡፡ በሌላ በኩል ደግሞ ሰዎች ለራሳቸው ወይም ሌሎች ሰዎች ለሌሎች ሰዎች የሚሰጡት የሰውነት ክብር ከቁስ ተራ የሚደባለቅበት የሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን ፈርጅ ነው፡፡ Moller እና Deci (2010)፣ Haslam (2006)ን መነሻ አድርገው እነዚህን ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ መገለጫዎችን፣ "Animalistic dehumanization involves denying uniquely human attributes to others, representing them as animal-like, whereas mechanistic dehumanization involves denying human nature to others, representing them as objects or automate" (ገጽ፣ 44), ሲሉ በይነዋል፡፡ ይሁን እንጂ እነዚህ ሁለት የሰብዓዊነት መንጠፍ

መከሰቻዎች የሰው ልጆችን ሰብዓዊነት ከመፈተን አኳያ የሚጋሯቸው የጋራ ባህሪ አላቸው፡፡ ይህ ሂደትም በግብረገብ መለኪያ ሰዎችን ከሰው በታች አድርጎ ከመፈረጅ እንደ ቁስ እስከመመልከት፣ በእንስሳት ባህሪም እስከመግለጽ የሚደርስ አካላዊም ሆነ ስነ ልቡናዊ ጫና የሚፈጥር ተግባር ነው፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍ ሰፋ ባለ መልኩ ሲገለጽ፣ የሌሎችን ሰብዕና መዘንጋት ወይም ማዋረድን የሚመለከት ነው፡፡ "Dehumanization is a psychological construct which has been very broadly defined as the denial of humanness to others"; (ገጽ፣ 44)፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍ ሰብዓዊ ማንነት በማሳጣት ግላዊ ስሜትና ፍላጎትን እስከመንፈግ የሚገለጽ የሕሊና ነጻነትን የሚጋፋ ተግባር ነው፡፡ Moller እና Deci እንዳረጋገጡትም፣ የሰብዓዊነት መንጠፍ በግለሰቦች ወይም በቡድኖች መካከል በሚኖር መስተጋብር የሚከሰተውን የተወሳሰበ ጥቃት ወይም ጭቆና የሚከስቱ ሁነቶችና ግንኙነትን ለመመልከት እድል ይፈጥራል፡፡

እንደ Vaeset እና ሌሎችም (2012)፣ በርካታ የታሪክ ሁነቶች በግለሰሰቦች ግንኙነት፣ በቡድን ወይም ከቡድን ውጪ በሚኖር መስተጋብር የተለያዩ አይነት የሰብዓዊነት መንጠፍን የሚያመላክቱ ሁኔታዎች ይከሰታሉ፡፡ ይሄም በዋናነት በሚፈጠሩ መስተጋብሮች መካከል በሚስተዋል ሌሎችን እንደ ሙሉ ሰው አለመቁጠርና ከሰው በታች አድርጎ የመመልከት፤ በዘይቤዎች የእነስሳትን ባህሪ የመስጠት፤ አጋጣሚ ሲኖር የተለያዩ ማህበራዊ ጎራዎች እንዲፈጠሩ ያደርጋል፡፡ "Dehumanisation has mostly been related to extreme reactions of aggression and hatred and seen as a destructive process in violent conflict situations" (ገጽ፣ 66)፡፡ በተመሳሳይ Manninen (2018)፣ "When we dehumanize others, when we stigmatize them as either lacking in agency or individuality, or as not belonging to our moral community, we are less likely to develop feelings of empathy or care for them." (ገጽ፣ 3)፣ ሲል ገልጾታል፡፡ ከዚህ የምንረዳውም የሰብዓዊነት መንጠፍ ሲከሰት የግብረ ገብ እሴቶች ይዘነጋሉ፡፡ ሰዎችም ለሰዎች የሚሰጡትን የክብር ቦታ ይነፍጋሉ፡፡ እነዚህ ግብረገባዊ እሴቶች ሲዘነጉ፣ እንደየ ሀሳብና ፈቃዳቸው መጓዝም ይጀምራሉ፡፡

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሆነው ደግሞ የሰው ልጆች ሰብዓዊ ማንነታቸውን ከየት እንደሚያገኙት ቢጠየቁ ሁሉም የተለያዩ መልሶችና ምክንያቶች ሊሰጡ ይችላሉ፡፡ ለምሳሌ፣ ከእንስሳት ልዩ ሆነው በመፈጠራቸው ያገኙት እንደሆነ ሊገልጹ፤ አልያም

ራሳቸውን ከሌሎች ሰዎች ጋር እያነጻጸሩ ወይም መልካም ብለው ከሚያምኑባቸው ከራሳቸው እሳቤና ተግባራት እንዲሁም ከማህበረሰቡ ባገኟቸው የሞራል እሴቶች አኳያ ሊያስረዱ ይችላሉ፡፡ እነዚህ ሁለት ጉዳዮችን እንኳን ብንመለከት አንድም ከሰዎች ተፈጥሯዊ ማንነት ጋር የተቆራኙ ሲሆን፤ በሌላ መልኩ በዚህ የተለየ የሰው ተፈጥሮ ምክንያት ሰዎች የሚከውኗቸው ሰብዓዊ ተግባራትን (የሞራል/የግብረገበነት ጥያቄን ይይዛል) መሰረት ያደረጉ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍ፣ ከተፈጥሯዊ ማንነት ጋር በተያያዘ፤ ወይም ከሰብዓዊና ግብረገባዊ ምግባራት ጋር የተቆራኘ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡

የሰብዓዊነት መንጠፍና የግብረ ገብ እሴቶች ቁርኝትን አስመልክታ Luna, (2015)፣ የዘርፉ ጥናቶችን ዋቢ በማድረግ እንደምታብራራው፤ የሰብዓዊነት መንጠፍ የሚለካው በአንድ ማህበረሰብ አባላት ውስጥ ባለ የሞራል ፍልስፍና አተያይ አንጻር ነው፡፡ በዚህም የማህበረሰቡ አባላት በአብዛኛው የተስማሙባቸው የሞራል ፍልስፍናና የምግባር መመሪያዎች የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰት አለመከሰትን ለመፈተሽ ያስችላሉ፡፡ እንደ Luna 2015 ገለጻ፤

> *Dehumanization undermines ways of viewing that have moral implications; …These moral implications determine what is good and bad, acceptable and non-acceptable towards an in-group versus an out-group. By framing others as something other than human, the dehumanize challenges their sense of individuality, identity and community, enables their moral exclusion and group discrimination, and psychologically conditions the abuser to morally disengage from this "non-human" in order to justify violence and abuse; (p.19).*

የሞራል ፍልስፍናዎች በዚህ መልኩ ሲዘነጉ፤ ማህበራዊ እሴቶችም ሲጣሱ ሰዎች ለሰዎች መድረስን፣ መረዳዳትና መከባበርን የመሳሰሉ ሰብዓዊና ግብረገባዊ ተግባራትን ሲዘነጉ ሰብዓዊነታቸው እየነጠፈ፣ ራስ ወዳድነታቸው እየገዘፈና ለሰዎች (በራሳቸው ማህበራዊ ጉድኝት ውስጥ ወይም ውጭ ያሉ ሊሆኑ ይችላሉ) የሚኖራቸው ርህራሄ ይጠፋል፡፡ ራስ ወዳድነት ሲበዛ ለሰዎች መድረስ እየተዘነጋ ይሄዳል፤ ለራስ የሚሰጥ ግምት ሲገዝፍ ለሰዎች ክብር መንሳት ይወለዳል፤ ፍቅር ሲቀዘቅዝ ጥላቻ ይጠነሰሳል፤ ቂም በቀል ግዘፍ ይነሳል፡፡ ኢ-ሰብዓዊ ድርጊቶች ፍሬ ሲያፈሩም የሰብዓዊነት መንጠፍን ይወልዳሉ፤ የሰብዓዊነት መንጠፍ ሲደረጅም የሰብዓዊ መገለጫዎች ይከስማሉ፤ ጥላቻዎችም ወደ ቂም በቀልና ግጭት ያመራሉ፡፡ ይሄንንም እነ Vaeset

(2012)፣ "Denying humanity to others serves to morally disengage from self-sanctions by justifying the harm one's group has caused to another"; (ገጽ፣ 86)፣ ሲሉ ገልጸውታል፡፡

እነ Park, (2015)፣ በሬናቸው የተለያዩ ስራዎችን መነሻ አድርገው እንዳብራሩት፤ የሰብዓዊነት መንጠፍ ቀውስ ከውስጣዊ ስሜት ጫና እስከ ማህበራዊ ግንኙነት መሻከር የሚዳርግ ነው፡፡ ይሁን እንጂ ይህ ተግባር ዘላለማዊና መፍትሄ የሌለው ሳይሆን ሰብዓዊ አዕምሮን በማሰራት፣ ሰዎችን እንደ ሰው ቆጥሮ ፍቅር በመስጠትና በመደገፍ፤ የሰብዓዊነት መገንቢያ የሆኑ ግብረገብ ባህሪን ማበልጸጊያ የሞራል እሴቶችን በማጎልበት ሊስተካከሉ፤ ሰብዓዊ ማንነትም ሊገነባ እንደሚችል ነው፡፡ ምክንያቱም የሰብዓዊነት መንጠፍ ሲነሳ የሞራል ፍልስፍና ወይም የግብረ ገብ እሴቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት እና የሰብዓዊነት መንጠፍ ትይዩነት የሚለካው ከሰዎች የሞራል ፍልስፍና አንጻር መመልከት ሲቻል ነው፡፡ ግብረ ገብነት ሲታሰብ ደግሞ የግብረገብነት መሰረት የሆኑ ውስጣዊና ውጫዊ ምክንያቶች አብረው ይነሳሉ፡፡ በመሆኑም የሰብዓዊነት መንጠፍን ስንፈትሽ ከእነዚህ መሰረታዊ ጉዳዮች (ከግብረገብነት እና ከግብረገብነት ምንጮች) አንጻር መፈተሽ ተገቢ ሲሆን፤ ከእነዚህ የሚነጠቁ ጉዳዮችም የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰትን በአግባቡ ለመፈተሽ አጋዥ ይሆናሉ፡፡

## 2.3. የተዛማጅ ጽሑፍ ክለሳ

ከእኔ ጥናት ርዕሰ ጉዳይ፣ ዓላማና የትኩረት አቅጣጫ ጋር ተዛማጅነት ያላቸውን (በቀጥታ ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ሊገናኙ የሚችሉትንም ይጨምራል) የመጀመሪያ ዲግሪ፣ የሁለተኛ ዲግሪ እና የዶክተሬት ዲግሪ የመመረቂያ ጽሑፎችን እንዲሁም የጥናት መጽሔቶችን በዩኒቨርሲቲው ባሉ ቤተ መጻሕፍት አስሻለሁ፡፡ ከዩኒቨርሲቲው ቤተ መጻሕፍት ውጪ ካሉ ለመመልከትም የተለያዩ ድረ-ገጾችን ጎብኝቻለሁ፡፡ ይሁን እንጂ በእኔ ጥናት ጉዳይ ዙሪያ የተከናወኑ ጥናቶችን በብዛት ማግኘት ባለመቻሌ፤ ከእኔ ጥናት ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ መንገድ ግንኙነት አላቸው ብዬ ያመንኩባቸውን አራት ሥራዎች መርጫለሁ፡፡

ለተዛማጅ ጽሑፎች ቅኝትነት ከመረጥኳቸው ሥራዎች መካከል ከእኔ ስራ ጋር የቀረበ ግንኙነት አለው ብዬ ቀዳሚውን ስፍራ የሰጠሁት፣ የዮናስ አድማሱ፣ "‹‹አስረኛንኳ?›› ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ሥልታቸው" ሲሆን፤ የሥነሕይወት ገዛኸኝ፣ "ባይተዋርነት በሰባተኛው መልአክ፡ በትኩሳትና በሌቱም አይነጋልኝ ውስጥ" በሚል ርዕስ የተከናወነው የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናት የሰብዓዊነት መንጠፍን እንደ አንድ ንዑስ ጉዳይነት በማንሳቱ ከሌሎቹ የተሻለ ቀረቤታ ያለው መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከዚህ ባለፈ የአያሌው አሰፋ "ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብዓዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ-ወለዶች ውስጥ"፤ እና የአሻግሬ አምጤ፣ "ባይተዋርነት በመቅደስ ጀምበሩ ግጥሞች" በሚል ርዕስ የተካሄዱት የሁለተኛ ዲግሪ ማሟያ ጥናቶች በተዘዋዋሪም ቢሆን ከእኔ ጥናት ጋር ይገናኛሉ በማለት ተመልክቻቸዋለሁ፡፡ ይሁን እንጂ ከእኔ ጥናት ጋር ተያያዥነት ያላቸው ጥናቶችን ለማግኘት ባደረኩት ጥረት ለመጀመሪያ ዲግሪ ማሟያነትም ሆነ ለሶስተኛ ዲግሪ ማሟያ (ዲሰርቴሽን) የተከናወኑ ጥናቶችን ማግኘት ስላልቻልኩ በዚህ ስር የምቃኛቸው ዲማጾችም ሆኑ ዲሰርቴሽኖች አይኖሩም፡፡

በመጀመሪያ የተመለከትኩት የዮናስ አድማሱን፣ "‹‹አስረኛንኳ?›› ሀዲስ አለማየሁና የማህበራዊ ሂስ ሥልታቸው"፣ በ1992 በኢትዮጵያ የቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ መጽሔት ቁጥር 10 ላይ የወጣ ሐቲት ሲሆን፤ ጥናቱ አንድን ጽሑፍ ለመሄስ ከፊት ለፊት ሆነው እያባበሉ ይዘውን ከሚነጉዱ ትላልቅ ጉዳዮች ይልቅ ሰፊ ቦታ የተሰጣቸው ለማይመስሉ ጥቃቅን ሁነቶች ትኩረት መስጠት እንደሚገባ የሚያስገነዝብ ነው፡፡ ከንድፈ ሀሳቡም፣ ከቴክስቱም ሰፊ ትንታኔ የተሰጠበት፤ ትዕምርቶችንም የተፈከረበትና ጥቃቅን ሁነቶችና ሁኔታዎች የልቦለዱ አብይ ጭብጥ መሆን እንደሚችሉ ያታየበት ነው፡፡

ጥናቱ አጭር መግቢያ፣ ፍካሬ እና እንደ ማጠቃለያ በሚሉ ሶስት አብይ ክፍሎች የተደራጀ ሲሆን፤ አጭር መግቢያ ብሎ ባደራጀው ክፍል ውስጥ የጥናቱን ዓላማና ግብ ከማስተዋወቅ፣ የጥናት ዘዴውን ከማብራራትና የንድፈ ሀሳብና ጽንሰ ሀሳብ ገለጻ እስከማድረግ፤ እነዚህንም ከቴክስቱ ቀንጨብ አድርጎ በሚያመጣቸው ጠቋሚ ማስረጃዎች እያበለጸገ ያመለከተበት ነው፡፡ ፍካሬ በሚል ያደራጀው ክፍልም በአራት አሃዶች የተዋቀረ ሲሆን፤ በአሃድ አንድ እና ሁለት ሥር በተለይ የውድነሽ በጣሙ እና የቄስ ታምሩ የትዳር ምልጃ ሂደት መነሻ በማድረግ የሚስተዋሉ ማህበራዊ ብቻ

ሳይሆን ኃይማኖታዊ የእውቀት ክፍተት ከቴክስቱ የተለያዩ ሁነቶች ጋር በማገናዘብ ያሳየበት ሂስ ነው፡፡

በሦስተኛው አሃድ የሰብለ ወንጌልን ነጻነት ናፋቂነት መነሻ አድርጎ የባህልና ወግ ባርነት በወጉ የሂሱበት ክፍል ሲሆን፤ በአራተኛው አሃድ የዕዝራን ፈረጀነት አምኖ መቀበል ከሰብዓዊነት መንጠፍ ጋር አቆራኝተው የሰብዓዊነት መንጠፍን በወጉ ያመለከቱበት ነው፡፡ እንደ ማጠቃለያ በሚለው ክፍልም ሥነ ጽሑፍ እንደምን ባህልን እንደሚተች ያሳዩበት ሲሆን፤ በልቦለዱ ውስጥ ያለው የጉድ ማህበር መሆኑን በመግለጽ፤ የማህበራዊ ሂሳቸውን ከሰብዓዊነት መንጠፍ አኳያ በማገናዘብ ትንታኔያዊ ማጠቃለያ የሰጡበት ነው፡፡ ይህ ጥናት በቀጥታም ባይሆን በሚያነሳው የማህበራዊ ሂስ አንጻር ከእኔ ስራ ጋር የመቀራረብ እድል ያለው ነው፡፡ ይሁን እንጂ ከቴክስት፣ ከጉዳይም ሆነ ከዘዴ አኳያ የተለያዩ በመሆናቸው ከእኔ ጥናት ጋር አንድ ናቸው ተብሎ የሚወሰድ አይደለም፡፡ ይልቁንም ሁለቱም በየፊናቸው መታየት የሚችሉ ናቸው እንጂ፡፡

በሁለተኝነት የተመለከትኩት ሥነሕይወት ገዛኸኝ፣ "ባይተዋርነት በ*ሰባተኛው መልዓክ፣ ትኩሳት* እና *ሌቱም አይነጋልኝ* ውስጥ"፣ በሚል ርዕስ በ2007 ዓ.ም ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ያቀረበችው ቴሲስ ነው፡፡ የዚህ ጥናት መሰረታዊ ዓላማ በተመረጡት ልቦለዶች ውስጥ የተስተማሰሉ ሰብዓዊ ጉዳዮችን በሐቲት በማቅረብ ቴክስቱን በመተንተንና በመተርጎም ማሳየት ነው፡፡ ለጥናቱ ማስኬጃነት የተመረጠው የባህል ጥናት ሲሆን፤ የባህል ጥናት ንድፈ ሀሳብ ከተለያዩ ምሑራን እይታ አንጻር ተቃኝቷል፡፡ ከዚህ ባለፈም ባይተዋርነት፣ የሥነምግባር ሞት፣ ፍርቅነት የሚሉ ጽንሰ ሀሳቦች ራሳቸውን ችለው የተብራሩ ሲሆን፤ የባይተዋርነት መከሰቻዎች በሚልም ለሥልጣን ባይተዋር መሆን፣ ወለፈንዲነት፣ ማህበራዊ ባይተዋርነት (ለሕግና ለደንብ ባይተዋር መሆን) እና ለራስ እንግዳ መሆን የሚሉ ንዑሳን ጉዳዮች ተብራርተዋል፡፡ በእነዚሁ ጉዳዮች ላይ ተመስርታም ከቴክስቶቹ በማጣቀስ በይነ ዲስፕሊናዊ ትንተና አድርጋለች፡፡

በጥናቱ የትንተና ክፍል በሁለተኛው ምዕራፍ ያቀረበቻቸውን ንድፈ ሃሳባዊና ጽንሰ ሃሳባዊ ዳራዎች ከልቦለዶቹ በማሳያነት በምታቀርባቸው ታሪኮች በመታገዝ ትዕምትሮችን ተንትናለች፡፡ በዚህም የባይተዋርነት መከሰቻ ያለቻቸውን ንኡሳን

ጉዳዮች በተናጥል በየልቦለዶቹ ውስጥ ተመልክታለች፡፡ የመረጠቻቸው ሶስቱም ልቦለዶች የባይተዋርነት መከሰቻ መሆናቸውን በማሳየት፤ ቴክስቶቹን በተናጥል ብቻ ሳይሆን ድንበር እያፋረሰች በጋራ በበመልከትም ሁነትና ሁኔታዎችን ተንትናለች፤ ትርጓሜም ሰጥታለች፡፡

ይህ ጥናት ከላይ ሲታይ ምንም እንኳን ቀጥተኛ የሆነ የርዕሰ ጉዳይ ግንኙነት ያለው ባይመስልም፤ በአግባቡ ሲፈትሹት በተለይ የሥነ ምግባራዊ ሞት እና የሰብዓዊነት መንጠፍ በሚሉ ንዑስ ርዕሶች ስር የቀረቡ ጉዳዮች ከእኔ ጥናት ጋር የተገናኙ ናቸው፡፡ ከዚህ ባለፈም ማህበራዊ ባይተዋርነት የሚለውም ለሰብዓዊነት መንጠፍ እንደ አንድ መንደርደሪያ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ፡፡ ከዚህ አኳያ ሲታይ የጥናቱ የተወሰነው ክፍል ከእኔ ጥናት ጋር የሀሳብ ግንኙነት ይኖረዋል፡፡ ሆኖም ጥናቶቹ ከያዙት ዓላማ እና ሊያስተላልፉ ከፈለጉት መልዕክት አኳያ የተለያየ አቅጣጫን የተከተሉ ናቸው፡፡ በጥናት ዘዴያቸውና በቴክስት ምርጫቸውም እንዲሁ የተለያዩ ናቸው፡፡ ይህ ደግሞ ጥናቱ ከእኔ ጥናት ጋር በተወሰነ መልኩ ይገናኝ እንጂ አንድ አለመሆኑን የሚያሳይ ነው፡፡

በሦስተኛነት የዳሰስኩት ጥናት ደግሞ አያሌው አሰፋ "ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብዓዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ-ወለዶች ውስጥ" በሚል ርዕስ በ1999 ዓ.ም ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያቀረበው ጽሑፍ ሲሆን፤ ጥናቱ በነጋሽ ገብረማርያም- *ሴተኛ አዳሪ*፣ በስበሃት ገብረእግዚአብሔር- *ሌቱም አይነጋልኝ* እና በተድባበ ጥላሁን- *መንልየ መንልይ ዘካዛንችስ* በተሰኙ ሶስት ልቦለድ ስራዎች መነሻነት የሴተኛ አዳሪዎችን የሰብዓዊ መንጠፍ ሁነትና ሁኔታ መተንተን ዓላማ ያደረገ ነው፡፡ ለዚህም ጠቋሚ ቃሎችን፣ ሀረጎችና ዐረፍተ ነገሮችንን ፈክሯል፤ የሴተኛ አዳሪን የሥነ ልቡና እንዲሁም የማህበራዊ አመለካከት መድሎና መገለል ያስከተለባቸውን የመንፈስ ስብራት፣ ያስከተለባቸውን የባይተዋርነት ስሜት፣ ከባህልና ልማዱ አመለካከት አንጻር፣ ከጽሁፎቹ እየወሰደ በአንድምታ ተርጉሟቸዋል፡፡

ጥናቱ በክለሳ ድርሳኑ ሰፊ ትኩረት የሰጠው ለሰብዓዊነት መንጠፍ ሳይሆን ከሴተኛ አዳሪነት ጋር ለተያያዙ ጉዳዮች ነው፡፡ በዚህም የሴተኛ አዳሪነት ምንነትን እና የሴተኛ አዳሪነት ታሪካዊ ዳራን ነው በስፋት ያብራራው፡፡ በተዛማጅ ጽሑፎች ክለሳውም ቢሆን በተለይ የሪቻርድ ፓንክረስትን ጽሑፍ የዳሰሰው ሴተኛ አዳሪነት

በኢትዮጵያ ያለውን ዳራ በማሳየት ላይ ነበር፡፡ በሌሎች ጥናቶች ዳሰሳውም ሴተኛ አዳሪነትን ማህበራዊና ኢኮኖሚያዊ ሁኔታውን በማመላከት ላይ ያተኮረ ነው፡፡ በመሆኑም ጥናቱ በክለሳ ድርሳኑም ሆነ በትንተናው (ርእስ ሰጥቶ ወደ ትንተናው ከመግባት ባለፈ) ስለ ሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ ለማስተዋወቅም ሆነ የጥናቱ ማጠናከሪያ እንዲሆነው ለማድረግ ያነሳው ሀሳብ የለም፡፡

ይሁን እንጂ የአጥኚው ዐብይ መንደርደሪያ ድርሰቶቹ በሰበካው ከሚነግሩት ወይም ከሚነበቡት ውጪና ጀርባ ያልበሰሉ በሚመስሉ ጥሬ ቃላት አማካኝነት የታጀቡ በምጸት የታመቁ የነገረ ሰብ ጣጣዎች እናገኛለን የሚል መሆኑን አስፍሯል፡፡ ጥናቱ ፍካሬውን መሰረት ያደረገው አንድም ከማህበረ ባህላዊ እና ከስነልቡናዊ ምክንያቶች አንጻር ሲሆን፤ በዚህም የማህበራዊ ለውጥና ከባህሉ የመነጨ የወንዶች ግብዝነት ለሴተኛ አዳሪዋ የሰብዓዊነት መንጠፍ ውስጥ መውደቅ ምክንያት መሆናቸውን በትንታኔው አሳይቷል፡፡ ሁለተኛም፣ ስነ ልቡናዊ ተጽዕኖው ላይ ያተኮረ ሲሆን፤ ይህ የስነ ልቡናዊ ሁኔታም ከቴክስቶቹ ጋር ተገናዝቦ ተተንትኗል፡፡ በዚህም በሶስቱም ልቦለዶች ያለው የሴተኛ አዳሪነትና የሰብዓዊነት ጥያቄ፣ ሴተኛ አዳሪዋን/ነትን እንጥፍጣፊ የሌለው የሰብዓዊነት ድርቀትን የሚያላብስ መሆኑ ታይቷል፡፡ በጥቅሉ ሶስቱም ልቦለዶች የሴተኛ አዳሪነትን የሰብዓዊነት መንጠፍ ሁነት በሚያሳዩ ሥነልቡናዊ ስብራትን በሚፈጥሩ ኢ-ሞራላዊ ትዕይንቶች የተሞሉባቸው ናቸው፡፡ ይሁን እንጂ በጥናቱ እንደተመላከተውም ትንታኔ ሲደረግ ሶስቱንም ልቦለዶች በተናጠል ሲሆን፤ በዚህም የሴተኛ አዳሪነት የሰብዓዊነት መንጠፍ መጠንና ልክ እንደየ ልቦለዶቹ ለየቅል መሆኑን መረዳት ተችሏል፡፡

ይህ ጥናት ምንም እንኳን በሴተኛ አዳሪነት ላይ ያተኮረ ቢሆንም ጉዳዩን ከሰብዓዊነት መንጠፍ ጋር ያቆራኘ በመሆኑ ከእኔ ጥናት ጋር የሚገናኝ ይሆናል፡፡ ነገር ግን ከሴተኛ አዳሪነት ጋር አያይዞ የሰብዓዊነት መንጠፍን ከመመልከቱ ባለፈ ጥናቱ ከዓላማውም ሆነ ከትኩረት ነጥቡ አኳያ ሲታይ ከእኔ ጥናት ጋር የጠበቀ ግንኙነት የለውም፡፡ በዚህም የአያሌው ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር በርዕሰ ጉዳይ ረገድ ከመመሳሰል ባለፈ ከንደፈ ሀሳብ ጀምሮ ባሉ ሌሎች ጉዳዮቻቸው የተለያዩ ሆኖ ስላገኘሁት፤ በእኔ ጥናት ከዳሰስኩት የሰብዓዊነት መንጠፍ ጽንሰ ሀሳብ ጋር አንድ አለመሆናቸውን መገንዘብ ይቻላል፡፡

በአራተኝነት የተመለከትኩት ጥናት አሻግሬ አምጤ በ2003 "ባይተዋርነት በመቅደስ ጀምበሩ ግጥሞች" በሚል ርዕስ ለሁለተኛ ዲግሪ ማሟያነት ያከናወነው ነው፡፡ ባይተዋርነት ለአካባቢው፣ ለሌላ ሰው፣ እንዲሁም ለገዛ ራስ እንግዳ መሆንን እንደሚያመክት አስፍሯል፡፡ በሥነ ማህበረሰብ፣ በፍልስፍና፣ በሥነልቡና፤ እንዲሁም በሥነጽሑፍ የሙያ መስኮች የሚጠና ጽንሰ ሀሳብ መሆኑንም አብራርቷል፡፡ ጥናቱ በመቅደስ ጀምበሩ ግጥሞች ባይተዋርነት የተወከለበትን ኪነጥበባዊ እሴት በማሳየት የባይተዋርነት አይነቶችን፣ ባይተዋርነት ያስከተለውን ተጽዕኖና ውጤቱን የመግለጽ ዓላማን የያዘ ነው፡፡ ባይተዋርነት ሰብዓዊ ጣጣ መሆኑን በመጠቆምም፤ የሜልቪን ሲማን (1959) ክልሰፋ መሰረት አድርጎ ባይተዋርነትን በአራት መድቦ ተመልክቷቸዋል፡፡ አንደኛው፣ ማህበራዊ ባይተዋርነት ሲሆን፤ ይሄም ከሚኖሩበት ማህበረሰብ በአስተሳሰብና መሰል ድርጊቶች መለየትን፣ ሀሳቡ ከሀሳባቸው አለመግጠምንተከትሎ የሚከሰት እንደሆነ ገልጿል፡፡ የግጥሙ ታሪክ እየመዘዘም ተንትኗል፡፡ ሁለተኛም ለስልጣን ባይተዋር መሆን ሲሆን፤ ይህ በአንድ በኩል አንድ ማህበረሰብ የሚያስተዳድረው አካል ችግሩን አልፈታለት ሲል በሌላ በኩል ደግሞ የሚያስተዳድረው አካልም ለሚጠየቀው ትያቄ ምለሽ መስጠትና ችግሮችን መፍታት ሲገባው ምክንያት እየደረደረ ከማህበረሰቡ ሲርቅ የሚከሰት ነው፡፡ ሦስተኛው፣ ግለ-ፍርቅነት ነው፡፡ ይህ ደግሞ ለራስ አዕምሯዊ ክንውን እንግዳ መሆንን፣ ለገዛ አዕምሮ ባዕድ መሆንን፣ ከራስ መለያየት ወይም የራስን መከበሪያ ፈልጎ አለማግኘትን የሚመለከት ነው፡፡ አራተኛው፣ ወለፈንዲነት ሲሆን፤ በምንም ነገር ላይ እርግጠኛ አለመሆንንና ለህይወት ትርጉም መጥፋት ነው፡፡ በመሆኑም አጥኚው እነዚህን የባይተዋርነት አይነቶች በመረጣቸው ግጥሞች (*ንባስል* 1984፣ *እኛ* 1990 እና *ሙጋ* 2000 ከሚሉት ሶስት መጻሕፍት ውስጥ የባይተዋርነት መከሰቻ ናቸው ብሎ በመረጣቸው) ታሪኮች አስረጅነት በማርክሲስት ንድፈ ሀሳብ ሂሳዊ ትንታኔ አቅርቦባቸዋል፡፡

በጥናቱ በማጠቃለያው እንዳስቀመጠውም የየግጥሞቹ ገጸ ሰቦች ለባይተዋርነት የተዳረጉት በትምህርት ምክንያት፣ የተሻለ ኑሮና ሥራ ለማግኘት በተፈጠረ ስደት፣ ተስፋ የጣሉበትን ባለማግኘታቸው፣ የመናገር፣ የመጻፍ፣ ሀሳብን በነጻ የመግለጽ መብቶችን በመነፈጋቸው፣ ተገዶ በመደፈር እንዲሁም የኑሮ መሰረታቸው በመናጋቱ

ነው፡፡ በትንተናው እንደታየውም የተወሰኑት ገጸሰቦች ባይተዋር መሆናቸውን ተረድተው ከባይተዋርነት ለመውጣት ጥረት ሲያደርጉ፤ የተወሰኑት ግን ባይተዋር መሆናቸውንና ያስከተለባቸውን ችግር ቢረዱም ከገቡበት ችግር የሚወጡበት አቅም በማጣት የኑሮ ጣዕሙ ጠፍቶባቸው ይታያሉ፡፡ ሌሎቹም ባይተዋር መሆናቸውን አለመረዳታቸውን መመልከት ችሏል፡፡

ይህ ጥናት ከእኔ ጥናት ጋር ምንም እንኳን ቀጥተኛ ግንኙነት ባይኖረውም፤ በጥናቱ የባይተዋርነት አይነቶች ተብለው ከተነሱት መካከል የማህበራዊ ባይተዋርነት የተወሰነ ቀረቤታ አለው ብዬ በማመኔ ዳስሼዋለሁ፡፡ በዚህ ጥናት የተነሳው የማህበራዊ ባይተዋርነት ለሰብዓዊነት መንጠፍ መንደርደሪያ የሚሆን ጅምር እንጂ የሰብዓዊነት መንጠፍን ወክሎ የቀረበ አለመሆኑን ተረድቻለሁ፡፡ በመሆኑም ይህ ጥናት ከዓላማ፣ ከንድፈ ሀሳብና ጽንሰ ሀሳብ፣ እንዲሁም ከመተንተኛ ዘዴና ከጥናቱ ግኝት አኳያ ሲመዘን ከእኔ ጥናት ጋር አንድነት ሊያስፈጥር የሚችል ጠንካራ መሰረት የሌለው ነው፡፡

በጥቅሉ ከእኔ ጋር በቀጥታም ይሁን በተዘዋዋሪ ግንኙነት አላቸው ብዬ የዳሰስኳቸው እነዚህ ጥናቶች ከእኔ ጥናት ጋር አንድ አይነት ያልሆኑና ይልቁንም የበዙ ልዩነቶች ያሏቸው ናቸው፡፡ በመሆኑም ጥናቴን "የሰብዓዊነት መንጠፍ ኪናዊ ፈርጆች እና ረቦች በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ" በሚል ርዕስ ለማከናወን የማያግዱ መሆናቸውን፤ ይልቁንም የጥናቱ መከናወን ስነ ጽሑፍን ከሰብዓዊነት መንጠፍ አንጻር ለማጥናት ለሚፈልጉ አጥኚዎች ለሥራቸው ግብዓት በመሆን ሊያገለግል የሚችል መሆኑን መገንዘብ ችያለሁ፡፡

# 3. ትንተና

## 3.1. የሰብዓዊነት መንጠፍ በ*የሕሊና ባርነት*፡ ከሞራል ፍልስፍና አንፃር

*የሕሊና ባርነት* በ1990ዎቹ አጋማሽ ላይ ከተጻፉ ልቦለዶች አንዱ ሲሆን፤ ትኩረቱን ከ1983ቱ ለውጥ በፊት በነበሩ የማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ምስቅልቅሎች ላይ ያደረገ ነው፡፡ በአሥራ አራት ምዕራፎች የተዋቀረው ይህ ልቦለድ፤ "ትግል ከራስ"፣ "ዋይታና ፌሽታ"፣ "ለሰው ሞት አነሰው"፣ "ኑሮ ካሉት"፣ "የምጽዋ ኮከብ"፣ የማይጠራው መንገድ"፣ "ለማን አቤት ይሏል"፣... በሚሉ ርዕሶች ተከፋፍሎ የቀረበ ነው፡፡ በዋና ገጸ ባህሪው ስንታየሁ አማካኝነት፣ ከቤተ መንግስት እስከ ወህኒ ቤት፤ ከወሎ ድርቅና የረሃብ ሰቆቃ እስከ አስመራ የጦርነት አውድማ፤ ከጋምቤላ ጥቅጥቅ ደኖች እስከ ጎጃም ገጠራማ እርሻ ቦታዎች፣ በየፈርጁ ያሉትን ሁነቶችና ሁኔታዎችን ተርኳል፡፡

የእነ ስንታየሁ፣ ፀጋዬ፣ አቶ ደጀኔና ሌሎችም የጋዜጠኝነት ሙያ ተቀይዷል፤ የሕሊና ነጻነታቸውን ተገፍፏል፡፡ በአስመራ በእነ ኮሎኔል በትሩ የሚገለጸው ሰራዊትም የጀግንነት ወኔው ተሰልቧል፤ ከፊሉም ልቡ ሸፍቶ ለአገሩ ፍቅር ሳይሆን ለገንዘብ አድሯል፡፡ የህዝብ አስተዳደር መዋቅሩ የሚመራውን ህዝብ ዘንግቶ ከህዝቡ ተነጥሎ ብቻውን በመሮጥ ነገውን ሊያሳምር ሲኳትን ይታያል፡፡ የወሎ ህዝብ በረሃብ አለንጋ ሲገረፍ አለሁ ባይ በማጣቱ እንደ ቅጠል ሲረግፍ የሚያሰማው የስቃይ ድምጽ ለጆሮ ይገብዳል፤ ሕሊናንም ያደማል፡፡ የሰው ሰብዕና ነጥፎ ይህ ጩኸት ለጊዜው ምላሽ ባያገኝም፤ በመጨረሻ ግን በዚህ መልኩ ስቃይና ብሶት የበዛበት ሥርዓት እርስ በእርሱ እየተብላላ ከስሩ በስብሶ በቁጣ ማዕበል ተገፍቶ ሲወድቅ ሕዝቦች የተስፋ ጭላንጭል ይመለከታሉ፡፡

በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ ውስጥ ክፋትና ደግነት፣ በቀልና ፀፀት፣ በደልና ይቅርታ፣ ባርነትና ነጻነት፣ በራስ መተማመንና አድር ባይነት፣ ጭቆናና ፍትህ፣ እኔነትና እኛነት፣ ወዘተ. አይነት የዚህች ዓለም የተቃርኖ ሁነቶች፤ እንዲሁም ምስቅልቅል ገጽታ በፊደላት ተቀርጸውና በሀሳብ ተደራጅተው በግልጽ ይታያሉ፡፡ የሰው ሀሳብና ግብሩ ሰብዓዊነቱን ሲፈትነው፣ በራስ ወዳድነት ፈረስ ተሳፍሮ በሰዎች ሕልውና ላይ ሲጋልብ፤ ከማህበራዊና ሞራላዊ እሴቶቹ ተፋትቶ ሰብዓዊ ክብሩን አጥቶ ሲያሳጣ፤ ሰብዕና

ተፈትኖ ከሰብዓዊ መገለጫው ሲርቅና ከእንስሳና ቁስ ተራ ገብቶ ሲገለጽ፤ በጥቅሉ ሰው የሚያሰኘውን ማንነት አጥቶ በሰብዓዊነቱ መንጠፍ ተገልፆ እናገኘዋለን፡፡ በዚህ ክፍልም በ*የሕሊና ባርነት* ልቦለድ የሰብዓዊነት መንጠፍ እንደምን ተከስቶ ታየ? የሚለውን ከሞራል ፍልስፍና አንጻር የሰብዓዊነት መንጠፍ ከሚገለጽባቸው እንስሳዊና ቁሳዊ (አኒማልስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን እና ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን) ፈርጆች አንጻር ለመመርመርና ለመተንተን የሞከርኩበት ነው፡፡ በስራቸው ሊካተቱና ሊገለጹ የሚችሉ ተሰናሳኝ የሰብዓዊነት መንጠፍ ጉዳዮችንም እግረ መንገዴን አጣምሬ ለማመላከት ሞክሬያለሁ፡፡

### 3.1.1. የሰብዓዊነት መንጠፍ ከ"አኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" አንጻር

*የሕሊና ባርነት* ከግለሰብ እስከ ቡድን፣ ከተርታው ሰው እስከ ሹማምንት፣ ከተራ ወታደር እስከ ከፍተኛ መኮንን፣ ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ መደብ የተሰጣቸው ገጸ ባሕሪያት በምግባርና ባህርያቸው አንጻር ሰው የመሆን ልዩ ተፈጥሯቸው የለገሳቸውን ሰዋዊ ውክልና ተነጥቀው ከእንስሳት ተራ ተመድበው እናገኛቸዋለን፡፡ ወደ ዋናው ጉዳዬ ለመዝለቅ ያክል፣ ተራኪው የአዲስ ዘመን ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ የሆነውን አቶ ደጀኔ ጉርሙን "ተናካሽ ውሻ ያሳደደው ይመስላል፡፡" (ገጽ፣ 10)፤ ሲል የገለጸበትን ሁነት ላነሳ ወደድኩ፡፡

አቶ ደጀኔ በራሱ አዕምሮ የሚመራ አይደለም፡፡ ሁሌም በሚያደርጋቸው እንቅስቃሴዎች "የበላይ ትዕዛዝ ነው" ማለትን የሚያዘወትር የራሱ የሆነ የሀሳብም ሆነ የምግባር እሴት የሌለው ነው፡፡ ይህ ደግሞ አንድም በሰው አማካኝነት የሚንቀሳቀስ የግዑዝ ነገር ባህሪ ሲሆን፤ አቶ ደጀኔ ግን በራሱ አስተሳሰብና ፈቃድ የማይመራ ቢሆንም በውጫዊ ጫናና ትዕዛዝ ተመርቶ "የበላይ ትዕዛዝ ነው" እያለ ተግባሩን የሚከውን ተንቀሳቃሽ አካል ነው፡፡ ሆኖም የተነገረውን መልሶ ከመንገር የዘለለ ሚና የሌለው፤ እንደ ሰው ያውም እንደ አንድ ጋዜጣ ዋና አዘጋጅ ይጠቅማል የሚለውን አዲስ ሀሳብ የማመንጨትና ወደተግባር የመቀየር አንዳች ድርሻ የማያበረክት፣ የተባለውን ብቻ ለማስተጋባት የተቀመጠ ነው፡፡ ታዲያ ያሳደደውና "ተናካሽ ውሻ" ተብሎ የተገለጸው ምንድን ይሆን? ይሄን ለማግኘት ተራኪውን ተከትለን በሊቀመንበሩ ወደተጠራው የስብሰባ አዳራሽ በማምራት ተያያዥ ሁነቶችን እንመልከት፡፡ ለስብሰባ

የተሰባሰቡ ሹማምንት በአደራሹ ዙሪያ ሁለትም ሶስትም እየሆኑ እዚህም እዚያም ሆነው በጋራ እያወሩ ሳለ፤ ድንገት ለአንድ አፍታ የገጠማቸውንና ያሳዩትን ባህሪ ተራኪው እንዲህ ይነግረናል፤

> *መጡ፣ መጡ፣ ቦታችሁን ያዙ" የሚል ድምጽ አቋረጣቸው፡፡ ይጠባበቁ የነበሩ ባለስልጣኖች ሁሉ ውሻ እንዳስበረገጋቸው በጎች ግር ብለው በመግባት አዳራሹ ውስጥ ቦታቸውን ለመያዝ ተዋጊ በሬ እንዳወከው የበረት መንጋ ይተራመሱ ጀመር፤ ... ሰብሳቢው ገቡ፤ ሁሉም ብድግ አሉና ጨብ፣ ጨብ፣ ጨብ፣ ጨብ፣ በሚል አዲሱ የጭብጨባ ዘይቤ ተቀበሏቸው፡፡ ሰብሳቢውም እንደተለማመደ ተዋናይ በቅጽበት ፊታቸውን ፊታ አድርገው ደረቅ ፈገግታ በማሳየት ባለስልጣኖች እንዲቀመጡ እጆቻቸውን ዘርጋ በማድረግ የፈቃድ ምልክት ሰጡና ተቀመጡ፤ (ገጽ፣ 12-13)፡፡*

ከዚህ ጥቅስ መረዳት የሚቻለው፤ በየቦታው ያሉ የስራ ኃላፊዎች እንደ ውሻ የሚያስበረግባቸው ነገር መኖሩን፤ እነርሱም ሁሌም በርግገውና ድንጉጥ ሆነው መገኘታቸውን ነው፡፡ ለምን ጉዳይ ስብሰባ እንደመጡ የሚያውቁና ትላልቅ ተቋማትን የሚመሩት እነዚህ ሹማምንት በበግና በበረት መንጋ ተመስለው ሲበረግጉና ሲተራመሱ ይታያል፡፡ በውሻና ተዋጊ በሬ ተገልጸውም በጎችን ያስበረግጋሉ፤ የበረት መንጋውንም ያውካሉ፡፡ ታዲያ የስብሰባ ታዳሚዎች ለምን በረገጉ? ለምንስ ተተራመሱ? በበግና በበረት መንጋስ ለምን ተገለጹ? ያዩት ሊቀመንበሩንና በእርሳቸው ዙሪያ ያሉ ጥቂት ኃላፊዎችን ሆኖ ሳለስ አስበርጋጊው በውሻ፣ አዋኪውንስ በተዋጊ በሬ ለምን ተገለጹ? የሚሉትን ጥያቄዎች ተከትዬ ጉዳዩን ለመመልከት ልሞክር፡፡

ምንም እንኳን ውሻ የጌታው ታማኝ አገልጋይ ቢሆንም፤ ተናካሽነቱ፣ ተሽቆጥቋጭነትና አንዳንዴም በበላበት አዳሪና ለበላበት ጪሂ መሆኑም የማይዘነጋ ነው፡፡ ምክንያቱም ውሻን በታማኝነቱ ብሎም በኃይለኝነቱ የሚገልጹት እንዳሉ ሁሉ፤ በተቃራኒው የተልከስካሽነት ባህሪውንና ለሆዱ አዳሪነት ገጽታን የሚያላብሱትም የበዙ ናቸው፡፡ እናም የተሻለ ላበላው የሚያድር፣ ጌታውን ሲያይ ጭራውን እያወዛወዘ የሚቅበጠበጥና የሚለማመጥ ሲሆን፤ አሳዳሪው "ጃስ" ካለውም ጌታው አጠገቡ እስካለ የሚችለውንም፣ የማይችለውንም ለማሳደድ ከቻለም ለመንከስ የሚፍጨረጨር እንስሳ ነው፡፡ ይህ መፍጨርጨሩና የማይችለውን እችላለሁ ባይነቱ ግን አሳዳሪው በቅርበት እስካለ ግሎ የሚቆይ፤ ነገር ግን አሳዳሪው ፊቱን አዞሮ ከአጠገቡ ራቅ ሲል ጭራውን ቀብሮ የሚለማመጥ አይነት ባህሪም ያለው ነው፡፡ በአንጻሩ በጎች የዋህ ብቻ ሳይሆኑ ጥቃትን

የሚፈሩና ችግርን መጋፈጥ የማይችሉ ደካሞች፤ ውሻ ባዩና በሮጠባቸው ቁጥርም ተባብሮ ከመከላከል ይልቅ የማምለጫ አቅጣጫቸውን እንኳ ሳያጤኑ የሚበረግጉ ናቸው፡፡

እነዚህ ሁለት እንስሳት በዚህ መልኩ በጽንፍ የቆሙ አሳዳጅና ተሳዳጅ ቢመስሉም፤ አብሮ በመዋልና በማደር በሚፈጠር ቅርበት ውሾች በጎችን በአግባቡ ጠብቀው ሲመሩም ይስተዋላል፡፡ በዚህ መልኩ የነካሽነት ብሎም የጠባቂነት ሚና ያለው ውሻም ሆነ፤ በታዳኝነትና በተጠባቂነት ማዕቀፍ ውስጥ ያሉት በጎች አብሮ የመዝለቃቸውና በጋራ የመኖራቸው ሂደት የሚወሰነው አንድም በበጎቹ ከውሾቹ ቁጥጥር ስር መሆንን ላይ፤ አንድም በውሾቹ የየእለት ስሜት ላይ ተመስርቶ ሊሆን እንደሚገባ መገመት አያዳግትም፡፡ ለዚህም ነው በጎች ውሻን ሲያዩ የሚበረገግት፤ ለማምለጥ ሲሞክሩም ቀድሞ መንገዳቸውን ሲዘጋባቸው በሚመራቸው አቅጣጫ የሚጓዙት፡፡ በአዳራሹ የተገኙት ሹማምንትም ሆኑ የጋዜጣው ዋና አዘጋጅ አቶ ደጀኔ የእነዚህ ሁለት እንስሳት ሁለተኛ ባህሪ መገለጫ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ ምክንያቱም ከላይ ያለው የበታቹን በማስጨነቅ፤ ከታች ያለውም ለበላዩ በመሽቆጥቆጥ ላይ ሰብዕናቸውን ገንብተዋል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ በውሻ የተመሰሉት ሹማምንት ግዛትና ስርዓታቸውን ለማስጠበቅ የማይወስዱት እርምጃ፣ የማይፈጽሙት ግፍ የለም፡፡ ከታች ያሉት ኃላፊዎችም ይሄንን በመፍራት ዝቅ ብለውና ሰውነታቸውን አዋርደው መኖርን ለምደዋል፡፡ ይህ ለእነርሱ የሞራል ፍልስፍናቸው ጥግ ነው፡፡

ኃላፊዎቹ በሚወስዱት ርምጃ እንደ ውሾቹ ተናክሰው ራሳቸውን ለማስከበር የሚጥሩ፤ ተከታይ ሹማምንቱም የጋራ ኃይላቸውን ሳያውቁት ዘወትር ፈርተውና በርግገው የሚኖሩ፣ እንኳን ለሌላው ሊደርሱ ራሳቸውን ማዳን የማይችሉ በጎች ሆነዋል፡፡ በዚህም ኃላፊዎቹ የሰውነት ባህሪያቸውን ትተው እንደ ውሻ ላበላቸው ጪሂና ተሽቆጥቋጭ፤ አዳራሹን የሞሉት ሹማምንትም ራሳቸውን የማያውቁና አቅማቸው እስከምን እንደሆነ እንኳን ለመሞከር ያልደፈሩ ከንቱ ሆነው እናገኛቸዋለን፡፡ እንደ ውሻ ሲያስበረግጉ፤ እንደ በግም ሲበረግጉ የሚኖሩ እንስሳዎች እንጂ እንደ ሰው በህሊናቸው ተመርተው በሃሳብ የበላይነት አሸንፈው በጋራ ለመሰለፍ የማይጥሩ፤ እርስ በእርስ ከመደጋገፍ ይልቅ ለመነካከስ፣ ስንታየሁ "ደግሞ ይሄ ፍሪጅ የመሰለ ነገር የማንን ትግል ለማቀዝቀዝ ነው" (ገጽ፣ 8) ሲል በሃሳቡ እንደገለጸውም በሚያከናውኑት ተግባር ሁሉ

አንዱ ሌላውን ለማሳደድ የተፈጠሩ መስለው ሳይሆን ሆነው ቀርበዋል፣ የሰውነት ክብርና ህሊናቸውንም አጥተዋል፡፡

ሊቀመንበሩም ቢሆኑ ከዚሁ እንስሳዊ ባህሪ የሚወጡ አይደሉም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ውሾች በጎቹን ጠብቀው እንዲመሩም ሆነ ነክሰው እንዲያስወግዱ ወደ ሰፊው መንጋ "ጃስ" የሚል አካል የግድ ይላል፡፡ ከዚህ በዘለለም ግዳያቸውን አድነው ለመያዝ የድርሻቸውን ተሳትፎም ሲያደርጉ ይስተዋላል፡፡ ለዚህም ተራኪው "… የትኛው አይጥ ላይ እንደምትዘል የምታማርጥ ያደባች ድመት ይመስላሉ፡፡" (ገጽ፣ 13)፣ ሲል የገለፀበትን መመልከቱ ተገቢ ነው፡፡ ድመቷ፣ ውሾቹም ሆኑ ተዋጊ በሬው የሚያመሳስላቸው አንድ ጉዳይ አለ፡፡ ሁሉም የራሳቸውን ደስታ ለማግኘት፣ የበላይነትታቸውን ለማስመስከር፣ እጅጉን የሚተጉ ናቸው፡፡ ለምሳሌ፣ ድመት ሆዷን ለመሙላት አይጥ ታድናለች፡፡ አድና የያዘቻትን አይጥ እንደማታመልጣት ካረጋገጠች በኋላ ቶሎ አትበላትም፣ ከአይጧ ጭንቀት ይልቅ የእርሷ ደስታ ስለሚበልጥባት ከመመገቧ በፊት ትጫወትባታለች፡፡ በእነዚህ ሹማምንት የሚስተዋለውም ይሄው ነው፡፡ ብዙዎችን አስረዋል፣ በግርፋት አሰቃይተዋል፣ ገድለዋልም፡፡ የእነርሱን ስርዓት ለማስጠበቅ፣ ህልውናቸውን ለማቆየትም ብዙ አካላዊና ሥነ ልቡናዊ ጫናም ፈጽመዋል፡፡

ይሄንንም በእነ አቶ ገብረ እግዚአብሔር እና ስንታየሁ ላይ ሲፈጽሙት አይተናል፡፡ አቶ ገብረ እግዚአብሔር ስርዓታቸውን በመቃወማቸው ከእስር አልፈው ለከፋ ድብደባ በመዳረጋቸው ቋሚ የሆነ የአካል ጉዳት ደርሶባቸዋል፡፡ "… እጃቸውን ወደ ብልታቸው አመለከቱት እዚህ እኮ ሰው እንዳንሆን አድርገው ነው የደበደቡን፡፡ ሴት መሄድ ቀርቶ ለሽንትም መጠቀም የቻልነው በስንት መከራ ነው፡፡"(ገጽ፣ 231)፣ በሚል ከራሳቸው አንደበት ተደምጧል፡፡ በተመሳሳይ ስንታየሁ ምንም እንኳን በስራው የሚሉትን ሁሉ የሚፈጽም ቢሆንም፣ ሕሊናው ግን ሁሌም ስለሚሞግተው የታሰረ ህሊናውን ነጻ የሚያወጣ ሰብዕናን ባይጎናጸፍም ውስት ለውስት በሚንሾካሾካቸው ወሬዎችና አንዳንዴም ተናግሮ ነገር ግን በተደጋጋሚ "ወይ ይሄ ምላሴ ዘንድሮ ሳያስገድለኝ አይቀርም" በማለት በሚሳቀቅባቸው ቃላቶች ምክንየት በህልውናቸው የመጣ መስሎ ስለተሰማቸው አስረውታል፣ ለከፋ ድብደባም ዳርገውታል፡፡

*ደም፣ አክታና ተውከት ወለሉ ላይ ተንጠባጥቧል፡፡ ለተራቡ አንበሶች የሰጠው መስሎ ተሰማው፡፡ ...ወደ ስንታየሁ ጠጋ አለና ሱሪውን እንዲያወልቅ በምልክት ነገረው፡፡ ...ሱሪውን ያወልቅ ጀመር፡፡ አውልቆ ሲጨርስ እግሮቹን በእጆቹ መሀል አሳልፈው አሰሩትና አጣና አስገብተው በማንሳት ዘቀዘቁት፡፡ የአጣናዎቹን ጫፍና ጫፍ ግራና ቀኝ ያሉ በርሚሎች ላይ አስደገፉ፤...” (ገጽ፣ 232)፡፡*

በዚህ መልኩ ኢ-ሰብዓዊ ተግባር የተፈጸመበት ስንታየሁ፣ እግሩ፣ ቂጡ፣ ጀርባው፣ በመላላጡ መቆምም ሆነ መቀመጥ ሳይችል ለሽንቱ ሳይቀር በሰው እየተመላለሰ በሆዱ ተኝቶ ሶስት ወራትን ካአስቆጠረ በኋላ ነው ራሱን ችሎ መንቀሳቀስ የጀመረው፡፡ ይህም የሰው ልጅን የሰብዕና ውርደትና የጭካኔ መጠን የሚያሳይ ነው፡፡

ወደ ቀደመ ነገሬ ልመለስና፣ ከላይ የጠቀስኳቸው በአዳራሹ የተገኙ ሹማምንት የተገለጹበት ሌላው ባህሪ የተዋጊ በሬ እና በበረት ውስጥ ያለ የከብት መንጋ ነው፡፡ ይህ በአንድ አዳራሽ የተሰበሰበ ሰው፣ በአንድ በረት እንደሚያድር፤ ነገር ግን በአንድ ተዋጊ በሬ በሚታመስ መንጋ ተወክሏል፡፡ “ተዋጊ በሬ እንዳወከው የበረት መንጋ ይተራመሱ ጀመር”፤ ሲል ተራኪው የገለጻቸው እነዚህ ሹማምንት፤ ልክ እንደ ተዋጊው በሬ አይነት አንዳች ኃይል መጥቶ ካላነቃቸው በራሳቸው ምንም ማድረግ የማይችሉ፣ ከአንድ ወገን ግፊት ሲመጣ ምድር ቁና የምትሆንባቸው በህሊናቸው ሳይሆን በሌላ አካል የሚነዱ በመሆናቸው ነው፡፡ ተዋጊ በሬ ለመንጋው ሰላም አይሰጥም፡፡ ተረጋግቶ እረፍት ላይ ያለውን መንጋ ይረብሻል፤ መንጋውም ማሸነፍ እንደማይችል በማመን ለአንዱ ተዋጊ ኮርማ እጅ ሰጥቶ ይታመሳል፤ ይታወካል፡፡ ከልክ ያለፈ መሸቆጥቆጥም ሆነ አድር ባይነት፤ በአንጻሩ ገደብ ያጣ አሳዳጅነትም ሆነ አዋኪነት ከሰው ምግባር የራቁ፣ የግብረገባዊ እሴት ያልቃኛቸውና የሰብዓዊ መገለጫ ያልሆኑ፣ ይልቁንም የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ናቸው፡፡

በአገር ጉዳይ ላይ ሊመክሩ የተሰባሰቡት እነዚህ ሹማምንት፤ የተሰበሰቡበትን ጉዳይ ወደጎን ትተው አንዳንዶቹ እርስ በእርስ ያወራሉ፤ አንዳንዶቹም በያዙት ወረቀት ላይ ትርጉም የማይሰጥ ስዕል መሳይ ነገር ይጫጭራሉ፤ አንዳንዶቹም ሀሳባቸውን ጥለው ተኝተዋል፡፡ ይህ ዓላማን መዘንጋት፤ ያሉበትን ስፍራ አለማወቅ፤ እንደሰው አዕምሮን ማሰራት አለመቻል ነው፡፡ የሚመሩትን ህዝብ ችግርና ስቃይ ሊረዳ የሚያስችል ሰብዕና መንጠፍ፤ የግብረ ገብ እሴት ማጣት ነው፡፡ እንደ አይጥና ድመቷም የእነርሱን ደስታ እንጂ የህዝቦችን ጭንቀት አለማሰብ ነው፡፡ በዚህ መልኩ በተገነባ ሰብዕናቸው

ምንም እንኳን በአያሌ ድሎች ታጅቦ ለፓርቲ ምስረታ ወደፊት እየገሰገሰ ያለ ስርዓት መኖሩን ቢገልጹም፣ እውነታው ግን "ዋይታና ፌሽታ" በሚለው በሁለተኛው የልቦለዱ ምዕራፍ እንዲህ እናገኘዋለን፣

> *እጭኗ ላይ ለሞተው ልጅ ለማልቀስ እንኳን አቅም ያጣች እናት፡፡ ... ወላጆች በጉዞ መሀል ዳገቱን አጋምሰው ልጆቻቸው ሲለዩአቸው፣ ጥለው ለመሄድ ወይም እዚያው አብረው ለመሞት መምረጥ ተቸግረው ሲያምጡና ሲሟገቱ አስተዋለ፡፡ ... ብዙዎች ትንፋሻቸው እየከሰመ ስለሆነ የሞተውን ካልሞተው መለየት ያስቸግራል፡፡ ሁሉም ቀስ እያሉ እየሞቱ ነው፡፡ በዚህ የሙታን ገበያ፣ የሬሳ ሽታ፣ የሞት ሽታና የበሽታ ሽታ ያውዳል፣(ገጽ፣ 46-47)፡፡*

ይህ የተራበ ህዝብ እንደሰው የሚረዳው ይፈልጋል፣ ነገር ግን አላገኘም፡፡ ሲብስበትም የማግኘትን ተስፋ ይዞ ይጓዛል፣ በጉዞውም ይወድቃል፣ ይሞታልም፡፡ ነገር ግን ማንም ማንንም ሲደግፍ፣ ማንም ማንንም ሲረዳ አይታይም፡፡ ጉልበት መራመድ፣ እጅ መደገፍ፣ አንደበትም መናገር፣ ዓይን እንኳን ለሚሞት ልጅ እንባ ማውጣት ተስኗቸዋል፡፡ መሪዎች ነን ባዮቹ ሰው እንደመምራታቸው ይሄን አይገነዘቡም፣ ይልቁንም ስብዕናቸው ተገፍፎ ልክ እንደ ድመቷና አይጧ በእነዚህ ሰዎች ህይወት ይጫወታሉ እንጂ በረሃብ አንጀታቸው የጣር ድምጽ የሚያሰሙ ህጻናትን እንኳ የሚሰማ ጆሮ አልነበራቸውም፡፡

> *ስንታየሁ ጠዋት ያየውን ልጅ የሚመስል ህጻን ብቻውን ቆሞ አየና ጠጋ አለ፡፡ ...የሚሰጠው ምግብና መልስ ስላጣ፣ መሀረቡን አውጥቶ ንፍጡን ጠረገለትና፣ ዝንቡን እየተከላከለለት ይጠይቀው ጀመር፡፡ ሕጻኑ በግምት ስምንት ዓመት ይሆነዋል፡፡*
>
> *"እናትህ የት አለች?"*
> *"የለችም"*
> *"አባትህስ?"*
> *"የለም"*
> *"ታዲያ ከማን ጋር መጣህ?"*
> *"ከአክስቴ ጋር ነበር"*
> *"ታዲያ አሁን የት አለች?"*
> *"እኔ እንጃ፣ እዚህ ካደረስኩህ ምግብ የሚሰጥህ አታጣም ብላኝ ጥላኝ ሄደች፡፡"*
> *"እናትና አባትህስ?"*
> *"ሞተዋል"...*
> *"ሲሞቱ አይተሃል አንተ?"*
> *"አዎን፡፡ ከሞቱ በኋላ ወስደው ከጓሮ ቀበሯቸው፡፡"*

*“ለምን ቤተ ክርስቲያን አልወሰደ ቸውም?”*
*“ብቃ የሚሸከም ሰው ስለሌለ ጎትተው አወጧቸውና ጓሮ የከብቶቹ በረት የነበረው ላይ ቀበሯቸው፡፡”*
*“ከብቶችስ የቧችሁም?”*
*“አንዳንዶቹ ሳር ሲታጣ ጊዜ በፊት ሸጧቸው፤ አንዷ ደግሞ እዚያው ሜዳ ላይ ሞተችና ቆዳዋን ገፈን በላናት፡፡”*
*“የሞተችዋን በላችሁ?”*
*“ታዲያ ሲርበን እኛም እንሞት የለ፡፡” (ገጽ፣ 40-42)፡፡*

ከዚህ ምልልስ መረዳት እንደሚቻለው፣ ይህ ማህበረሰብ የመረዳዳት፣ የመደጋገፍና አንዱ የአንዱን ችግር የመካፈል ጠንካራ ባህል፤ የሞቱ እንስሳትን ያለመመገብ ግብረ ገባዊ እሴት አለው፡፡ ረሃብ ሲጸናበት፣ እርስ በእርሱ የመደጋገፍ አቅም ሲያጥረው ሕይወቱን ለማትረፍ ሲል ለምጽዋት እጁን ዘረጋ፤ የግብረ ገብ እሴቶቹንም ዘነጋ፡፡ ሆኖም በዚህ ህዝብ መኖር ላይ ህልውናቸው እንደተመሰረተ ያልተገነዘቡት ሹማምንት የገነቡት ሰብዕና የሚሰማውን የጣር ድምጽ፤ የሚታየውን ሰቆቃ ቸል እንዲሉ አድርጓቸዋል፡፡ ይህ ተግባር ግን ከኃላፊነት በዘለለ ሰብዓዊነትን የሚጠይቅ ቢሆንም፤ የሞራል ግዴታ ተሰምቷቸውም እነዚህን ህዝቦች አላሰቧቸውም፡፡ ከሪፖርት ባለፈ ጉዳዩን በቅርበት ያዩትም ቢሆን፣ “አንድ ባለስልጣን ረሃብተኞችን እያዩ እንባቸው ሲፈስ ተመለከተ” (ገጽ፣ 39)፤ ሲል ተራኪው እንዳሰፈረው፣ እንዲሁም፣ ዓለሚቱ “የዛሬ ባለስልጣኖች ‹የአህያ ባል ከጅብ አያስጥልም› እንደሚባሉት ናቸው”(ገጽ፣ 238)፣ እንዳለችው፤ እንባን ከማፍሰስ ያለፈ ኃላፊነታቸውን ሲወጡም ሆነ አንዳች የሰብዓዊነት ተግባር ሲያከናውኑ አልታዩም፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ሹማምንት ህዝቡን ሊያገለገሉ ሳይሆን የበላይ አለቆቻቸውን ሊላላኩ ቦታውን የያዙ ስለመሆናቸው አምነው ተቀብለዋል፤ ስብዕናቸውንም በዚሁ ልክ ቀርጸዋል፤ ፍቅርና ሰብዕናቸውን ለጥቅም አሳልፈው ሰጥተዋል፡፡ እናም እነዚህ ሹማምንት ሰብዓዊነታቸው ነጥፏል፤ ስልጣናቸውም ስብዕናቸውን ገፍፎ ከእንስሳት ጎራ አድርሷቸዋል፡፡

ይህ የሰብዓዊነት መራቆት በእነዚህ ሹማምንት ብቻ ተወስኖ የቀረ ሳይሆን፤ ይህን እውነት እያዩ እንዳላዩ አንደበታቸው ዝም ያለ፤ ብዕራቸውም የዶለዶመ ጋዜጠኞችንም የሚመለከት ነው፡፡ በልቦለዱ እንደተጠቀሰው፣ “… የሶሻሊስት ጋዜጠኛነት የተቀየደ በቅሎ ማለት ነው፡፡” (ገጽ፣ 150)፡፡ በቅሎ እንዳትጎዳ ጥሩ እንክብካቤ ይደረግላታል፤ ጥሩ አመል እስካላትም በወጉ ተጭና ጌታዋን ታገለግላለች፡፡ ይሁን እንጂ በመጥገቧ ወይም በሌላ ምክንያት አመል ካወጣች ለጌታዋ ስጋት ናትና ትሰከላለች፡፡ መሰከሏ

ደግሞ እንደርሷ ሳይሆን እንደ ጌታዋ ፈቃድና ፍጥነት እድትጓዝ ያደርጋታል፡፡ በዚህ ጊዜ እንደታዘዘች እንጂ እንደ ልቧ መራመድና መዝለል ስለማትችል ያለ ስጋት ይገለገሉባታል፡፡ የእነዚህ ጋዜጠኞችም እውነት ይሄ ነው፡፡ መልካም የሚባል እንክብካቤ አላቸው፤ ባለስልጣናቱ የዋሉበት ይውላሉ፤ ያደሩበትም ያድራሉ፤ በአንድ ገበታ ባይቀርቡም አብረው ይመገባሉ፡፡ በዚህ መልኩ ካገኙት ምቾት መውጣትን ስለማይፈልጉም በጥቅም ልጓም ተሸብበው ሙያዊ ኃላፊነታቸውን ቸል ብለዋል፡፡ ይሄን የተገነዘቡት ሹማምንትም በእነርሱው ፈቃድና ይሁንታ ላይ ጥገኛ አድርገው ቀርጸዋቸዋል፡፡ ሹማምንቱም ይህን ማድረግ እንደሚችሉ አምነው "በሉ እንግዲህ በሰላም ለማደር ሞክሩ" (ገጽ፣ 15)፣ እያሉ ማስፈራራቱን፤ ጋዜጠኞቹም ከዚህ የዘለለ አማራጭ እንደሌላቸው አስበው "አይ መከራዩ፣ ዛሬ ደግሞ ምን እንዲቀናበርላቸው ይሆን የሚፈልጉት?" (ገጽ፣5)፤ እያሉ መኖርን ተላምደውታል፡፡ የሞራል ፍልስፍናቸውም በዚሁ ልክ ተቃኝቶ ከብዙሃኑ በተለየ በራሳቸው ዓለም አኑረቸዋል፡፡

ከተሜውም ቢሆን ያለውን ተካፍሎ የመብላት የሞራል ኃላፊነቱን ዘንግቶ አጋጣሚውን በመጠቀም መንጠቅን የተለማመደ ይመስላል፡፡ በዚህ የረሃብ ገጽታ በከፋበት፣ ሰዎች እንደቅጠል በሚረግፉበት፣ በሞተና በሕይወት ያለ በማይለይበት ዘግናኝ የሙታን ገበያ በፈጠረው የረሃብ ድባብ ውስጥ እንኳን ሆነው፤ ጊዜያዊ ሀብት ስለያዙ ብቻ ነገ በእነርሱም መሰል እጣ እንደሚደርሳቸው የዘነጉ ሰዎች የእነዚህን በጣር ላይ ያሉ ወገኖቻቸውን ሀብትና ንብረት ወደመቀራመት ሲሄዱ እናያለን፡፡ "አንዳንድ የከተማ ሰዎች ረሃብተኞቹ በደጉ ጊዜ ያፈሯቸውንና በደህና ጊዜ የተዋቡባቸውን ጌጣጌጦች በአንድ ብርና በሽርፍራፊ ሣንቲም ለመግዛት ሲሽቀዳደሙ ተመለከተ፤" (ገጽ፣ 39)፡፡ በዚህ መልኩ የሚገለጹት አንዳንድ የከተማው ነዋሪዎችም ሰዎችን በመርዳት ሰብኣዊ ተግባር ከመፈጸም፤ ሞራላዊ ግዴታቸውን ከመወጣትና ሰብዓዊ ፍቅር ከማሳየት ይልቅ ጌጣጌጦች ለመግዛት ሲሽቀዳደሙ ይታያሉ፡፡ በህዝብ የተመላችዋን ከተማም የመረዳዳትና የመተሳሰብ ግብረ ገባዊ እሴቱ የተነጠለው መኖሪያ እንደመሆኗም፤ ወና መስላለች፡፡ ከቀጣዩ ታሪክም ይሄንኑ እንረዳለን፡፡

> *ጫካው ውስጥ ራቅ ብሎ የዱር አሳማ ያስካካል፡፡ "ተው ጃል!" አለና "ኧረ ጎራው! ኧረ ወንድ ኡ!" እያለ ያዜም ጀመር በሞቅታ፣ እንደ አገሩ ጀግኖች፡፡ ያ ጋርጠው ለካ ወዶ አይደለም ሞቅ ባለው ቁጥር*

*የሚፎክረው፣ እንዲህ ዙሪያው ወና ሆኖበት ነው አለና አሰበ፤ (ገጽ፣ 154)፡፡*

ይህ የስንታየሁ ሁኔታ ከአሳማዎቹ ማስካካል በዘለለ የአከባቢውን ወይም ዙሪያውን ወና መሆንን እንመለከት ያደርገናል፡፡ ይህ ወናነት ደግሞ ባዶነት ነው፡፡ አንድ ቤት ወይም ከተማ ወና ሆነ ሲባል ለዓመታት ተዘግቶ ባዶውን ኖረ ወይም ሰው አላባ ሆነ ማለት እንደመሆኑ፤ ወና ሲሆን ይቆሽሳል፣ መጥፎ ሽታንም ያመጣል፡፡ ታዲያ አካባቢው ሰው እየኖረበት ለምን ወና ተባለ? ብሎ ለጠየቀ ደግሞ፤ ሰዉ በሀሳቡም ሆነ በምግባሩ እንስሳዊ ባህሪን በመላበሱ ማለት ይቻላል፡፡ ከተማ የሚደምቅ፣ መኖሪያም የሚመስል ሰው ሲኖርበት፣ ሰዋዊ ምግባር ሲገለጽበት ነው፡፡ ካልሆነ ሰው እንደሌለበት ተቆጥሮ ወና መሆኑ አይቀሬ ነው፡፡ እርግጥ ነው የሰው ልጆች ለሞራል እሴቶች አልገዛ ብለው በዝሙት ወድቀዋል፤ እርስ በእርሳቸው ተላልቀዋል፤ አልተዛዘን አልረዳዳ ብለዋል፡፡ ቅቡል የሆኑ ግብረ ገባዊ እሴቶችን ገፍተው በህብረተሰቡ እንደ ነውር የሚቆጠሩትን ተቀብለዋል፡፡ መልካምነትን ሳይሆን ዝሙትን እንደ ጽድቅም ቆጥረዋል፡፡ "እሷም ቢሆን ታሳዝናለች፡፡ ባሏ ከታሰሩ ወራት አልፈዋል፡፡ ሰው ናትና ያምራታል፡፡ በእግዚአብሔርም በኩል የሚያስመሰግን እንጂ የሚያስኮንን አይመስለኝም፤" (ገጽ፣ 24)፤ የሚለው የነስንታየሁ በስሜት የተመላ ወሬም የዚሁ ማረጋገጫ ነው፡፡

ጽድቅ የመልካምነት ፍሬ ነው፡፡ መልካምነት ደግሞ ለሰዎች ደስታ መፍጠር ብቻ ሳይሆን፣ ህመማቸውን ታሞ በችግራቸው አለሁ ማለትን፤ እንባቸውን አብሶ ነገን እንዲኖር ድረግን ይጠይቃል፡፡ ከዚህ ታሪክ የምንረዳው ግን በእግዚአብሔር ዘንድ የሚያስመሰግን ተግባር ሆኖ የቀረበው በእጅ ያለን ገንዘብ ተካፍሎ ችግርን መሻገር ሳይሆን፤ የሰው ሚስት አንሶላ ተጋፍፎ ማነወር ነው፡፡ እንደ ስንታየሁ ላሉ በዚህ መልኩ ለሚገለጹ ገጸ ባህሪያት ደግሞ ከራሳቸው ስሜትና ፍላጎት በዘለለ የማህበረሰቡ ባህልና ወግ ምናቸውም አይደል፡፡ ይልቁንም የእነርሱ የሞራል ፍልስፍና በችግር መረዳዳትንና መተሳሰብን አያውቅም፡፡ የታሰረን የመጠየቅ ማህበራዊ እሴትም የላቸውም፡፡ ለእነርሱ መልካምነትና በፈጣሪያቸው ዘንድም የሚያስመሰግን መስሎ የሚሰማቸው ቆንጆ ሴቶችን ማማገጥ፤ የአባ ወራ ሚስት አንሶላ መጋፈፍ ነው፡፡ ስንታየሁም በዚሁ መልኩ በግላዊ ስሜቱ ምክንያት ማህበራዊ እሴቱን አጥቷል፤

ሰብዓዊነቱን ተገፍፎም እንስሳዊ ባህሪን ተላብሷል፡፡ ይሄ እንስሳዊ ባህሪውም ከሕሊናው ሳይሆን ከሰዎች እይታ ለመከላከል በሚያስችለው መስመር ፍላጎቱን እንዲፈጽም አስገድዶታል፡፡

> *እንደጎመጀ አንበሳ ይወርድባት ጀመር፡፡ የስሜታቸውን ማየል ተሰላለሉና ስንታየሁ ወደጫካው እያጫወተ አስገባት፡፡ በጨረቃዋ ብርሃን እየተያዩ ውስጥ አካላቸውን ተፈታተሹ፡፡ አምሮታቸውን አወጡ፣ (ገጽ፣ 146)፡፡*
>
> *አብራው ከምትማር የሰፈሩ ልጃገረድ ጋር ወደ ሰፈራቸው ሲመለሱ ኩሸት ያምረውና እንጆሪ እንብላ ብሎ ወደ ጫካው መሃል ይዟት ይገባል፡፡ ሰናይትም ለአቅመ ሔዋን የደረሰች በመሆንዋ ጥርጣሬ አድሮባት ሆዷ ቦጭ ቦጭ እያለ ትከተለዋለች፡፡ በሀሳቡ የጠነሰሰው ድብቅ ፍላጎት ስላለው ልቡ እየዘለለች ሲያወራት ትንፋሹ ቁርጥ ቁርጥ ይላል፡፡ … እንዲያ እንዲያ እያሉ "ኧረ በቃ እንመለስ አንተ" እያለችው ወደ ደኑ መሃል ገቡ፡፡ ሸጥ መዝለል አቅቷት አዝሎ ሲያሻግራት አጎጠጎጤ ጡቶቿ ጀርባው ላይ ሲተከሉና ጭኖቿን በሁለት እጆቹ ሲያቅፈው መላ ሰውነቱን ወረረው፡፡ … ለምለም ሳር ያለበት ዘንድ ሲደርስ ያደናቀፈው በመምሰል ተንገዳግዶ ወደቀና እርሷን ከታች አድርጎ ፍየል እንዳገኘ ነብር ተከመረባት፣ (ገጽ፣ 172)፡፡*

ሰዎች ለሁሉም ነገር የባህላዊ ብቻ ሳይሆን የሞራላዊ እሴት ባለቤት ናቸው፡፡ ይሄን መሰል የስሜት ፈቃዳቸውንም እንዴት ማስተናገድ እንዳለባቸው ከማን ጋር፣ መቼ፣ የትና እንዴት የሚሉ ጉዳዮችን የሚያስቀምጥ ማህበራዊ ስርዓት አላቸው፡፡ ይህ የስንታየው ተግባር ግን ይሄን ሰብዓዊ እሴት የጣሰ፣ ይልቁንም የሚያድናትን ፍየል ያለምንም ርህራሄና ሞራላዊ ግዴታ ይዞ እንደሚበላ ነብር ነው የሆነው፡፡ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ለሁሉ ነገር ቦታና ጊዜ አለው፡፡ እናም እነስንታየው በዚህ መልኩ ከቦታ አኳያ ከከተማ ይልቅ ዱርን፣ ከቤት ይልቅ ጫካን፣ ከአልጋ ይልቅ መስክን መረጠ፣ ከተግባር አኳያም በፍቃድ ላይ ከተመሰረተ ከፍቅር ይልቅ በማስገደድ ላይ የተመሰረተ ጥቃትን መረጠ፡፡ ይህ ሂደት ደግሞ ቀደም ብዬ ከገለጽኩት ሞራላዊ ግዴታን የሚያስጥስ የዝሙት አባዜ ባለፈ የፍትወት ተግባርን ባገኙበት ጊዜ፣ ቦታና ሁኔታ የመፈጸም እንስሳዊ ባህሪን አመላካች ነው፡፡ ይህ ሲሆን ነው እንግዲህ የሰብዓዊነት ልኩ የሚታይ፣ የግብረ ገብ እሴት ፍንገጣውም ፀሐይ የሚመታውና የሰብዕና ደረጃው ለሚዛን የሚቀርበው፡፡

በእነዚህና ሌሎች መመሰያዎች ባህሪው ተገልጸ የምናገኘው የዚህ ልቦለድ ማህበረሰብ "ከተማው ራሱ የተዘጋ ቤት ሽታ አለው፤" (ገጽ፣ 139)፣ ተብሎ እንደተገለጸው፤ ከሰዋዊ ባህሪው ይልቅ እንስሳዊነቱ ጎልቶ የሚታይ ነው፡፡ ምክንያቱም ህዝብ ያለበት ከተማ የተዘጋ ቤት ሽታ ካመጣ ሰው ሰውነቱ እንደጠፋበት፤ አስቦ መስራትና የሰውነት መመሪያውን መፈጸም እንዳቃተው አመላካች ነው፡፡ ይህ ማለት በራሱ ሳይሆን በሌሎች ምሪትና ፍላጎት የሚነዳና የኑሮ መሰረቱ የጠፋበት መንጋ ሆኗል፡፡ ይሄንን የሚያጠናክርልኝን የሚከተለውን ታሪክ ከልቦለዱ ወስጄ ላብቃ፤

> *ኑሮን ኑሮ የሚያሰኙት ጉዳዮች ሁሉ ተናግተውበታል፤ እምነት፣ ዓላማ፣ ማህበራዊ ዋጋ፣ ተግባር፡፡ ለእሱም ብቻ አልመሰል አለው፡፡ ብዙዎቹ የስራ ባልደረቦቹም ሆኑ ሌላው ህዝብ፣ ብዙው የተሰፋ ስሜቱ ተሰልቦ፣ የማስመሰል ኑሮ አንገፍግፎት፣ አልፎ አልፎ ዋስትና ስለሌለው ኑሮው ዋጋ ቢስነት የሚንሾካሾክ ጠባቂ ያጣ መንጋ ሆኖ ታየው፤(ገጽ፣ 79)፡፡*

## 3.1.2. የሰብዓዊነት መንጠፍ ከ"ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" አንጻር

በየሕሊና ባርነት ውስጥ የሰው ልጅ በቁስ ሲመሰልና ሲተካ፣ ህሊናም ለገንዘብና ለጥቅም ሲሸነፍ፣ ማንነት በሰው ልጆች የእጅ ስራ ሲመነዘር፣ ሰብዕና ወርዶ በቁስ ሚዛን ሲለካ፣ የሰው ሰውነት ሲደበዝዝ በእነ እማማ ዛብሽወርቅ፣ ኃይሉ ዓለማየሁና ሌሎችም ይታያል፡፡ ሰው ከሰብዕናው ሲወርድና ሲዋረድ፣ ለሰው ልጅ የእጅ ስራዎች ተገዢ በመሆን እጁ እንዳይሰራ፣ እግሩ እንዳይራመድ፣ አንደበቱ እንዳይናገርና ኃላፊነቱን ጭምር እንዳይወጣ ሲሆን በእነ ስንታየሁ፣ አቶ ደጀኔ፣ ኮሎኔል በትሩና ሌሎችም እናገኘዋለን፡፡ ሰው እንደ ሰው ሳይሆን እንደ ቁስ ለደስታ መፍጠሪያ፣ ለጉዳይ ማስፈጸሚያም ሲውል፤ ይሄንንም አምኖ በመቀበል ራሱንም ለዚሁ ሲያዘጋጅ በእነ ዓለሚቱ ተወክሎ እናስተውላለን፡፡

በእነ ስንታየሁ የጋዜጠኝነት ሙያ ለሙያ ሳይሆን ለጥቅም መስሎ ለማደር ሲውል "...ባይሆን ለደመወዝህ ስራ" (ገጽ፣ 10)፤ "እንደተለመደው ድክመቱን ጥንካሬ፣ ውድቀቱን እድገት፣ ረሃቡን ጥጋብ፣ መጨውን የስቃይ ጊዜ ብሩህ ዘመን አድርገህ መተርተር ነው፤" (ገጽ፣ 15)፤ እየተባባሉ ሙያን ሳይሆን ገንዘብን፣ እውነትን ሳይሆን ሀሰትን፣ ህዝብን ሳይሆን ተሿሚን፣ ለህሊና ሳይሆን ለሆድ፣ ትክክለኛነትን ሳይሆን

መስሎ አዳሪነትን፣ መሰረት ያደረገ ሰብዕናን በቁስ የመለወጥ ጉዞን እናያለን፡፡ እነዚህ ባለሙያዎች የሙያ ግዴታቸውን አልተወጡም፤ ህዝቡ በርካታ ጥያቄዎች እያሉት ጥያቄው ተመልሷል፤ ተርቦ ጠግቧል፤ ተራቁቶ ለብሷል፤ ታስሮ ነጻ ወጥቷል፤ ወዘተ እያሉ በአድር ባይነትና ንዋይ አፍቃሪነት የህዝቡን ጩኸት የሚያፍኑ ናቸው፡፡ “ጋዜጠኞችም ይህን አሳዛኝ የህዝብ ህይወት ለመለወጥ የብዕራቸውን ኃይል ለመጠቀም አልቻሉም፡፡ በፍርሀት፣ መስዋዕትነትን በመሸሽ፣ በአድር ባይነት፣ በአላዋቂነት፣ በአቅም ማነስ ወዘተ. አደጋ የማያስከትለውን እየጻፉ መቀጠልን መርጠዋል፤” (ገጽ፣ 9)፡፡

ይህ በተራኪው ብቻ ተነግሮ አያበቃም፡፡ ይልቁንም የእነርሱ ተግባር ህዝቡን ብቻ ሳይሆን የራስን ሙያና ሰብዓዊ ክብር ያዋረደ፣ ነጻነትንም የገፈፈ፣ ህሊናንም የተፈታተነ ስለመሆኑ ስንታየሁና መሰል የሙያ ባልደረቦቹም ያውቁታል፡፡ “ራስን ሳንሱር ለማድረግ፣ የራስን ብዕር ለማዶልዶም፣ የራስን ነጻነት ገፎ የሌላውንም ለመጨፍለቅ፣ የራስን አንደበት በራስ ማፈን፣ የሚያውቁትን እንደማያውቁ፣ የሰሙትን እንዳልሰሙ ሆኖ ራስን አታሎ ሌላውንም ለማታለል መሞከር፣...” (ገጽ፣ 17)፡፡

እነዚህ ባለሙያዎች ብቻ ሳይሆኑ የበላይ ኃላፊዎቻቸው፣ ሌሎች ሹመኞችና ባላስልጣናት ጭምር ህልውናቸውን የመሰረቱት ለጥቅም ሲሉ ራሳቸውን አዋርደው ሌሎችን ያከበሩ በሚመስል (መስሎ ለመታየት እንጂ ለማክበር ያልሆነ) ለሌሎች ጎንበስ ቀና የሚሉ ናቸው፡፡ የአቶ ደጀኔ፣ “እኔ ልጆቼን ማሳደግ ነው የምፈልገው፤” (ገጽ፣ 53)፤ የኮሎኔል በትሩ፣ “ሆሆ! ወንድሜ በሰላም እንኑርበት እዚሁ ፀሐያችንን እየጠጣን፡፡ ... አንድ እርምጃ ሳትሄድ ነው ተጠልፈህ የምትወድቀው፤” (ገጽ፣ 189)፤ አይነት አባባል በበርካቶቹ የሚደመጥ የራስን ህልውና እንደ ሰው ሆኖ መኖር ሳይሆን ራስን ለጥቅምና አድር ባይነት አስገዝቶ እና እንደ መገልገያ ተቆጥሮ በመኖር ላይ የተመሰረተ ነው፡፡ በዚህ መልኩ ተሸቆጥቁጠው መኖር ከቻሉ፣ የህዝብን ጥቅም አሳልፈው ለሹማምንት ክብር ከሰጡ፣ እውቀት ባይኖራቸውም ይሾማሉ፤ ሁሉን ያገኛሉ፡፡ ለዚህ ደግሞ እንደ አቶ ደጀኔ አይነቶቹ ማሳያ ሲሆኑ፤ “አሁን ያለው በሙያው የማይመካና የበላዮቹ ያሉትን ሁሉ አሜን፣ እሺ የሚል መሆኑ ነው፤” (ገጽ፣ 53)፤ የሚለው የስንታየሁ ትዝብትም ይሄንኑ ግልጽ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

በዚህ መልኩ እዚህ የደረሱ እነዚህ ኃላፊዎች ደግሞ አቅም ሳይኖራቸው ህሊናቸውን ሸጠው ለመሾም መብቃታቸውን ስለሚያውቁ ምንም የማለትና የመናገር ሞራል

የላቸውም፡፡ የራሳቸውን ስብዕና አውርደው ሌሎችን የሚያወርዱና በጥቅም ራሳቸውን የሸጡ ናቸው፡፡ ይልቁንም አንዳች ለመናገር በዳዳቸው ጊዜ የሰው ፊት የሚገርፋቸው፤ ለሚናገሩት የሚሽማቀቁና ፊት ሲነሷቸውም እንደ ህጻን ልጅ ፈርተው ዝም የሚሉ ናቸው፡፡ የስንታየሁ የሥራ ባልደረባ የሆነው ፀጋዬ፣ ከእነ ስንታየሁ ጋር ከሰው ተደብቀው በሚያደርጓት የብሶት ወሬ ሰዓታቸው ወቅት "...አሁን በሚታየው ሁኔታ አንድ ክፍል ውስጥ ስላልተቀለፈብን እንጂ ሁላችንም እስረኞች ነን፡፡ አካላችን፣ መንፈሳችን፣ ሕሊናችን ታስሯል፡፡..."፤(ገጽ፣ 124)፤ ሲል የገለጸውም ለዚህ ይመስላል፡፡ ምክንያቱም እነዚህ ባለሙያዎች ሳይቀሩ በስራቸው አለቆች ያሏቸውን እንጂ ሙያቸው የሚፈቅድላቸውን ለመስራት አይችሉም፤ በስብሰባና በእርስ በርስ መስተጋብር የሃሳብ ልውውጥ ወቅት ሳይቀር የተናገሩት ቃል ምን ያስከትልብን ይሆን ብለው የሚሳቀቁ፣ ከንግግራቸው አንድ ሰው ፊቱን ካጠቆረባቸው ተሸማቅቀው ዝም የሚሉና አንገት የሚደፉ ሆነዋል፡፡ እናም የሚሏቸውን አድርገው፣ የበላዩቻቸውን መስለውና አስመስለው ኑሮን ተላምደዋል፡፡ ሆኖም በዚህ መልኩ ራሳቸውን በመሸንገል የመሰረቱት ኑሮ ማንነታቸውን በጥቅም ስለሸበበው ጊዜያዊ ደስታን እንጂ ዘላቂ እርካታን አላስገኘላቸውም፡፡ ይልቁንም ከስንታየሁ እንደምንረዳው ሰብዓዊነታቸውን አዋርደው መኖራቸው እንዲቆጫቸው፤ ተግባራቸውም እንዲጸጽታቸው አደረገ እንጂ፤

> *አካልን በባርነት አስገዝተው ድንጋይ ሲፈልጡና በጅራፍ ሲላጡ የኖሩ የሰው ልጆች ምንኛ የተሻሉ ናቸው፡፡ የአካልን ባርነት ስንቃወም ... ጭራሽ ለአእምሮ ባርነት ተዳረግን፡፡ ከዚህ የከፋ ለሰው ልጅ ምን ውርደት ሊኖር ይችላል፤ ... የአካል ባርነት የሚያንገሸግሽ ከሆነ የመንፈስና የሕሊና ባርነት... የበለጠ የሚያንገሸግሽ ነው፡፡ ... የሰውን ልጅ ክብር ያዋረደ የፍቅርንም ሞገስ ያኮሰሰ ነውና፤ (ገጽ፣ 18)፡፡*

እነዚህ ለጊዜያዊ ደስታ ራስን ማስገዛት የመረጡ ሰዎች የሙያቸውን ክብር በማዋረዳቸውና ኃላፊነታቸውን መዘንጋታቸው ዘላቂ እርካታቸውን ብቻ አይደለም የተነጠቁት፡፡ ይልቁንም ሰው መሆናቸውን ረስተው ለቁስ አድረው በሰው ላይ ግፍ እንዲፈጽሙ ያደረጓቸውና በጥቅም ያሰሯቸው አካላትም ከሰው አይቆጥሯቸውም፡፡ ከእነርሱ ይልቅ ለቁስ የተሻለ ጥበቃ ያደርጋሉ፤ ዋጋና ክብርም ይሰጣሉ፡፡ ይሄንንም እንደግል ንብረታቸው በሚገለገሉባቸው ጋዜጠኞች ላይ አሳይተዋል፡፡ ህዝብን ያለፈቃዱ ለማስፈር በሚያደርጉት ጥረት ውስጥ የህዝቡን አንደበት መዝጊያ አድርገው ይዘዋቸው የሄዱትን እነ ስንታየሁን፤ በረሃ ውስጥ ተጥለው መቅረታቸው ሳያንስ ችግር

በደረሰባቸው ወቅት እንኳን ያሳሰባቸውና ያስጨነቃቸው የጋዜጠኞቹ ደህንነት ሳይሆን ጋዜጠኞቹ ለያዟቸው እቃ(ለፎቶና ቪዲዮ ካሜራዎች) እንደነበር ማየቱ በቂ ነው፡፡

> *‹ ... ከመኪና ተገልብጠን ሾፌሩ ሞተ እኛም ተጎድተናልና መኪና ላኩልን እለዋለሁ፣ ካሜራው ተርፏል ወይ አይለኝ መሰለህ፡፡ በቃ ከእኛ ይልቅ እነዚህ ሰዎች ለዕቃቸው ነው የሚያስቡት ማለት ነው፡፡›*

> *‹ምን ታደርገዋለህ! ለጊዜው በአገራችን ከሁሉም ነገር ረክሶ የሚታያቸው ሰው ነው፡፡ ማንኛውም ነገር ከሰው በኋላ የመጣና ሰው የሰራው መሆኑን ረስተዋል፡፡ ለእነርሱ የመጨረሻው ርካሽ ነገር ሰው ነው፡፡ ለሰው ልጅ ከፍተኛውን ከበሬታ እስካልሰጡ ድረስ ደግሞ የሚያዋርዱት ራሳቸውን ነው፡፡ ... ›*

> *‹ወይ ጉድ! እስካለን ተጠቅመውብን እንደ አገዳ መጠው መጣል ነው የሚያውቁበት? ምን ያድርጉ እኛም ወኔ ቢሶች ነን፡፡ ... › (ገጽ፣ 119-120)፡፡*

በዚህ መልኩ የምንመለከተው የሙያ ኃላፊነትን ለራስ ጥቅም አሳልፎ የመስጠትና ስብዕናን የመለወጥ ችግር በእነስንታየሁ የተወከሉ የመገናኛ ብዙሃን ባለሙያዎችና ኃላፊዎች ብቻ ተወስኖ የሚቀር አይደለም፡፡ ይልቁንም የአገርን ደህንነት ይጠብቃሉ የተባሉ የሰራዊት አባላትና ኃላፊዎችም ዘንድ ዘለቀ እንጂ፡፡ ሰራዊቱ ለአገሩ ሕይወቱን አሳልፎ ለመስጠት የተዘጋጀ ብቻ ሳይሆን ሂንኑ የሚያደርግ ነው፡፡ በአንጻሩ ለራስ ጥቅም ሲሉ አገርና ህዝብን አሳልፈው የሚሰጡ፣ ለገንዘብ የሰውን ህልውና አደጋ ውስጥ የጣሉ መኖራቸውንም በስንታየሁ ወሬ አውጣጪነት፤ በኮሎኔል በትሩ ምስጢር አውጪነት አይተናል፡፡ እነዚህ የሰራዊት አመራሮች ሰብዓዊነታቸውን ሽጠው ለአገር ሳይሆን የራስ ጥቅም ማስቀደማቸውን ትንሽ በሚመስል ነገር ግን በሰራዊቱ ውስጥ መከፋፈልና ቁርሾን ፈጥሮ ትልቅ አደጋ ሊያደርስ በሚችል መልኩ የጀመሩት ተግባር ወደ ገንዘብ ሰረቃ ያድጋል፡፡ ሰራዊቱ የሚዋጋበትን ጥይትና መሳሪያ መሸጥ፤ አልፎ ተርፎም የሚበላውን ማጉደል ይጀምራሉ፡፡

> *... አሁንማ የሚገርምህ ለአገሩ ክብር ለመስዋዕት የተሰለፈው ይህ ሰራዊት የደንብ ልብስ እንኳን በወቅቱ አያገኝም፡፡ ገንዘቡ ወጪ መሆኑ ላይቀር ባለሥልጣኖቹ ይበሉታል መሰለኝ ለሶስት ዓመት ያለቅያሪ በተጣጣፈ ሱሪ ነው የሚዋጋው፡፡ ... አገር ሳይሆን ቦሌ የሚሰራውን ቤቱን የሚያሰላስል ነው፡፡ ... ወገን ለወገን እንኳን መተዛዘን ትቷል፡፡ ... ለመስዋዕትነቱ ትርጉም አጥቶለታል፡፡" (ገጽ፣ 188-92)፡፡*

ይህ እጅጉን ኃላፊነትን መዘንጋት፣ አገርና ህዝብን መክዳትና ለጠላት አሳልፎ መስጠት ብቻ ሳይሆን፤ ማንነትን አውርዶ ከትቢያ መቀላቀል ነው፡፡ የዚህን ሰብዓዊነትን አዋርዶና ህልውናን በጥቅም አሳልፎ መስጠት በሰራዊቱ ውስጥ ቅሬታን፤ ምን አገባኝ ባይነትን፤ አለመተሳሰብና አለመረዳዳትን አስርጾ እናገኘዋለን፡፡

በዚህ መልኩ በእነስንታየሁም ሆነ በእነ ኮሎኔል በትሩ ዘንድ የሚነሱ የሰብዓዊነት ጥያቄዎች፤ በእነ ወይዘሮ ዛብሽወርቅ እና በእነ ኃይሉ ዓለማየሁ ስብዕናም የሚገለጹ ናቸው፡፡ ወይዘሮ ዛብሽ ወርቅ ከዓለሚቱ በሚያገኟት ሽራፊ ሳንቲም ወሬ ለማቀበል ተገዝተው እድሜ የሰጣቸውን ክብር ከአፈር ደባልቀውታል፡፡ የአዛውንትነት ክብራቸውን ለሰዎች ፍርቅና አብሮነት ከማዋል ይልቅ ወሬ በማመላለስ ለጠብና ለማቆራረጥ በማዋላቸውም፤ የካሳንችስ ሊስትሮዎችና የሆቴል ቤቶች አስተናጋጆች መጠቋቆሚያና መሳቂያ እስከመሆን ስብዕናቸውን ገፍተዋል፤ አዋርደዋልም፡፡

> *ወይዘሮ ዛብሽ መሸረፈታቸውን እንደያዙ ካሳንቺስ ቶታል ያለውን የሕዝብ ስልክ ይደውላሉ፡፡... "...አሁን ዋናው ነገር ያ ያንቺ ሰውና እሷ ተከታትለው ሲወጡ፣ እኔ እናትሽ ቀስ ብዬ እያደባሁ ከእሷ ኋላ ሳዘግም፣ ይኸውልሽ ለምን አደዋ ሆቴል አትገባ መሰለሽ"፤ ...መንገደኛውና መሀል ካሳንችስ የቡና ቤት ሰራተኞች በሙሉ መጨረሻቸውን ለማየት በመጓጓትም አፋቸውን ከፍተው ቆመዋል፡፡ መስኮት ተሰበረ፣ በር ተበረቀሰ፤ ተመልካቹ ተጨነቀ፤ ውስጥ ውጪው ታመሰ፤ ብዙ ደቂቃዎች አለፉ፤ አንድም የተገኘ ነገር የለም፡፡ ...ወይዘሮ ዛብሽ ኩምሽሽ አሉ፤ እንዳልሆነ ገባቸው፤ ቃል አልተነፈሱም፤ አለባበሳቸውና መሸረፈታቸውን ያስተዋሉት አሁን ነው፡፡ እዚያ ሰው ሁሉ ፊት ራቁታቸውን የቆሙ መሰላቸው፤(ገጽ፣ 71)፡፡*

በዚህ ታሪክ ውስጥ ወይዘሮ ዛብሽወርቅ ራቁታቸውን የቆሙ መስሎ እንደተሰማቸው ተራኪው ይነግረናል፡፡ ወይዘሮዋ ልብስ መልበሳቸውን እያወቀ ለምን "ራቁታቸውን የቆሙ መሰላቸው" ሲል ገለጸ? የሚለውን መመልከት ተገቢ ነው፡፡ በማህበረሰቡ ባህል እንደ ወይዘሮ ዛብሽ ወርቅ ያሉ ባልቴቶች በልብስነት ከሚደረብ የጨርቅ ካባ በህብረተሰቡ ዘንድ የሚሰጣቸው የክብር ስምና ካባ አለ፡፡ ይህ የክብር ካባ ግን በቦታውና በሰዓቱ ሲሆን እንጂ አይደምቅም፤ ገመናንም አይሸፍንም፡፡ ወይዘሮዋም መሸረፈታቸውን ይዘው የተገኙበት ስፍራ ብቻ ሳይሆን ሁኔታ ጭምር በህብረሰተቡ የተሰጣቸውን ካባ የሚያስደርብ ሳይሆን የሚያስወልቅ ነው፡፡ ለገንዘብ ብለው በፈጸሙት የወሬ አቀባይነት ተግባር ብቻ ሳይሆን የወሬውም ፍሬ ቢስነት

አሳፍሯቸዋል፡፡ ከብቦ በሚመለከታቸው ህዝብ መሃልም አቅልሎ አሳይቷቸዋል፡፡ የምግባራቸውን ፍሬ ቢስነት ሲገነዘቡም ከማህበራዊ ደረጃቸው፣ ከባህሉ የክብር ቦታቸው እንደወረዱ አወቁ፡፡ የትልቅነት ካባቸውን እንዳወረዱ ሲረዱትም ነው ራቁታቸውን የቆሙ የመሰላቸው፡፡ ራሳቸውን ለገንዘብ ማስገዛታቸውም ሰብዓዊ ክብራቸውን አሳጣቸው፤ የግብረ ገብ እሴታቸውን ነጠቃቸው፤ በክብር ካባቸው ፈንታም የሀፍረት ሸማ አልብሶ ራቁታቸውን አቆማቸው፡፡

ከዚሁ ከእነ ወይዘሮ ዛብሽወርቅ ማህበረሰብ የወጣው ኃይሉ ዓለማየሁ በተመሳሳይ ለገንዘብ ፍቅር ማንነቱን ሲያዋርድና ለቁሳቁስ ስብዕናውን ዝቅ ሲያደርግ ይታያል፡፡ ከስንታየሁ ጋር ጀርመን ለስልጠና የተላከው ኃይሉ፣ ከጉዞው ሲመለስ በአየር መንገድ ጣቢያው ያሳየው ባህሪ ለእውቀት ግድ የሌለው መሆንኑን ብቻ ሳይሆን፤ ለሰብዓዊ ክብሩ የማይጨነቅ መሆኑም በተግባር የተገለጸበት ነበር፡፡

> *የኃይሉ ሻንጣ ቀደም ሲል ከሃያ ኪሎ በላይ ስለመዘነ ዕቃውን ቀንሰው እንዳያስቀሩበት በመስጋት ደራርቦ ለብሶ ቁም ሳጥን ሆኗል፡፡ በዚያ በፈረንጅ ቢጋ በላብ እየታጠበ ሊያስመዝን ተጠጋ፡፡ እንደፈራው ሻንጣው ሲመዘን ሃያ ሶስት ኪሎ ሆነ፡፡ ‹በል የሶስት ኪሎ ዋጋ በዶላር ክፈል አለዚያ ዕቃ ቀንስ› አለችው መዛኝዋ፡፡ ኧረ በናትሽ ማለት ነው የቀረው፡፡ …ላቡ እያየለ ከሻወር የወጣ መሰለ፡፡ ፈረንጆች ደራርቦ የለበሳቸውን ሸሚዞች ሹራቦች፣ ካፖርቱን እያስተዋሉ በጀርመንኛ እየተቹት ይሳሳቃሉ፡፡ …ሊሸኟቸው የመጡት መምህራንና ሾፌሩም ለብቻ ቆመው ይስቃሉ፡፡ …ታላቁ ማርክሲስት ካድሬ የማርክስና የሌኒን መጻሕፍትን እያወጣ በወለሉ ላይ ያሽቀነጥራቸው ገባ፡፡ …መዛኞቹ "ይህን ነው ይዘህ የምትሄደው" አሉና ሁሉም ሳቁበት፤ (ገጽ፣ 158-159)፡፡*

ከታሪኩ እንደምንረዳው፣ ኃይሉ ከእውቀት ይልቅ አላቂ እቃን መርጧል፡፡ እውቀት ገብይቶ የተሻለ ስራ በመስራት ከፍ ማለትን ዘንግቶ፤ ጊዜያዊ ውበት በሚሰጡ ልብሶች ደምቆ ለመታየት ሲል በባዕድ አገር ራሱን አዋርዷል፡፡ ለእቃ ብሎ ማንነቱን ዝቅ አድርጓል፡፡ የኃይሉ የሞራል ጥያቄ አውቆ መገኘት ሳይሆን ለብሶ ማማር፤ አይሆኑትን ሆኖና ራስን ዝቅ አድርጎ እነዚህን ቁሶች ማግኘት ነው፡፡

በዚህ ልቦለድ የሚስተዋለው የሰብዓዊነት መንጠፍ ለቁስ ራስን አስገዝቶ ዝቅ ማለትን ብቻ ሳይሆን ሰዎችን እንደ ቁስ ቆጥሮ በእነርሱ አካል የመገልገል፤ ደስታን የመፈለግ፣ እንዲሁም ራስን እንደ እቃ ቆጥሮ እስከ ማቅረብ የሚገለጽ ነው፡፡ በዚህ ረገድ በተለይ ሴቶች ወንድን ለማገልገልና ለማስደሰት የተፈጠሩ ሆነው ይታሰባሉ፡፡ እነርሱም

ይሄንኑ አምነው በዚሁ ልክ ራሳቸውን ያቀርባሉ፡፡ ይህ የግብረገብ እሴት የተለየው ምክባርም በእነ ስንታየሁ የሴቶችን መልክና ቁመና እየተመለከቱ ከመመዘንና የልብ እርካታን ለማግኘት ገበያ ወጥቶ የተሻለ እቃን መርጦ እንደመግዛት ያክል ሴቶች በመንገድ ሲሄዱ ጭምር ከማማረጥና ለጊዜያዊ ደስታ ከመመኘት ይጀምራል፡፡ ይሄንንም ሁሉን አወቅ የሆነው የልቦለዱ ተራኪ እንዲህ ይነግረናል፤

> *መቼም የተቃራኒ ጾታ ጉዳይ አይሆንለትምና ቀሚስ እንደ ማግኔት ዓይኑን እየነጠቀው አንዷን ከሌላዋ ያነጻጽር ጀመር፡፡*
>
> *በስመአብ! እንዴት ቀጭን ናት፡፡*
> *ደሃ ጨካኝ ነው፣ ይህንንም እግር ብላ ትሄድበታለች፡፡*
> *ይቺ ይልቅ ሎጋ ናት፣ ጎሽ! ምርጥ ዘር፡፡*
> *የማን ናት ድውይ? የምድር ጉድ፡፡*
> *እንዴ! አጎዛ የመሰለች ፍጥረት ደግሞ ከየት መጣች?*
> *ያቺ ደህና ናት ከኋላዋ፣ እስቲ ዘወር! አዎ፣ መልኳም ምንም አይል፡፡*
> *አቤት ጥቁረት! በምን ቢቆሏት ነው ጃል እንደዚህ ያረረችው፡፡*
> *አይ! ይቺ ቂጧና ቦርጯ በዛ፤ ሸረሪት የመሰለች ጉድ፡፡*
> *ያቺ ጡቷ ትንሽ ቢሆንም ሎጋ ናት፡፡*
> *ውይ! ይቺ ደግሞ የማናት ጥርብ ቂጥ?*
> *አሃሃ! ይልቁን ይችን የምታልፍበትን ሰዓት ጠብቆ በሥልት መቅረብና .... (ገጽ፣ 28)፡፡*

በዚህ መልኩ ሴቶችን እንደ እቃ በተናጥላዊ የሰውነት አካላቸው ግዝፈትና ቀለም እየለኩ ማየት ሴቶችን ከሰውነት ጎራ የማራቅ ተግባር ብቻ ሳይሆን ራስንም በዛው ሚዛን የሚያስገባ ነው፡፡ የወንዶች በዚህ መልኩ መውረድና ሴቶችን የማዋረድ ተግባር በማማረጥና በመመኘት ብቻ አያበቃም፤ ይልቁኑ ሴቶችን የማይታመኑ አድርጎ በመቅረጽ በትዳር ዓለም ያሉትን ጭምር ወንዶቹ እንደሚሉት “ተካፍሎ ለመብላት” የሚደርስ ሀሳብና ተግባር እንጂ፡፡ “ሴቶች ለብር የሚይዙትና ለክብር የሚወሽሙት፣ ለፍቅር ከሚቀርቡት ይለያል፡፡ ነጋዴ ለብር፣ ደርግ አባል ለክብር፣ ፔቲ ለፍቅር ሲሉ አልሰማህም? እኔ ልቧ ላይ ዙፋኔን ተክዬ ጉብ ካልሁ፣ አካሏ ላይ ማንስ ቢጨፍር ምንተዳዬ፤”(ገጽ፣ 90)፤ በሚል የተገለጸውም ይሄንኑ የሚያጠናክርልኝ ነው፡፡ በተመሳሳይ፣ “‹ሴትና ኮርቻ እንደሆን ከአንድ አይለምድም ይባላል፡፡ ታድያ ስንት ቀን ተጠብቆ ይዘለቃል፡፡ ያው ተካፍሎ ለመብላት መፍቀድ ነው እንጂ፡፡› ሲል አሰበ፤” (ገጽ፣ 85)፤ ከሚለው የተራኪው ገለጻ መረዳት የሚቻለውም፤ ሴትን ልጅ ፈረስ ወይም በቅሎ ላይ ተጭኖ ሁሉም ከሚሳፈርበት ኮርቻ ጋር እስከማነጻጸር የደረሰ ነው፡፡ ይሄም

ሴትን ልጅ እጅጉን ለሰብዓዊነቷ፣ ሰብዓዊ ግብሯና ክብሯ ቦታ መንፈግ ነው፡፡ ተፈጥሯዊ ማንነቷ፣ ማህበራዊ የሞራል እሴት ያጎናጸፋትን ሆና እንዳትኖር ቁንጅናዋን ምክንያት በማድረግ እንደ ቅርጫ ስጋ አንዷን ለብዙ ለመቀራመት የመመኘት ከሰብዓዊ ተግባር የወጣ የሰብዓዊነታቸው መንጠፍ መከሰቻም ነው፡፡

ወንዶቹ ሴቶቹን ሲርባቸው እንደ ረሃብ ማስታገሻ፣ ደስታ ሲርቃቸው እንደ ደስታ መፍጠሪያ፣ ሀሳብ ሲበዛባቸው እንደ መደበቂያ፣ ሲደክማቸው እንደ ማነቃቂያ፣ ወዘተ. ይጠቀሙባቸዋል፡፡

> *... እንደእናንተ አይነቱማ በሥራ የደከመ አዕምሮን ያድሳል እንጂ መች ቅር ያሰኛል ብለሽ ነው፡፡ ብቻ አንተ በዚኝ አንቱታ የሚያስፈልገኝ አይደለሁም፤ (ገጽ፣ 74)፤*
>
> *ወደቡ አከባቢ ያሉ መጠጥ ቤቶችን እያሰሱና ሴተኛ አዳሪዎችን እየዳሰሱ፣ አልኮል እየጨለጡ ሲጋራም እየሞካከሩ፤...(ገጽ፣ 194)፤*
>
> *መርከባቸውን በወደብ ያስጠጉ የልዩ ልዩ አገር መርከበኞችና የአገሪቱ ልጆች ከአዳናሽ ሴቶች ጋር ይወዛወዛሉ፤(ገጽ፣ 195)፤*
>
> *ጭንቀቱን ለማቃለል ሲል የቀድሞ ወዳጁ ከሆነችው ትብለጽ አርአያ ጋር እየተገናኘ በመደሰት ላይ አተኮረ፡፡ (ገጽ፣ 196)፤*
>
> *"በዚህ ዓለም ላይ ሙዚቃ፣ ቢራና ጥሩ ሴቶች ባይኖሩ ሕይወት ምንኛ ጣዕም ባጣች" አለ በሀሳቡ፤ (ገጽ፣ 216)፡፡*

በወንዶች በዚህ መልኩ የሚታዩ ሴቶችም፤ ይሄን አካሄድ ከመቃወም፣ ይልቅ ይሄንኑ አምነው በዛው መስመር ሲሄዱ ይታያል፡፡ ለዚህ አብይ ማሳያዋ ደግሞ ዓለሚቱ ስትሆን፤ ለዚህም ተራኪው "... እንዲደሰትበት የፈቀደችለትን ሴትነትዋን እንዲንገላታበት ልትጠቀምበት ወስናለች፤" (ገጽ፣ 70)፤ ሲል የገለጸበትን ማጤን ተገቢ ነው፡፡ ይህ ማለት ምን ማለት ነው? ዓለሚቱስ ለምን ይሄን መንገድ መረጠች? የሚሉ ጥያቄዎችን ለመመለስ መሞከሩ ደግሞ የግብረ ገብ እሴቶችን መቃወስ በሁሉም አቅጣጫ ለመመልከት የሚያስችል ነው፡፡ ወደዚህ ከመሄዴ በፊት ግን፣ "ዛሬ ጊዜ በሴት፣ በገንዘብና በዘመድ የማይሰራ የለም፤" (ገጽ፣ 62)፤ ተብሎ የተገለጸውን ለመመልከት ልሞክር፡፡ በዚህ ውስጥ ልብ ሊባሉ የሚገባባቸው "ገንዘብ" እና "ሴት" የሚሉት ሁለት በንጽጽር የቀረቡ ቃላት ናቸው፡፡ ገንዘብ የሚያጓጓና ሁሉም የሚመኘው፤ ተመኝቶም የሚያገኘውና የሚገለገልበት መገበያያ ነው፡፡ በዛው መጠን

በወጉ ከያዙት የሚወደድ፤ በስርዓቱ ካልተጠቀሙበትም የሚባክን ነው፡፡ በአንጻሩ ሴት ልጅ በተፈጥሮ ክብርን የታደለች፤ ግብረገባዊ እሴቶችን ጠብቃ የምትገዝ ናት፡፡ ይሁን እንጂ በታሪኩ ሴት ልጅ ከገንዘብ እኩል ተገልጻለች፡፡ ሰው መሆኗ ተዘንግቶም ለጉዳይ ማስፈጸሚያ ውላለች፡፡

በዚህ መልኩ ሴቶችን መመልከቱ የሰብዕናን አጥር ያፈረሰ ተግባር ቢሆንም፤ እንደ ዓለሚቱ አይነቶቹ ግን ንጽጽሩ የሚገልጻቸው ሆነው ቀርበዋል፡፡ ዓለሚቱ፣ የምትፈልገውን ነገር ለማግኘት እንደ አስፈላጊነቱ ገንዘቧን ወይም ሴትነቷን ለጉዳይ ማስፈጸሚያነት ታውላለች፡፡ ሥራ ለመቀጠር ገላዋን ለተለያዩ ሹማምንት እንደ ጉቦ አቅርባለች፤ ስለ ስንታየሁ መረጃን ለማግኘት ለወይዘሮ ዛብሽወርቅ ገንዘቧን ሰጥታለች፡፡ ዛሬ ደግሞ ወዳጇ ስንታየሁን ለመበቀል ለደስታው አቅርባለት የነበረውን ገላዋን እንዲሰቃይበት ለማድረግ እርሱን ይበቀሉልኛል ላለቻቸው ባላስልጣናት አዘጋጅታዋለች፤ አጋርታቸዋለችም፡፡

> *ዓለሚቱ የሄራውን ቀጣይ አንጓ ለማሰር ተጊያጊጣ ወደ ከፍተኛ 15 አብዮት ጥበቃ ሊቀመንበር ሃምሳ አለቃ አርጋው ተክሌ ቢሮ ሄደችና ታሽከረምመው ጀመር፡፡ ልቡ እንደማለለላት ስታይ፣ ...ምስጢሯን ገለጸችለት፡፡ በፈለገው ጊዜ በራትም ሆነ በቢራ ልታጅበው እንደምትችል በማሽኮርመም አይነት፣ "ለማንኛውም ከአሥር በኋላ ቤት ነኝ ደውልልኝና እናወራለን"፣ በማለት የስልክ ቁጥሯን አስመዝግባው፣ እርምጃዋን አሳምራ ስሜቱን ለመሳብ ደላላዋን(ዳሌዋን-ለማለት ይመስለኛል) እያወዛወዘች ዓይኑን አስከትላ ሄደች፡፡ የዓለሚቱ ውበት ከቡና ቤት አካባቢ የራቀ ጀብዱ ሰርቶ ለማያውቀው ሃምሳ አለቃ ተጽዕኖ አሳደረበት፡፡ እሺ ካለችው ገደል ግባም ብትለው ላያመነታ ወሰነ፤ (ገጽ፣ 70)፡፡*

ይህ የዓለሚቱ ሃሳብና ምግባር ፍጹም የሰብዕናን ወሰን ያለፈ፤ ወደ ቁስነት ተርታ ራሷን ያወረደ ነው፡፡ በዚህ ሁነት ውስጥ ሁለት ነገሮችን ማየት እንችላለን፡፡ አንደኛው ዓለሚቱ ራሷን እንደ ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቁስ አድርጋ መቀበሏን ሲሆን፤ ሁለተኛው ሃምሳ አለቃውም በዛው ልክ ገምቶ(አስቦ) እርሷን መቀበሉ ነው፡፡ ሁለቱም ሰዎች አንዳቸው አንዳቸውን እንደተጠቀሙባቸው ያስባሉ፤ እሷ በእሱ እንደተጠቀመች ስታስብ እሱም በበኩሉ በእርሷ እንደተጠቀመ ያስባል፡፡ በሁለቱም በኩል የድል አድራጊነትና የአሸናፊነት ስሜት ይንጸባረቃል፡፡ ምክንያቱም እሷ ሴትነቷንና ውበቷን ተጠቅማ ባደረገችው የማማለል ሙከራ በእርግጥም ሙሉ ትኩረት እንዳገኘች

ተረድታለች፡፡ እርሱም የምትፈልገውን ለማሳካት በእርሱ ጋ ማለፍ እንዳለባት አምና ለዚህም በጉዳይ ማስፈጸሚያነት ገላዋን ማቅረቧን፤ ለሚፈጸምላት ጉዳይ በወረታነት ሴትነቷን ማጨቷን ስለተረዳ አሳይታው ያስጎመዠችውንና የተመኘውን ገላ እንደሚያገኝ ተማምኗል፡፡ ይሁን እንጂ ሁለቱም ሰብዓዊ ማዕረጋቸውን አጥተዋል፤ የግብረገብ እሴት ርቋቸዋል፡፡ ሴትነትን ከገንዘብ እኩል ሚዛን ላይ አስቀምጠው ተመልክተዋል፤ በዛው ልክ ጥቅም ላይም አውለዋል፡፡ እሷ እሷነቷን ወረታ ለማቅረብ ስትስማማ፤ እርሱም እሷን በእጅ መንሻ መልኩ ገላዋን ሲጋራ ሁለቱም ከሰብዓዊነት ተርታ ርቀዋል፡፡ የሞራል እሴታቸው ጠፍቷል፤ ሰብአዊነታቸው ነጥፏል፡፡

እዚህ ጋ ቀደም ሲል፣ "በዚህ ዓለም ላይ ሙዚቃ፣ ቢራና ጥሩ ሴቶች ባይኖሩ ሕይወት ምንኛ ጣዕም ባጣች"፤ ሲል ስንታየው የተናገረውን ቃል ከታሪኩ ወስዶ መመልከቱ ተገቢ ይመስለኛል፡፡ ምክንያቱም ሴቶች ያውም "ጥሩ" የተባሉቱ የቀረቡበትን መንገድ ማጤን አስፈላጊ ሆኖ ስላገኘሁት ነው፡፡ በዚህ ንግግር ሴት ልጅ አንደኛ፣ ከሙዚቃ ጋር ተነጻጽራ ቀርባለች፡፡ ይህን ከተነገረበት አውድ አንጻር መመልከቱም ተገቢ ነው፡፡ ሙዚቃ የሰው ልጅ ሀሴት መፍጠሪያ፣ አዕምሮ ማደሻና የመንፈስ እርካታ ማግኛ ጥበብ ናት፡፡ ሆኖም እሱ ያነሳው ሙዚቃ በጋራ የሚጨፈርበትን የሆይሆይታ ስፍራ ነው፡፡ በዚህ ቦታ የሚደመጥ ሙዚቃ ሁሉም በጋርዮሽ የሚያዳምጠው፤ በጋራም የሚደሰትበት እና በማስተዋል ሳይሆን በደመነፍስ እንደ አቅምና ችሎታውም የሚጨፍርበት የጋራ ንብረት ነው፡፡ ሴትን በዚህ ሙዚቃ ሲገልጻት ደግሞ ቀደም ሲል "ሴትና ኮርቻ" እንዳለዉ ሴት የጋራ ንብረትና መደሰቻ ናት የሚለውን አስተሳሰብ ያዘለ ፍጹም የግብረገብ እሴት የጎደለው ነው፡፡ በሁለተኘነት ቆንጆ ሴት ተነጻጽራ የቀረበችው ከቢራ ጋር ነው፡፡ ቢራ አንደኛ ለመዝናኛነት፣ ሁለተኛ ራስን ለመሸሸጊያነት የሚጎነጩት ነው፡፡ ለመዝናኛነትም ሆነ ለመሸሸጊያነት የሚጠጣው ይህ ቢራ አዕምሮን ማሳቱና በየሜዳው በሽንት መወገዱ የማይቀር ነው፡፡ ሴት ልጅን በዚህ መልኩ ተጠጥቶ ህሊናን ከሚያስት፣ በየጎዳናው ተሸንቶ በቆሻሻነቱ አፍንጫን ከሚያስይዝ ቢራ ጋር ማነጻጸሩም ሴትን ልጅ ማዋረድ ብቻ ሳይሆን የትም ቦታ እንደሚጣል ቆሻሻ አድርጎ ማሰብ ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሴትን ብቻ ሳይሆን የራስን ሰብዓዊ ማንነት የሚያጎድፍ፣ የስብዕናን ጉድለት ቁልጭ አድርጎ የሚያሳይ ነው፡፡

ቀደም ብዬ ባነሳኋቸው የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻዎች (በአኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን እና ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን) አንጻር ለማሳየት እንደሞከርኩት በዚህ ልቦለድ ውስጥ፣ ሰው እንደ ሰው የተገለጸበትን ማንነት ለቅቆ የእንስሳትን ባህሪ ተላብሷል፤ ሰው ለራሱ ቁሳዊ ሃብቶች ተገዝቷል፤ ራሱንም በዛው ልክ አቅርቧል፡፡ የማህበራዊ እሴቶቹን ገፍቶ፣ የሞራል ግዴታዎቹን ጨፍልቆና ሰብዓዊ ክብሩን አዋርዶ ከሰብዓዊነት ተርታ ወጥቷል፡፡

> *…የእኛ ሕብረተሰብ ባህርይ ግራ ያጋባኛል፡፡ በጋራ ጉዳዮች ላይ ቸልተኛ እየሆነ መጥቷል፡፡ ለግል ጥቅም ግን አንዱ ሌላውን አስጠልፎ ለመረማመድ ይሉኝታውን ሽጦ የሚራወጥ ብዙ ነው፡፡ …ይሉኝታ፣ እግዚአብሔርን ፈርቶ ክፉ አለመስራት፣ አሳ ባይነት፣ መተሳሰብ፣ ታላቆችን ማክበር ይህ ህብረተሰብ የሚደነቅባቸው ባህሪያት ነበሩ፡፡ አሁን ግን እንዲያ አይደለም፡፡ …የአስተሳሰብ መዋዠቅና የሞራል ግዴታዎች መኮሰስ፣ ህብረተሰቡ ዋጋ የሚሰጣቸው ቁም ነገሮች ቸል መባል በሰፊው ይታያል፡፡ …የሕሊና ዳኝነት ኮስምኗል፡፡ የኃላፊነት ስሜት ቀዝቅዟል፡፡ የአገር ፍቅር፣ የዓላማ ጽናት፣ የብሔራዊ ጀግንነት ስሜት ቁሳዊ መሰረቱ ተቦርቡሯል፡፡ ጀግናውና ፈሪው፣ ክፉውና ደጉ፣ ሐቀኛውና ሸፍጠኛው መሳ ለመሳ እየሆነ መጥቷል፡፡ …የኑሮ እድገት በስብቅናና በሸፍጥ ሰለሆነ እውነትና ተግባር ደብዛው እየጠፋ ነው፡፡…"፣ (ገጽ፣ 212-213)፡፡*

ይህን መሰል ሰብዓዊ ምስቅልቅል መፈጠሩ፣ ሰው ለሰው አለኝታና ምስጢረኛ መሆኑ አልሆን ቢለው ነው፣ ስንታየው ከሰው ይልቅ ማስታወሻ ደብተሩን የልብ ጓደኛው ማድረጉ፡፡ በልቦለዱ (ገጽ፣ 11) ላይ እንደምናገኘው፤ ለስንታየሁ የቀረችው የሁልጊዜ ጓደኛና ምስጢረኛው ማስታወሻ ደብተሩ ናት፡፡ ለህዝብ መግለጥ የማይችለውን ሁሉ የሚያካፍላት፤ የሚሰማውን የልቡን ትኩሳት ሁሉ የሚያሰፍርባት ይህችው ማስታወሻው ናት፡፡ በእርሷ ውስጥ ሲጫጭር ስሜቱን የተወጣ እየመሰለው ቀለል ይለዋል፤ ደህንነትም ይሰማዋል፡፡ ምክንያቱም ይህች ግዑዝ ነገር የጻፈባትን ይዛ ባስቀመጣት ትገኛለች እንጂ ምስጢሩን ለማባከን በጥቅመኞች አትደለልም፤ ማስተዋል የጎደላት ህሊናቢስ ሆናም አሳልፋ አትሰጠውም፡፡ እናም በዚህ ልቦለድ የቀረቡት ገጸ ባህሪያት ይህን መሰል ሰብአዊና ግብረ ገባዊ እቴቶች የጎደሏቸው፤ ብዙ ሰብዓዊ እሳቤዎችና ግብሮችም የራራቋቸው ብቻ ሳይሆኑ፤ የነጠፉባቸውም ናቸው፡፡

# 4. ማጠቃለያ

ይህ ጥናት የሰብዓዊነት መንጠፍ በየሕሊና ባርነት ውስጥ ከሞራል ፍልስፍና አንጻር እንደምን እንደተከሰተ ለማየት ሙከራ የተደረገበት ነው፡፡ ይሄን ለመመልከትም የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ናቸው በሚል የተለያዩ ባለሙያዎች ከገለጿቸው ከ"አኒማልስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" እና ከ"ሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን" ጽንሰ ሀሳቦች አንጻር ብቻ በመወሰን ተከናውኗል፡፡ በዚህም ደራሲ ነቢዩ ኢያሱ በልቦለዱ ውስጥ የሰው ልጆችን ስብዕና ከሞራል ፍልስፍና አኳያ የሰው ልጆችን ባህርይ በእጅጉ የገለጸበት መሆኑን ለማየት ተችሏል፡፡ የሰብዓዊነት መንጠፍም በእነዚሁ የግብረ ገብ እሴቶች እየተመዘነ የስብዕና ጉዳይ የተለየበት፣ የሰው ልጅ እንስሳዊም ሆነ ቁሳዊ ልኬቱ እንደየመመሰያ ባህርዩ ተሰናስሎ የቀረበበት ነው፡፡

ልቦለዱ እንደ ክፋትና ደግነት፣ ፍርሃትና ጀግንነት፣ እውቀትና ድንቁርና፣ በቀለኛነትና ይቅር ባይነት፣ ራስ ወዳድነትና እኛ ባይነት፣ ክብርና ውርደት፣ ረሃብና ጥጋብ፣ ሕይወትና ሞት፣ አይነት በሁለት ጽንፍ ያሉ ሁነቶች በጉልህ የታዩበትና እርስ በእርሳቸው ተሳስረው የቀረቡበት ነው፡፡ የእነዚህ በአንጻርነት የቆሙ ሁነቶች በዚህ መልኩ መቅረብ ደግሞ ደራሲው በልቦለዱ የስብዕናን ጥግ እንድንመለከት፣ በተይዩነት በመመልከትም የግብረገባዊ እሴቶች እንዴት እንደተዘነጉና እንደተጣሱ ለመፈተሽ፣ የሰብዓዊነት መንጠፍ አከሳሰትን እንድንመረምርም በከፈቱት በር በመዝለቅ በተደረገው ትንተና በልቦለዱ ያሉ ገጸ ባሕሪያት አንድም የስብዕና ባህርያቸው በእንስሳዊ ገጽታው የሚገለጽ፣ አንድም በእቃ(ቁስ) ሲወከልና ሲመዘን ታይቷል፡፡

የሰብዓዊነት መንጠፍን ከአኒማሊስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን አኳያ ልቦለዱን ለመመርመር በተደረገው ጥረት፣ የሰው ልጆች እንደምን ሰዋዊ መገለጫቸው በእንስሳዊ ባህርይ ተወከለ የሚለውን ለመመለከት ተሞክሯል፡፡ በዚህም የልቦለዱ ገጸ ባሕሪያት የሰብዓዊነት እሴቶቻቸውን ቸል ብለው ሰው መሆናቸው ያጎናጸፋቸውን አስተውሎት ተነጥቀው ከእንስሳት ጎራ ተመድበው ተገልጸዋል፡፡ ይህ ደግሞ የሀሳብና ፍላጎታቸው ግፊት፣ እንዲሁም ከዚህ ፍላጎት በመነጨ በደመነፍሳዊ ጉዞ የሚያከናውኑት ምግባራቸው ውጤት ነው፡፡ ሰው ለሰው ከመረዳዳት ይልቅ መጎዳዳት፣ ከመደማመጥ ይልቅ መነቃቀፍ፣ ከመደጋገፍ ይልቅ መጠላለፍ፣ ከመተማመን ይልቅ መጠራጠር፣

ራስን ከመሆን ይልቅ መስሎ ማደር፣ ከእውነት ይልቅ አባይነት፣ ባህርዩ ሆኖ የተገኘበትም ነው፡፡ ከእኛነት ይልቅ እኔነት፣ ተካፍሎ ከመብላት ይልቅ መናጠቅ፣ በእጅጉ ተንሰራፍቶ ያለበት፤ የመተሳሰብና መደጋገፍ ሰዋዊ እሴቶች ሲጣሱና ሲጨፈለቁ የሚታይበት የራስ ወዳዶች ማህበርተኛ ሆነው የተከሰቱበት ነው፡፡ ሰዎች ከሰው ባህሪያቸው ይልቅ እንደ ውሻ ሲናጠቁና ሲያስበረግጉ፣ እንደ ተዋጊ በሬ መንጋውን ሲያውኩ፣ እንደ ድመት አድብተው ግዳይ ሲጠባበቁ፣ እንደ በቅሎ ሲቀየዱ፣ እንደ እንስሳ በየዱርና ጫካው ድሪያ ሲፈጽሙ፣ ወዘተ ተገልጸዋል፤ በዚሁም ልክ በሀሳብና ምግባራቸው ታይተዋል፡፡

በሌላ በኩል በልቦለዱ ውስጥ ሰው ስብእናውን ከራሱ ነጥቆና አስነጥቆ የሰውነት ክብሩን በቁስ የለካበትን እውነት፣ የሰብዓዊነት መንጠፍን በልቦለዱ እንዴት እንደተከሰተ ከሜካኒስቲክ ዲሂዩማናይዜሽን አንጻር በተደረገው ትንተና ወቅት መመልከት ተችሏል፡፡ እቃ የሰው ልጅ የእጅ ስራ ውጤት ነው፡፡ ይህ ደግሞ የሰው ልጅ ሊገለገልበት እንጂ በተቃራኒው የሰው ልጅ ሊያገለግለው አልያም የሰውን ልጅ ፈጽሞ ሊተካው አይችልም፡፡ ሆኖም በየሕሊና ባርነት የምናገኛቸው ገጸ ባህሪያት አንደኛ፣ የሰው ልጅን በቁስ ልክ ሲገልጹት አንዳንዴም ከቁስ አሳንሰው ሲመለከቱት እንመለከታለን፡፡ ሁለተኛ፣ ግለሰቦች በራሳቸው ስብዕናቸውን ጥለው ራሳቸውን ከቁስ ተራ መድበው ቀርበዋል፡፡ ከዚህ ሁነቶች መረዳት የሚቻለውም ሰው ራሱን ከራሱ የስራ ውጤት ጋር አነጻጽሮ መቅረቡን፤ አልፎም ለዚሁ ለስራው ውጤት ለሆነው ቁስ አካል ተገዥ መሆኑን ነው፡፡

የልቦለዱ ገጸ ባሕሪያት የመሰረቱት ይህ የሰዎች ማህበር ለገንዘብ ሲል ኃላፊነቱን መወጣት ያቃተው ኃላፊ፣ አገሩንና ህዝቡን ለጠላት አሳልፎ የሰጠ የጦር መኮንን፣ ህሊናውን የሸበበና ሙያውን ያራከሰ ጋዜጠኛ፣ እድሜ ያጎናጸፋቸውን ትልቅነት አዋርደው የታናናሾቻቸው መጠቋቆሚያ የሆኑ ባልቴቶች፣ ሴትነትን እንደ እጅ መንሻና ጉዳይ ማስፈጸሚያ ቁስ አድርገው የቀረቡ እንስቶች እና ይሄንኑ የሚቀበሉ ባለስልጣናት ናቸው፡፡ የነዚህ በዚህ መልኩ መቅረብ ደግሞ የልቦለዱ ትልም ማራመጃያ ብቻ ሳይሆን የሰው ልጆች ምግባራዊ እሴት መለኪያና የሰብዓዊነት መንጠፍ መከሰቻ ሆነው ቀርበዋል፡፡ ሴቶች ስብዕናቸው ተዘንግቶ ከቢራና ሙዚቃ ጋር ተነጻጽረው፣ በኮርቻ ተመስለው፣ እንደ ቅርጫ ስጋ የሁሉም ሆነው ለሁሉም የሚዳረሱ፣

ለወንዶች ደስታ መፍጠሪያ እንጂ የራሳቸው ስብዕናና ምርጫ የሌላቸው ሆነው ተስለዋል፡፡

በልቦለዱ በሁለቱም አንጻር ስብዕና መፈተኑ ተገልጿል፤ ከመፈተን አልፎም አፈር ትቢያ ሲሆን ታይቶበታል፡፡ ሰው እንደ እንስሳ ደመነፍሳዊ የሆነበትና በራሱ የማይመራበት፣ ከሰብዓዊ ፍጡርነቱ ይልቅ ቁሳዊነቱ ጎልቶ የወጣበት ነው፡፡ ማህበረሰቡ ለሰራው ሰብዕናና ግብረገባዊ እሴት የማይገዛ፤ ለራሱ በተመቸውና ባስደሰተው መንገድ ራሱን እያረካ የሌሎችን ደስታና እርካታ እየቀማ የሚሄድ ሆኗል፡፡ በልቦለዱ በግልጽ እንደሚታየውም፣ የሰው ልጅ አስተሳሰብ ዋዥቋል፤ የሞራል ግዴታዎቹም ኮስምነዋል፡፡ ህብረተሰቡ ዋጋ የሚሰጣቸው ቁም ነገሮች ቸል ተብለው ተግባራቱ መረን ወጥተዋል፡፡ የኃላፊነት ስሜትና የሕሊና ዳኝነት ደብዝዞ አድር ባይነት ከአበባነት አልፎ ፍሬ አፍርቷል፡፡ ለአገርና ለወገን የሚከፈል ዋጋ ጠፍቶ ዓላማ ቢስነት ነግሷል፡፡ ሰው ከራሱ ብቻ ሳይሆን ከማህበሩና ማህበራዊና ግብረ ገባዊ እሴቶቹ ተኳርፏል፤ ተጣልቷል፤ ሰብዓዊነቱም ነጥፏል፡፡

# ማጣቀሻ ጽሑፎች


ሥነሕይወት ገዛኸኝ፡፡ (2007)፡፡ "ባይተዋርነት በሰባተኛው መልአክ፡ ትኩሳትና ሌቱም አይነጋልኝ"፡፡ ለአማርኛ ቋንቋ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ትምህርት ክፍል የድህር ምረቃ ትምህርት ክፍል የቀረበ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ነቢዩ ኢያሱ፡፡ (1985)፡፡ *የሕሊና ባርነት*፡፡ አዲስ አበባ፤ ቦሌ ማተሚያ ድርጅት፡፡

አሻግሬ አምጤ፡፡ (2003)፡፡ "ባይተዋርነት በመቅደስ ጀምበሩ ግጥሞች"፡፡ በኢትዮጵያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል ለኢትዮጵያ ሥነጽሑፍና ፎክሎር ድህረምረቃ መርሃ ግብር፡ የቀረበ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

አያሌው አስፋው፡፡ (1999)፡፡ "ሴተኛ አዳሪነት እና የሰብዓዊነት ጥያቄ በሶስት ልብ-ወለዶች ውስጥ"፡፡ የኢትዮያ ቋንቋዎችና ሥነጽሑፍ ትምህርት ክፍል የድህረ ምረቃ መርሐ ግብር የቀረበ ቴሲስ፤ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፡፡

ወልደጊዮርጊስ ወልደ ዮሐንስ፡፡ (1943 ዓ.ም)፡፡ *ሥነ ምግባር*፡፡ አዲስ አበባ፤ ትንሣኤ ዘጉባኤ ማተሚያ ቤት፡፡

የኢትዮጵያ ቋንቋዎች ጥናትና ምርምር ማእከል፡፡ (1993)፡፡ *የአማርኛ መዝገበ ቃላት*፡፡ አዲስ አበባ ዩኒቨርሲቲ፤ አርቲስቲክ ማተሚያ ቤት፡፡

ዮናስ አድማሱ፡፡(1992) "'አስረኛንኩዋ?'፤ ሀዲስ ዓለማዬሁና የማኅበራዊ ሂስ ሥልታቸው፡፡" *የኢትዮጵያ የቋንቋዎችና የሥነ ጽሑፍ መጽሔት*፡ ቁጥር 10፤ ገጽ 77-119፡፡

ያለው እንዳወቅ፡፡ (2009)፡፡ የምርምር መሰረታዊ መርሆዎችና አተገባበር፡፡ 3ኛ እትም፡፡ ባህር ዳር ዩኒቨርሲቲ፤ ተስፋ ስዩም ፕሪንቲንግ ፕሬስ፡፡

Bandura, A. (1999). "Moral disengagement in the perpetration of inhumanities". *Personality and Social Psychology Review*. [Special Issue on Evil and Violence], V. 3, pp. 193-209.

Bar-Tal, D. (2000). *Shared beliefs in a society: Social psychological analysis*. Thousand Oaks, CA: Sage.

Bloom, Paul.(2012). Religion, Morality, Evolution. *Annu. Review of Psychology*, V.63: pp.179-199. From: www.annualreviews.org

Fulkerson Holly. (2007). "Georg Büchner's Woyzeck: An Individual's Struggle Between Society and Religion". A Thesis submitted to the Department of Modern Languages and Linguistics; Florida State University; Ffrom: http://diginole.lib.fsu.edu.

G.E.M. Anscombe. (1956). "Modern Moral Philosophy". *Jornal of Philosophy;* V. 33, No.124. From:http://www.pitt.edu.

Green, Ronald M.. (2014). "Kant's Philosophy of Religion and the Challenges of Moral Commitment". *Religious Inquiries.* V. 3, No. 5, pp. 21-34.

Gunn, Giles B. (1979). *The Interpretation of Otherness: Literature, Religion, and the American Imagination.* New York: Oxford University Press.

Haslam, Nick. 2006. "Dehumanization: An integrative review". *Personality and social psychology review*, Vol. 10, No. 3, pp. 252–264.

Haslam S. Alexander and Reicher Stephen D. (2012). "When Prisoners Take Over the Prison: A Social Psychology of Resistance". *Personality and Social Psychology Review;* V. 16(2),PP. 154 – 179. From: http://pspr.sagepub.com

Henry, Home and Lord Kames. (2005). Natural law and enlightenment classics. G.Knud Haakonssen. (Ed.) Essays on the principles of morality and natural religion; published by Liberty Fund, Inc.

Jo-Ann, Tsang. (2002). "Moral Rationalization and the Integration of Situational Factors and Psychological Processes in Immoral Behavior". Southern Methodist University, Dallas: *Review of General Psychology*; Vol. 6, No. 1, p. 25–50.

John, Wolkowski. (2011). "The Moral Value of Literature: Defending a Diamondian Realist Approach". A Thesis presented to The Faculty of Graduate Studies of The University

of Guelph; for In partial fulfilment of requirements for the degree of Master of Arts in Philosophy; University of Guelph, Ontario.

Karim, Asim and Others. (2012). “Literature and Morality”. *International J. Soc. Sci. & Education,* Vol. 2 Issue 2, ISSN: 2223-4934 E and 2227-393X.

Luna, Aniuska M. (2015). "The Components of Dehumanization," *Peace and Conflict Studies*: Vol. 22: No. 1, Article 2.

Manninen, B. A. (2018). “Dehumanization”. *The Society of Philosophers in America*, *Civil American*, Volume 3, Article 2, Pages 1-13, ISSN 0271–0137. From: https://www.huffingtonpost.com/ author/bertha-alvarez-manninen.

Marc, Hauser and Peter Singer. (2011). ‘Morality without religion”. From: http://pactiss.org/

Martínez, Rocío and others. (2012). “Are they Animals or Machines? Measuring Dehumanization”. *The Spanish Journal of Psychology*, vol. 15, No. 3, pp. 1110-1122. From: http://www.redalyc.org/articulo.oa?id=1722448902.

McKay, Ryan and Whitehouse, Harvey. (2014). “Religion and Morality”. *Psychological Bulletin*; Vol. 141, No. 2, 447– 473. From: http://dx.doi.org/

Moller, Arlen C. and Deci Edward L. (2010). “Interpersonal control, dehumanization, and violence: A self-determination theory perspective”. *Group Processes & Intergroup Relations;* V. 13(1), pp. 41–53. From: http://gpi.sagepub.com

Nel, P.J.. (2008). “Morality and religion in African thought”. *Centre for African Studies*, University of the Free State.

Oliver, Sophie. (2011). “Dehumanization: Perceiving the Body as (In)Human”. Kaufmann, Paulus and etal.(Eds.). *Humiliation*, *Degradation*, *Dehumanization*, Library of Ethics and Applied Philosophy, V. 24, DOI 10.1007/ 978- 90- 481- 9661- 6_7; From:www.springer.com

Ronald M. Green. (2014). “Kant’s Philosophy of Religion and the Challenges of Moral Commitment”. *Religious Inquiries*، Volume 3, No. 5, pp, 21-34.

Rossano, Matt J. (2008). “The Moral Faculty: Does Religion Promote ‘Moral Expertise’?”, *International Journal for the Psychology of Religion*, V. 18:3, pp. 169 — 194.

Smith, David Livingstone. (2014). “Dehumanization, Essentialism and Moral Psychology”. From: https://www.cl.cam.ac.uk

Vaes, Jeroen and others. (2012). “We are human, they are not: Driving forces behind outgroup dehumanisation and the humanisation of the ingroup”. *European Review of Social Psychology*, V.23:1, pp. 64-106. From: http://dx.doi.org